  It is the act of silencing the members who speak loudly and openly in favor of the principles of our party EPRP (D). Thus, is there any wrong doing about naming and shaming ato Mersha that he is a conspirator? Any logic of induction or deduction can easily approve that ato Mersha is a conspirator and manipulator with very little input for productive and innovative initiatives.

3. **The explanation as to why I have characterized ato Mersha as a man who is perusing ethnically biased hate-politics against people like me who are originally from Tigray killil.**

- Here, I would not go deep into the case, unless and otherwise invited or provoked to do so. But I would like to call the attention of "Yehigna Yefth Askebari Commission" that ato Mersha and Co. has conspired against members of EPRP (D) who are original from Tigray Kill.
  The statistics confirms that ato Mersha is very busy about people from Tigray. For example, ato Mersha has accused me /Haileselassie/ and ato Beyene of being "Weyane" while his close pupate has announced in his "Yenba-Bmambis pal talk chat»"that the purging of those comrades of EPRP (D) who are originally from Tigray/the Agamies / are progressively functional. The pal talk chat has made explicit the names of the few left over Tigrians (agamewoch); namely Selamawit (fifi)/, Yohannes, Tesfahune and Mesfin mario (Toronto) among others. In the pal talk chat; there are also some speculations about those who are Agame and Gondere.

- In one way or another "Yenb-Banbis pal talk chat" is the manifestation of internal conflict and conspiracy generated and undergoing by ato Mersha. A sound example for this is that it articulates that "<u>Yenba: last month in our congress we kicked out those left behind"</u> (underling is mine.)

- Thus there is no doubt that ato Mersha and his clique are indulged in unnecessary, unfruitful and catastrophic campaign of ethnically asserted hate-politics against "Agames" and "Gonder" comrades of EPRP (D).

- Shall we be silent against a deadly conspirator who runs ethnically founded hate politics? Should we not expose the wrong thinking men who endanger our unity, integrity and continuity?

**<u>My Conclusion.</u>**

Dear "Yehigna Yemebt Atebaki commission" members,

Until this day I have not intended to accuse ato Mersha and Co. for instigating ethnically based segregation and discrimination of comrades like me for I have had always thought that there will be a better day to convince ato Mersha to do so. But today I do accuse ato Mersha for all his wrong doings I have enumerated here above, because I lost my hope in him.

- I am looking forward for justice!!!

**As I have repeatedly stated:**

- It was ato Mersha who has conspired and manipulated against me so as to evict me from my EPRP (D) membership, by convincing my comrades here in Norway.
- It was ato Mersha who accused me several times of being "Weyane" without any substantial evidence. He continued to do so for only reason that I used to challenge him

or take my own stand in different opinions. I could not find myself to be finger-puppet of ato Mersha.

- It was ato Mersha who has accused me by fabricating a crime of my conspiracy to assassinate him. After he realized that he badly failed in his plotting, he thought that he changed the tactic and accused me in our OC (supreme council) as if I have conspired to assassinate him. Again he failed to show his case of allegation was true and the council rejected his unfounded fabrications. But the council directed him to take on board the case to the Commission.
- I have been expecting ato Mersha to bring the case of " conspiracy for assassination" up to the commission officially. Now that I have realized that ato Mersha has dropped the case from pushing forward, it is my turn to bring the case open and official to all members of our party as I did it on our net-work.
- Now it is my turn to expose ato Mersha from further damaging our integrity on individual level as well as on our party level.
- Thus I hereby officially appeal to you/ "Yehigna Yemebt Askebari Commission" to stop this comrade and convict him for his destructive measures enlisted here above.

**As my respected comrade:**

- I gave ato Mersha good time in which he can reconstruct himself and reinstate the true spirit of EPRP/EPRP (D). But his deeds have proved that he is a man who cannot recover from his misconducts and principal mistakes.
- In times, I thought that ato Mersha was doing all the dirty things for the sake of our party. I was always considerate in thinking that he will be convinced one day after he found out that I am not "Weyane". Of course after being exhausted for nothing.
- But now, I found out that I was wrong about ato Mersha. Finally, I was convinced that ato Mersha was born to be a deadly conspirator who is highly affected and damaged by inferiority complexes. I have also learned that he does not hesitate to take any measure of revenge if any one criticizes him, and stand in his way when he strives hard to win for power.

**<u>My appeal to "Yehigna Yemebt askebari Commission"</u>**

- To revise the embargo imposed on me by ato Mersha and Co. for I have exposed his misconducts as stated in my articles "For your information", "COMRADES SHOULD NOT BE ABASED AND HARASSED, RATHER SHOULD BE HEARD AND ADDRESSED !", and "LETS US NOT DIGRESS FROM THE PRINCIPAL ISSUE TO MINOR"
- First and for most I appeal to you to restore my write of participating in the network family as any member of EPRP (D).
- I believe that justice should be done and govern upon all of us and it should not be in the hands and pockets of the accused; but that it must serve us all equally. While ato Mersha being accused for all inexcusable misdeeds he remain enjoying all the rights of EPRP (D) membership, I believe that I should not be cornered out by reasons of injustice. After all, as I have already stated in my previous appeal to you, I have never heard of anyone who have been excommunicated from the net-work family like me for his/her expressing ones thoughts and grievances!!!
- At last, once again, I am appealing for justice for the injustice done upon me by ato Mersha Yosuf and his Co. I remain looking forward to hear justice from you as you are

the only hope I and people like me look upon to safe guard the true justice which is invaluable by the spirit of EPRP (D).

- We need to make clear that something wrong against the values and principles of our party, EPRP (D), must come to an end. We do not afford to live in darkness and play with eminent danger to our integrity. We must solve our problem of corruption, opportunism and liberalism.
- Let us act quickly to reconcile ourselves and stick to our oath we begotten with our fallen comrades, and renew ourselves afresh.

Truth shall triumph.

Haileselassie Yohannes.

Footnote #4

KKKKKKKKK

bambis_1: **selam aba**

Yenba: hey, selam bambis wondeme

Yenba: good to see you my dear

bambis_1: **endet neh? how the family and business?**

Yenba: dehina negn wondeme

Yenba: antes? beteseb endet new?

bambis_1: **dehna,**

Yenba: America business is down

Yenba: leji balebetih endet nachew?

bambis_1: **u did not go to chicago this year?**

Yenba: no, sera neberegn ezih

bambis_1: **i see**

Yenba: endet newu nuro abye?

bambis_1: **how is our new party doing (eprpd)?**

Yenba: shegaw dehina newu woye?

Yenba: it's fine bambis, kenezia ke agamewoch teleyayetenal

bambis_1: **kkkkkkkkkkkk**

Yenba: kkk

Yenba: ewuneten newu bambis

Yenba: they played on us for so long

bambis_1: **what are they (agamewoch) doing any way now a days?**

Yenba: when I hear now those left behind are all Tigrians, Iyasu, his wife, Ayalnesh etc

bambis_1: **kkkk**

Yenba: ere tewogn wondeme, techawotubin eko

Footnote #4

bambis_1: **how are they doing any way ?**

Yenba: They will never be better, you know, behind the seen they work for Tigray interest

bambis_1: **is Ayalnessh agame too? gude eko nehu**

Yenba: yes

bambis_1: **wow**

Yenba: that is what I heard too

bambis_1: **wow**

Yenba: that is why woyane release her from preson

bambis_1: **how about Fassika?**

Yenba: No Fassika is fooled

bambis_1: **i think so**

Yenba: he is from wollo

Yenba: but Tegegn is another agame and Gondere

bambis_1: **kkkkkkkkkkkkk**

bambis_1: **but we have to becarefull they may be some among us**

Yenba: No way bambis, from now on I will never deal with any of those tigrians

bambis_1: **me too**

Yenba: last month in our congress we kikked out those left behind

bambis_1: **i have liked/trust that Yohanes and his family**

bambis_1: **never**

Yenba: he is out

Yenba: me and him confronted in the congress

bambis_1: **ihope so for good**

Yenba: believe me we no more be fooled

bambis_1: **how about his family? from Atlanta (fifi and tesfahune)**

Footnote #4

Yenba: His brother too is out

Yenba: yes, fifi too

bambis_1: **good job**

Yenba: they more closer to iyasu you know

bambis_1: **u know between me and u, Mesfin mario (Toronto) is half tigre too**

Yenba: Selamawit (fifi) is boycotting our room

bambis_1: **i saw that kkkkkkkkk**

Yenba: no he is half Eritrian

Yenba: but he hate woyane agame

bambis_1: **is he? i though he is from agame kkkkk**

Yenba: no

bambis_1: **ok**

bambis_1: **we need to clean our house**

Yenba: yes

Yenba: we will

Yenba: ayezon abye

bambis_1: **who is left now?**

Yenba: none

bambis_1: **talk to u soon i need to go**

bambis_1:

Yenba:

የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 23, 2010)
የአሉላ ምስክርነት
ለ፡ ኢሕ አፓ ዴ አመራር ምክር ቤት አባላት በሞላ

ተወልጄ ያደኩት ከምወዳት ሀገሬም እስክወጣ የኖርኩት ካዝእንችስ ነው። በ1970 ዓ.ም. ህዳር 23 ቀን ወደ ከፍተኛ 15 እስር ቤት ተወርውሬ ለ 1 ዓመት ቆይታ ያደረኩበት ቤት መለያ ስሙ ባንቢስ እስር ቤት ነበር። ከባንቢስ በስተጀርባ ስለሚገኝ።

ባንቢስ በከፍተኛ 15 ቀበሌ 34 የሚገኝ የአንድ ጣሊያናዊ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ሲሆን ከዓፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ያለ በገቢያቸው የደለቡ የሚገበዩበት መደብር ነው። ከፍተኛ 15 እስር ቤት እያለን የእስር ቤቱን መራራነት ለማውጋት እዚያው አንድ ድምጻዊ ያዜመው የነበረው ዜማ ትዝ ይለኛል፡

"አይባባ . . . አይባባ . . . ሆዴ
ባንቢስን ማን ባሻገረኝ
ካዛእንችስ ጉዳይ ነበረኝ . . . "

ባምቢስ ሲባል ሁሌም ከፍተኛ 15 እስርቤትና የዛሬ 30 ዓመት ሰቆቃው ለታሳሪው ትዝ ሲል፡ ዋና ፈላጭ ቆራጭ ለነበሩት የቀይ ሽብር ተዋንያን ኮሚቴ አባላትና ገዳይ የቀበሌ ካድሬዎች በተቃራኒው ያደረጉት ስቃይና ያፈሰሱት ደም ፊታቸው ድቅን እንደሚል መተንበይ ይቻላል።

በየዓመቱ የካቲትንና ዝክረ ሰማዕታትን ለሦስት ጊዜ በVEDR በአቀረብኩበት ወቅት የከፍተኛ 15 ትዝታዬንና በዚህ ጉደኛ እስር ቤት ሕይወታቸውን ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ነፃነት የሰውትን የደርግ ሥርዓት የገደላቸውን ስማቸውንና ገድላቸውን አስታውስ ነበር። በዚህ ወቅት ባንቢስ በሚል የፓልቶክ ስም ይዞ ቴክስት የሚያደርግ ታዳሚ ትዝ ይለኛል። ባንቢስን በመጥሯ ትዝታው ስለማስታውስ በውስጤ ለምን ይኼን ስም መረጠው እል ነበር። አንዳንዴ ስሙን በፓልቶክ ሳየው። ምናልባት በዚያ እስር ቤት የኖረና መራራነቱን ለማስታወስ ይሆናል ወይም ባንቢስ መደብር ውስጥ ተቀጥሮ ሲሰራ የኖረ ይሁን ወይስ የዚያ አካባቢ ነዋሪ ይሆን እያልኩ ግምት እወስድ ነበር። ይህ ሁላ አተታዬ ታዲያ ባንቢስ የሚለውን የፓልቶክ ስም እንዴት እንደማስታውሰው ለመግለጽ መንደርደሪያ ይሆን ብዬ ነውና ማስተላለፍ ወደ ምፈልገው ጉዳይ ልግባ።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 5

**የንባ-ባንቢስን ጉዳይ እህት አበባ በኢሕአፓ ዴ መወያያ መድረክ ሐምሌ** 12 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**. (July 19, 2009) **ከመልቀቋ በፊት ማክሰኞ ማታ ሐምሌ** 6 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**. (July 14, 2009) **ስልክ ይደወልልኛል።**

**አሉላ ፡ ጤና ይስጥልኝ ወንድሜ የንባ**
**የንባ ፡ አሉላ ወንድሜ እንደምን አለህ**
**አሉላ ፡ ደህና ነኝ**
**የንባ ፡ ወንድሜ እባክህ ጉድ ሆንኩልህ ..እህ..እህ..እህ የሲቃ ትንፋሽ**
**አሉላ ፡ ምነው የንባዬ**
**የንባ ፡ አዬ እባክህ**
**አሉላ ፡ ምንድነው?**
**የንባ ፡ አላስፈላጊ ነገር በፓልቶክ ተናገርኩ እባክህ**
**አሉላ ፡ ምን አልክ የንባዬ**
**የንባ ፡ አይ እንደው የዛሬ ቀን**
**አሉላ ፡ ምንድነው የንባ**
**የንባ ፡ እባክህ ከማይሆን ሰው ጋር አላስፈላጊ ነገር ተለዋወጥኩ**
**አሉላ ፡ ምን ተለዋወጥክ? ማነው እሱስ?**
**የንባ ፡ ባንቢስ በሚል ስም የሚገባውን ታውቀዋለህ**
**አሉላ ፡ ማን እንደሆነ አላውቅም ግና በፓልቶክ ስሙ ትዝ ይለኛል፡ አንዳንዴ አየዋለሁ**
**የንባ ፡ በፕራይቬት ጠርቶ የማይሆን ነገር አናገረኝ እባክህ እ…ህ…ህ…**
**አሉላ ፡ ምን አለህ? ምን ተናገርህ?**
**የንባ ፡ እንደው እነዚህን ሰዎች ወያኔዎች ናቸው እያልኩ የማይሆን ነገር አልኩት፡ እንደው ምን ልበልህ እባክህ፡ የጭንቅ ድምጽ**
**አሉላ ፡ ምንድነው የምትለኝ? ማንን ነው የንባ?**
**የንባ ፡ ይችን አበባንና ሌሎችን ነው ወንድሜ**
**አሉላ ፡ ግልጽ አርገህ ንገረኝ ምንድነው ያልከው?**
**የንባ ፡ አይ ስለ አበባንና ዮሐንስን ሲጠይቀኝ አይ እነሱ ወያኔዎች ናቸው አልኩት ምልልሱም አመራሩ ጋ ደርሷል**
**አሉላ ፡ ቀዳህ?**
**የንባ ፡ አይ ቴክስት ነው የተለዋወጥነው፡ ልውውጡ አመራሩ ጋ ደርሷል**
**አሉላ ፡ እንዴት አወቅህ?**
**የንባ ፡ ከአመራሩ አንድ ሰው አናግሮኛል**
**አሉላ ፡ ምን አልክ?**
**የንባ ፡ ምን እላለሁ እባክህ፡ አብዬ በቃ ድርጅቱን መልቀቅ አለብኝ**
**አሉላ ፡ ዝርዝሩን ለምን አትነግረኝም፡ በዚህ ነው እንዴ የምትለቀው?**
**የንባ ፡ ምኑን ልንገርህ እንደው የማይሆን ስህተት ነው የሠራሁት**
**አሉላ ፡ አምነሃል ለአናገረህ አመራር**
**የንባ ፡ አዎ**
**አሉላ ፡ ይቅርታ ብትጠይቅስ**
**የንባ ፡ የሚሆን አይመስለኝም**
**አሉላ ፡ በል አይዞህ ተባብለን ስልኩ ተዘጋ።**



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 5

*የንባ ያወጋኝ ጉዳይ በደንብ አልገባኝም። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ስናወራ አበባን፣ ዮሐንስንና በየነን "ወያኔ ናቸው" "አሉላ፣ እኔ በእርግጠኝነት አውቃለሁ፣" እያለ ሲደጋግም አይጥመኝም ነበር። ሥራዬ ብዬ ግን አልከራከረውም ነበር። በተለይ እህት አበባ በወቅቱ በ*VEDR *በተፈጠረው ጉዳይ ከእኔ ጋር የነበረን የተለየ ግንኙነት ሻክሯል፣ ተቋርጧል። በተጨማሪ በ*VEDR *"እየረበሸች" ነውን ስለምሰማ በዚያ ምክንያት የሚሰጠው የተሳሳተ አመለካከት ቢሆንም ገፍቼ ግን ልናገረው አልደፈርኩም። ከእህት አበባም ሆነ ከሌሎች በነበረው አለመግባባት* VEDR*ን ከለቀቅሁ በኋላ በተከታይ ከየንባም ሆነ ከነበለት ጋር ችግር እንዳለ እሰማለሁ። ነበለትም ለቆ ወጥቷል። የንባ ግን አልፎ አልፎ ያለ ይመስለኛል።*

*ይህ በእንዲህ እንዳለ የንባ ስላወራኝ ጉዳይ ብዙም አልተጨነኩም። ምክንያቱም ዝርዝሩን ስላላየሁ ይመስለኛል። በተጨማሪም ሁሌም ወያኔዎች ናቸው የሚላቸው ስላሉ ይህንንኑ ነው ያለው በሚል ትኩረት አልሰጠሁትም። ብቻ አጠንክሮ ድርጅቱን መልቀቅ አለብኝ ያለው ከምን አንጻር እንደሆነም ግራ ገባኝ።*

*ሐምሌ* 12 *ቀን* 2001 *ዓ.ም.* (July19, 2009) *እህት አበባ የለጠፈችውን "የንባ-ባንቢስ" ጉዳይ ሳይ እጅጉን ደነገጥሁ። ደጋግሜ አነበብኩት እንዴ አልኩ። እውነት የንባ ነው? አልኩ። ከማውቀው ባህሪው አንፃር ላምን አልቻልኩም። መቀበል ከበደኝ። ወዲያውኑ ስልክ አነሳሁ፣*

*የንባ ፡ ሰላም አሉላ ወንድሜ*
*አሉላ ፡ እንደምን አለህ የንባ የተለጠፈውን አየኸው*
*የንባ ፡ አዎ አየሁት አብዬ*
*አሉላ ፡ በጣም ከባድ ነው እንዲህ አልመሰለኝም ነበር የንባ*
*የንባ ፡ አይ ከባድ ነው ድርጅቱን መልቀቅ ይኖርብኛል፣ በእኔ ምክንያት እንዲጐዳ አልፈልግምና መልቀቅ ነው ያለብኝ*
*አሉላ ፡ ይቅርታ ብትጠይቅስ*
*የንባ ፡ የሚሆን አይደለም*
*አሉላ ፡ ከአመራር ደርሶት ያናገረህ ማነው*
*የንባ ፡ መስፍን ዲሲ ነው*
*አሉላ ፡ እንደኔ ከሆነ ጉዳዩ ከባድ ነው ይቅርታ ጠይቅና የሚሆነውን እይ*
*የንባ ፡ እንጃ እባክህ*
*አሉላ ፡ ተረጋጋ በቅድሚያ ሳይውል ሳያድር ይቅርታ ጠይቅና ቀጣይ ሂደቱን ተከታተል*

*በዚሁ ተለያየን። በጣሙን እንቅልፍ ነሳኝ። ጉዳዩ አበባን ዮሐንስን ምን ያልነካው አለ? የፓርቲውን ገጽታ በአጠቃላይ ያበላሸ ሁኔታ መሆኑ ልገምተው ከማልችለው ሰው፣ ከማከብረው ሰው ሳይ፣ አብዱል እንዴ? እውን በጤናው ነው? ያልኩት። ወያኔዎች ናቸው እያለ በተደጋጋሚ የሚያወራው እኔ ጋ ብቻ ሊሆን እንደማይችል ገባኝ። ለዚህም ነው ከቤታችን አልፎ በፓልቶክ ደፍሮ የተናገረው፣ ግን ሁሉን የሚያይ አምላክ ከማይሆን ጣለው? አጋለጠው? ለድርጅቱ ያለውን ፍቅርና በአነጋገሩም ሥርዓት ያለው አድርጌ ስለምወስደው የማከብረውና የምወደው ወገኔ ነው። እራሴን ሲመክረኝ ሲያበረታታኝ ነውና የማውቀው አንዳንድ አባባሎቹን ቁብ*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 5

አልሰጠሁትም ነበር ጽሁፉን ካየሁ በኋላ ግን ማጠንጠን ጀመርሁ። ድርጅቱን መልቀቅ አለብኝ ያለው ቢከብደኝም በቅድሚያ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት ላሳምነው ፈለግሁ። እጅጉን ለማከብረው ወንድሜ መቼም መረጃዬ አንተነህና እንዲህ ዓይነት ጉዳይ ሰምቻለሁ በማለት እህት አበባ በመድረኩ ከመለጠፏ በፊት ሁኔታውን አጫወትኩት። የጉዳዩንም ሚስጥርነት ስገልጽለት እስከዛሬ የያዝኩትን ዛሬ አወጣሁት? ለምን ያዝኩት ምክንያቴን እገልጻለሁ ጽሁፌን ከመቋጨቴ በፊት።

ጉዳዩ በመድረኩ ይፋ ከሆነ ከ24 ሰዓት በኋላ ሰኞ July 20, 2009 ቀን የንባ ወንድሜ በመወያያ መድረኩ የለጠፈውን ክህደት ተመለከትሁ። ግራ ገባኝ። ተያይዞም በፓልቶክ Yenba የሚለውን መለያውን Yenba1 አደረገው። እስከዛሬም ይህ መሆኑን ልብ ብላችኋል? ያላደረገ ሰው ለምን 1 ቅጥያ አስፍለገው? መልሱን ለአንባቢው።

ወዲያው ደወልኩለት

የንባ ፡ ሰላም አሉላ እንደምን አለህ?
አሉላ ፡ አለሁ ደህና ነኝ
የንባ ፡ የለጠፍኩትን አየህ?
አሉላ ፡ አየሁ፡ በጣም ተሳስተሃል የንባ
የንባ ፡ አይ ደግሞ ለነ'ኒህ ብዬ ድርጅቱንም አለቅም፡ ይቅርታም አልጠይቅም፡
ከበፊቱ በተለየ የአነጋገር ቃና

ነገር እንዳለ ገባኝ

አሉላ ፡ ምን ማለትህ ነው ስህተት ነው የሠራኸው
የንባ ፡ ችግር የለውም
አሉላ ፡ መስፍን ምንም አይል? ማመንህን ሌላስ ያወቀ የለም?
የንባ ፡ አይ በሱ በኩል ችግር የለውም፡ ለአመራሩም ዶር ጌታቸው ስላቀረበው
በመስፍን በኩል አላወቁምና ችግር አያመጣም።
አሉላ ፡ መልካም

በዚሁ ተለያየን። ግራ ገባኝ፡ ምንድን ነው የማደርገው? የጉዳዩን አካሄድ ልከታተል ወሰንኩ። አንዳንዶች የየራሳቸውን ግምት ሲሰጡም ውዝግቡ ውስጥ መግባትን አልመረጥኩም። ምክንያቱም ቢያንስ መስፍን ዲሲና፡ መንግሥቱ ጉዳዩን እንደሚያውቁ ስለተረዳሁ ሂደቱን ማጤኑ የሚሻል እንደሆነና አንድ ቀን ግን ቃሌን እንደማሰማ ወሰንኩ።

የኮሚሽኑን በ October 10, 2009 የተጻፈውን ውሳኔ አየሁት። አሳዛኝ ውሳኔ አልኩ። ለየንባ ያደላ። ቢያንስ ሁኔታውን የማያውቁ ሰዎች ስለ ጉዳዩ በሁለቱም በኩል ልናጣራ አልቻልንምና ሁለቱንም ወገን በማያዳላ ሁኔታ አንደምታ ያለው ውሳኔ ላይ ለምን አልደረሱም አልኩኝ። በዚህ አሳፋሪ ጉዳይ አንድ አንጋፋ ፓርቲ ይታመሳል አልኩኝ። በጉዳዩ አውቀው የተኙ እንዳሉ ስለምረዳ በአለው ውዝግብ ውስጥ መግባቱ ጉዳዩን በዋህነት ካልተረዱት ጋር መላተምን እንዳያመጣ ሰጋሁ። ለድርጅቱም አሳፋሪ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 5

ጉዳት መሆኑን ብረዳም በዚህ ጉዳይ ስማቸው የተጠቀሰው ከደረሰባቸው ስነልቦና ጥቃት ባሻገር የጉዳዩ ፈጣሪዎች ተደርገው ሊፈረጁ ሲከጀል ግና እጅጉን ይቆረቁረኛል። "ጅራፍ እራሱ ገርፎ . . ." እንዲሉ ይባስ ተብሎ በድፍረት ወያኔነታቸውን ለማሳመን የሚካሄደው የንባ ዘመቻ የነዚህ ጥቂት ሰዎች መጨረሻው መጨረሻ እንዳይሆን ቢገባኝም ፓርቲውን ግና ምንኛ እንደምንጎዳው ተገነዘብሁ። ዛሬም ለደረስንበት አስከፊ ሁኔታ ብታምኑም ባታምኑም "የንባ ባንቢስ" ጉዳይ አብላጫውን ድርሻ ይይዛል።

በቅድሚያ የተነሱ መሠረታዊ ድርጅታዊ ጉዳዮች ወደ ጎን ተትተው ጉዳዩ "የንባ ባንቢስ" ጉዳይ ሲሸፍነውና ከኮሚሽኑም ውሳኔ ባሻገር አመራር ካውንስሉም አባላትን ለማባረሪያ የክሱ አካል ሲያደርገው እየታየና ሀቅ በውሸት ሲጀቦድ፡ "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" ብሎ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም። መሆንም የለበትም።

በዚህ ሂደት ላይ እንደበፊቱ ባይሆንም ወንድሜ የንባ ዘግየት እያለ ይደውልልኛል። በደወለ ቁጥር "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ አስቦትም ይሁን ሳያስበው ወደ የንባ-ባንቢስ ጉዳይ ይገባል። ቀደም ሲል ገና ከጅምሩ ያወራኝ እያባነነው ይመስለኛል አቅጣጫውን በሌላ መልኩ ለራሴ ሊገልጽልኝ ይሞክራል። ይባስ ብሎ አንድ ቀን ዶር ጌታቸው "እንዳቀነባበረው" ሊያወራኝ ሞከረ። ለራሴ ያወራውን እራሴን ሊክደኝ ሲሞክር በመንፈስ ጭንቀት ላይ መሆኑን ብረዳም "ምነዋ የንባዬ አሉላ እኮ ነኝ" አልኩት። ዝም አለ። ከዚያ በኋላ መደወል አይደለም ጭራሹን ጠፋ። ውስጡ ነጻና እውነተኛ የሆነ ሰው ሁሌም ነጻ ነው። ስህተትን ሰርቶ ስህተትን አምኖ ተቀብሎ ይቅር በሉኝ ብሎ ወደፊት መጓዝን የሚፈራ ሰው ግና የፊቱን ስህተት ለመሸፈን ሌላ ስህተት ይሠራል፡ ቀጣዩንም ለመሸፈን ሌላ ይደግምበትና በስህተት ደረጃ እየተረማመደ ወደ አደገኛ ጉዞ ላይ ይሠማራል። ይህ ነው የወንድሜ የንባ ጉዞ። "የንባ-ባንቢስን" ጉዳይ በመጋለጡ ወዲያውኑ ከሙሉ ስሜቱ ይቅርታውን ማሰማት ሲገባው መሸፈኛው ይበልጥ በየአካባቢው የሞባይል ስም ማጥፋት ዘመቻ፡ ለአባላት መባረር ጉዳዩን ማቀናበር፡ ሚስጥሩን የሚያውቁትንና ያልተባበሩትን ማጥቃት፤ በቀጣይነት ደግሞ ነገ ሌላ ገና እናያለን። "በስህተት ላይ ስህተት፡ ስህተት ተደርቦ፤ ሊያጠፋን ነውና እኛን አንገብግቦ" ማለቱ በቂ ይመስላል።

"የንባ-ባንቢስ" ጉዳይን የሚያውቁ አመራር አካላትና የንባ በድርጅታችን በተከሰተው ውስጣዊ ችግር ድርጅትን በማዳን ስም እራሳቸውን እየተከላከሉ መሆኑ ግልጽ እየወጣ ባለበት ሁኔታ ይህን ጉዳይ በመጪው ጁላይ ኮንፈረንስ ላይ ለአባላት በማሳወቅ የንባ እዚያው መድርክ ላይ ኢሕአፓ ዴ ንና አባላቱን ይቅርታ ይጠይቅ ዘንዳ ሀሳብ ነበረኝ። ግና ከኮንፈረንሱ በፊት በቅድመ ዝግጅትነት የተያዘው በአንዳንድ አባላት አካሄድና አቀራረብ አባላትም ማዘናቸውን እንደትብብር በመውሰድና የአንዳንዶች ንዴትና ብስጭት ለፍርድ የተመቻቸላቸው ጥቂት አመራር አካላት የወሰዱት ከአባልነት የማገድ ሂደት በአባላት ዘንድ ትርታውን አድምጦ ቀጣዩ የበለው ጅራፍ ሲገመድ ያሳዝናል። በዚህ 11 ገጽ አዋጅ አባላትም ተደናግጠው ዝም እንዲሉ የሚደረገው ዘመቻ ጊዜያዊነቱን ካለመረዳት የመነጨ የስህተተኞች አመራር የሚመሩት የኢሕአፓ ን ልጆች መሆኑን ለደቂቃ እንዲያስቡት ይገባል።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 5

ዶር ጌታቸው በፓርቲያችን በተፈጠረው ውዝግብ የመረጠው አካሄድ አባላቱን ማሳዘኑን የተገነዘቡና ለቀጣይ ውሳኔያቸው የተመቻቸላቸው እኚህ ጥቂቶች በየንባ-ባንቢስ ጉዳይ ዶር ጌታቸውን ሲወነጅሉ እንዲህ አስቀምጠውታል ". . . ዶር ጌታቸው ይህን ወረቀት ያገኘው በርግጥ ከሌላ ምንጭ ነው? ወይስ በተወሰነ ደረጃ ቅሬታ አላቸው የሚላቸውን ግለሰቦች ልብ በመሳብ ድርጅት የማፍረስ ሤራ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከዛ ጊዜ በኋላ የሆኑትንና ያደረጋቸውን ተግባሮች መመልከቱ በቂ ነው።" የጥቅሱ መጨረሻ ከባለ 11 ገጹ ሠነድ ግጽ 7 መጀመሪያ ላይ።

አዎ የዶር ጌታቸው አቀራረብ በራሱ ላይ ችግር ማምጣቱ ቢታወቅም እነ መስፍን ዲሲ ከየት አግኝተው የንባን አናገሩት? ለምንስ የንባን አመኔታ እንደአመራር አካልነት ለመደበቅ ተፈለገ? መልስ ለአንባቢያን። ይህ ነው የማኀተቤ ምስክርነት።

ይህንን ሚስጥር የሚያውቀው አሉላ እንጁ የጥቃቴ ምክንይት እንደሆነ ነጋሪ አልፈልግም። ይገባኛል። ሰው ባላደረገው፡ በሌለበት ጉዳይ ሲወነጀል ያውም እያወኩኝ ተባባሪ ልሆን ኀሊናዬ አይፈቅድምና ስለ የንባ-ባንቢስ ጉዳይ ምስክርነቴ ይህ ነው። <u>እንደ ሃይማኖቴ መጽሐፍ ቅዱስ ይዤ፡ እንደ ፖለቲከኛነቴ የሀገሬን ባንዲራ በቀኝ እጄ የኢሕአፓን አርማ በግራዬ ይዤ በማከብራቸው አባላት ፊት የእውነት ምስክርኔቴን የማቀርብበት ጊዜው እሩቅ አይሆንም።</u> ይህንን ጉዳይም በተደጋጋሚ በቅርቡም ወደ ዳላስ በአደረኩት ቆይታ ለየንባ "ሌላ ቢቀር በየንባ-ባንቢስ ጉዳይ ሲወነጀሉ ለኀሊናህ ምን ይሰማዋል?" የሚል ጥያቄ ድረስ ብገፋም አርፌ እንድቀመጥ ከቀስታ እስከ ቁጣ ባለ አንደምታ፡ ከመማጸን እስከ ዓይን ማፍጠጥ ቢሠነዝርብኝም ውስጤን እየከነከነኝ እንደማይኖር፡ መታወቅ ያለበትን ማሳወቅ አለብኝና አንድ ሰው በሠራው አሳፋሪ ስህተት ኢሕአፓ ዴ ሲታመስ አይኖርም። ይህ ጉዳይ አሁንም ስህተትን የሠራችሁ ሁላ አምናችሁ ለይቅርታ ካልተዘጋጃችሁ ነገ ደግሞ ገና ባንቢስ ራሱን ሲገልጽ መነሳቱ አይቀርምና ጥንት ያልፈራነውን ሂስና ግለ ሂስ ዛሬ አንፍራው። መፍትሄው ለኮሚሽን ልኮ ጊዜ ማጥፋት ሳይሆን ይቅርታ መጠየቅ ነው።

በሕግና የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሽን ውሳኔ አገላለጽ "የንባ-ባንቢስን ጉዳይ ኦሪጅናል ባለማግኘታችን" ይላል። አንድ የራሳችን አባል tentag በሚል ኢሜል አድራሻ ያለው (አቶ ፋሲጋ በለጠ እንደሆነ ይገመታል) የላከለትን ልኮልኝ በመረጃ የያዝኩትን አባሪ አድርጌላችኋለሁ። ይህ መረጃ ግና ሌሎችም ደርሷቸዋል የሚል ግምት አለኝ።

ወንድሜ የንባ በዚህ መልዕክቴ ሊከፋ አይገባም። ለኢሕአፓ ዴ የቆምኩኝ ስለሆነ። አሉላ "ቀጣፊ" ለማለት ከመቃጣት ይልቅ ይህንን ከባድ ስህተት አራግፎ ጥሎ የሰላም እንቅልፍ ቢተኛ ይብጀዋል። ዕድሜውን ሙሉ ሲከነክነው፡ ያንንም ለመሸፈን ወደ አላስፈላጊ ስህተት ከሚጓዝ ይልቅ ይቅር በሉኝ ባለ ጊዜ የምከራከርለት ወንድሙ አሉላ ነኝና ይመን፡ በማመኑና ይቅርታ በመጠየቁ የአህምሮ እረፍቱን ወደፊት ያገኘዋል።

ቸር ይግጠመን፡ አሉላ
የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 23, 2010)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 6

ውድ የኢሕአፓ (ዴ) አባላት፥

እስከ ዛሬ ድረስ ድርጅታዊ ተቋሞችንና ስነ-ሥርዐትን ለማክበር በማለት ከአመራር ካውንስሉ ለመሰናበት ያበቁኝን ምክንያቶች ያሰፈርኩበትን የስንብት ደብዳቤ የአመራር ካውንስሉ በጉባዔ ለመረጡኝ አባላት እንዳይደርስ ሲያፍነው በትዕግስት እየተመለከትኩ ቆይቻለሁ:: አግባብነት ባላቸው ድርጅታዊ መዋቅሮች አማካይነትም ስሞታዬን አቅርቤአለሁ:: ይህንንም ዝምታ ስመርጥ፥ እኔ በፈለግኩት መድረክ፥ መንገድና ሁኔታ ለአባላት ለመበተን እንደምችልና ይህንን ማድረግም ደግሞ ሙሉ መብቴ እንደሆነ እያወቅኩኝ ነው:: ካውንስሉ ግን ለማሰብ ካለመቻል ይሁን በማንአለብኝነት፥ ጉዳዩ በምንም መልኩ የማያገባውን የመብት ኮሚሽን እንደ መከለያና እንደ ማዘግያ ወይም ጊዜ መግዣ መሳሪያ በመጠቀም፥ ደብዳቤዬን ይኼው ለሁለት ወራት አግዶት ቆይቷል::ብዙ የሀሰት ወሬዎችም በኔ ላይ እንዲሰራጩ አድርጓል:: ይባስ ብሎም፥ አሁንም ይህኑ ደብዳቤዬን አግዶ፥ ዛሬ አባላት በየአህጉሮች ተከፋፍለው የድርጅታቸውን ችግሮች (አንዱ ችግር ከኔ ጋር የተያያዘው ሆኖ እያለ) በቴሌኮንፈራንስ የሚወያዩበትን ስብሰባ ጠርቷል::

በመሰረቱ፥ እኔ በካውንስሉ ውስጥ ሆኜ ስታገልለት የነበረው የአባላት የውይይት መድረክ ዛሬ መፈቀዱ ትልቅ እርምጃ ነው:: ነገር ግን፥ አሁን በተጠራው መልኩ የሚካሄደው የአባላት የቴሌኮንፈራንስ ስብሰባ ብዙ ጉድለቶች አሉበት::

1. አባላትን በተለያዩ አህጉራት ከፋፍሎ ቴሌኮንፈራንስ ማድረግ ለድርጅታዊ አንድነትና ችግሮችን ለመፍታት እንደማይጠቅም ለመገመት የሚያዳግተው አባል ይኖራል ብዬ አላስብም:: ይህ የአባላት መወያያ መድረክ በምን ዘዴ ወይም ዓይነት መሆን እንዳለበት እኔው ራሴ ከካውንስሉ ሳልሰናበት የታገልኩለት ስለሆነ ጉዳዩን በዝርዝር አውቃለሁ፥ አስፈላጊ ከሆነም መረጃ አቀርባለሁ:: ይህንን የአባላት መድረክ ጉዳይ እኔና አንድ ሌላ የካውንስል አባል ስንጠይቅ፥ ዛሬ ይህንን አህጉራዊ የአባላት ስብሰባ ለመጥራት የተገደደው ካውንሰል አላደርገውም ሲል ቆይቶ ነበር:: የተጠየቀውን የመላ አባላት መድረክ እንደመፍቀድ፥ በአንዳንድ ስንኩል ምክንያቶቸ በማሳበብ፥ "ችግር" ያለባቸውን አንዳንድ አባላትን ብቻ እየለዩ ማነጋገር በቂ ነው በማለት በተለመደው ቡድናዊ የድምጽ ብልጫው ወስኖ ነበር:: ይህ የቡድኑ አባላት ውሳኔና ተግባር መልካም ውጤት ሊኖረው እንደማይችልና ውድቅ እንደሚሆንም በተደጋጋሚ ለቡድኑ በይፋ በካውንስሉ ስብሰባ ላይ ሳሳስብ ነበር:: ቡድኑ ግን በትዕቢትና በክፋት በመረጠው መንገድ ቀጠለ:: "ችግር" አለባቸው ብሎ ለይቶ ያወጣቸውን አንዳንድ አባላት በሁለት ወይም በሶስት የካውንስል አባላት ከግራ ከቀኝ ሲያዋክብ ሰነበተ:: የእነኝህን አባላት ጊዜ በከንቱ አባከነ፥ የማያስፈልግ ጥላቻና ጥርጣሬ ፈጠረ:: በተደጋጋሚ እንደተነገረውም የቡድኑ የመከፋፈልና የማስፈራራት ሙከራውም ከሸፈ:: ይኼው ዛሬ ከሁሉም አቅጣጫ በአባላት ጥያቄ ሲወጠር አሁን ያወጀውን ስንኩል የቴሌኮነፈራንስ ስብሰባ ለመጥራት ወሰነ::

2. የተነሱት ችግሮች በየአህጉሩ የተወሰኑ ሳይሆኑ ጠቅላላ ድርጅቱን የሚመለከቱ ናቸው:: በድርጅቱ አካሄድ ላይ ችግር ያላቸው በአንድ አህጉር የተወሰኑ ሳይሆኑ በተለያዩ አህጉሮች ያሉ ናቸው:: ታዲያ፥ በየአህጉሩ አባላትን ከፋፍሎ በቴሌኮንፈራንስ ማነጋገርን ምን አመጣው? ቡድኑ የአባላትን በአንድ መድረክ መገናኘት የማይፈራ ካልሆነ ለምን ሁሉም አባላት በአንድ ጊዜ በአንድ ሰፊ አዳራሽ ተገናኝተው አንድ ዓይነት መረጃ፥ አንድ ዓይነት መልስ፥ አንድ ዓይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አይደረግም?

3. አሁን እንደ ምክንያት ሊቀርብ የሚችለው ሰበብ በአህጉሮች መሀል ያለው የሰዓት ልዩነት ነው:: ይህ ስንኩል ሰበብ ነው:: ቡድኑ ዓይኑን ካልጨፈነ በስተቀር ድርጅቱ

Footnote # 6

ትልቅ ቸግር ላይ ነው ያለው። እውነትም የሰዓት ልዩነት ችግር አለ ብለን ብንወስድም እንኳን (አይደለም እንጂ)፥ ይህንን ያህል የድርጅትን ኅልውና የሚያናጉ ችግሮች ተከስተው አበላት ድርጅታቸውን ለማዳን ሲሉ አንድ ቀን ቢተጓጎሉስ ምን ችግር አለ? አህጉርና ውቂያኖስ እያቋረጡ ስራ ትተው ብዙ ገንዘብ አፍስሰው ለጉባዔ ይመጡ የለ? አባላትን ለመከፋፈል ካልሆነ፥ የተወሰኑ አባላት ሰፊውን አባላት እንዳያገኙ ለማሰናከል ካልሆነ፥ የተወሰኑ የአመራር አባላትን ከተወሰኑ ጠያቂ አባላት ለመከላከል ካልሆነ፥ ይህ የሰዓት ልዩነት ሁሉም አባላት በአንድ ጊዜ በአንድ ጥላ ስር የማይገናኙበትና የማይወያዩበት ምክንያት ሊሆን አይችልም።

4. የታቀደው ቴሌኮንፈራንስ ፈጽሞ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ካሁን ቀደም በቴሌኮንፈራንስ የተሰበሰባችሁ በሙሉ ታውቁታላችሁ። ብዙ ቴክኒካል ችግሮች እንዳሉት መግለጽ አይኖርብኝም። በኔ ግምትና አስተያዬት ፓልቶክ የተመረጠ ይሆናል። ይህንንም ሀሳብ ካውንስሉ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ አቅርቤ ታግዬበታለሁ (ክፍያውንም ጭምር ለመቻል)። ነገር ግን፥ እንደሌሎቹ ሀሳቦቼ ሁሉ፥ ይህም ሀሳቤ በቡድኑ ተረግጦ ተዘግቷል። አሁንም ቢሆን፥ የተከፈለበትና ደኅንነቱ የተረጋገጠበት ክፍል ለማግኘት ይቻላል። ስብሰባውን በጊዜ ለመጀመር ከማስቻሉም በተጨማሪ ማንም ሰው የሚደረገውን ስብሰባ ሊቆጣጠረው፥ ሊጠመዝዘው፥ ወይም ሊያበላሸው አይችልም። ግልጽ ስብሰባ ይሆናል፤ ሁሉም አባላት በእውነተኛ ስማቸው ብቻ መግባት ይኖርባቸዋል (አሁን በአዲሱ የውይይት ፎረም ላይ እንደተጀመረው የመደበቂያ ስም ሳይሆን ማለቴ ነው)። በርካታ አባላት የሚሳተፉበት ቴሌኮንፈራንስ ችግር የሚፈጥር እንጂ አባላት ቀጥተኛና የተጣራ ስብሰባ የሚያካሄዱበት የመገናኛ ዘዴ አይደለም።

ውድ አባላት፥ ይህ የታቀደው ስብሰባ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚያስችለን ሳይሆን የበለጠ የሚያራርቅና ችግሮቹን የሚያበዛ ነው። ይህ የቡድን አመራር የአባላትን ስብሰባና መገናኘት በቀና መንፈስና መንገድ ማዘጋጀት የተሳነው ይመስለኛል። ቡድኑ በእምቢተኝነቱና አሁን ግልጽ ሆኖ በወጣው አምባገነንነቱ የሚገፋ ከሆነ ይህ ስብሰባ ለድርጅቱ መጥፎ ጠንቅ ሊሆንበት ይችላል። ሰሞኑን በውይይት ፎረሙ አስተዳዳሪ በኩል እየተደረገ ያለውን ህገ-ወጥና አምባገነናዊ እርምጃዎችን እየታዘባችሁ ያላችሁ ይመስለኛል። የተሰጠው የመተዳደሪያ ደንብ ራሱ ህገ-ወጥ ነው፤ ይህንንም ህግ ነው ብለን ብንቀበለውም እንኳን አስተዳዳሪው የጫነብንን ህግ ራሱ በአግባብ እየተጠቀመው አይደለም።ይህም ስልጣን ሆነና አስተዳዳሪው የተለየ ሀሳብ የሚያቀርቡትን ወይም ጥያቄ የሚያቀርቡ አባላትን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከባዱንና የመጨረሻውን እርምጃ ይወስዳል፤ ከመድረኩ እየመነጠረ ያባርራል (እንኳንም አሜሪካ ውስጥ ሆን ያሰኛል!)። ይህ ዓይነት እርምጃ፥ አብረን በነበርንበት ጊዜ፥ በለውጥ አጋቹ ቡድን እንኳን ተወስዶ አያውቅም። ዛሬ እኛ ጋ ያለው የቡድን አምባገነንነት የቱን ያህል የከፋ እንደሆነ ከዚህ የበለጠ መረጃ የሚያስፈልገንም አይመስለኝም። የዚህ የመድረኩ አስተዳዳሪ ይሁን የሚተባበረው ቡድን የድርጅቱ አባላት ለዚህ ድርጅት ምን ያህል እሴት እንደሆኑ በውል የተገነዘቡ አይመስለኝም። ይህንን ድርጅት ሁሉም አባላት በእኩልነት በገንዘባቸው፥ በጊዜአቸውና በጉልበታቸው የገነቡት እንደሆነ የሚረዱ አይመስለኝም፤ እንደ ግል ንብረታቸው የሚያዙበትና የሚናኙበት እቃ ይቆጥሯቸዋል።

እንግዲህ፥ ይህ የታቀደው ስብሰባ ችግሮችን ለመፍታትና የድርጅቱን አንድነት ጠብቆ ለመቀጠል የተፈለገ እርምጃ ከሆነ በስብሰባው አዘገጃጀትና አካሄድ ላይ ለውጥ የግድ ያስፈልጋል።

1. ህገ-ወጥና የአባላት መብት ማፈኛ መሳሪያ የሆነው የውይይት መድረኩ የመተዳደሪያ ደንብ አሁኑኑ መነሳት ይኖርበታል፤ ያለ አግባብና ህገ-ወጥ በሆነ

Footnote # 6

መንደግ ከመድረኩ የተባረሩት አባላት ከሙሉ የአባልነት መብታቸው ጋር በመድረኩም ሆነ በሁሉም የድርጅቱ ዘርፎች ለመሳተፍ መቻል ይኖርባቸዋል።

2. የመድረኩ አስተዳዳሪ ከዛሬው ጀምሮ ምንም ዓይነት የማባረር ወይም የማገድ እርምጃ ከመውሰድ መታቀብ ይኖርበታል።

3. የታቀደው የአባላት ስብሰባ ከላይ በተገለጠው መንገድ፥ ማለትም ሁሉም አባላት በሚገኙበት የፓልቶክ አዳራሽ፥ ሊደረግ ይገባል። ይህ የማይደረግ ከሆነ ቴሌኮንፈራንሱ የቡድኑ ስብሰባ ብቻ ይሆናል። ውስጠ-ፓርቲ ትግሉ የሚፈጠረው ሁኔታ በሚፈቅድው መልክ ይቀጥላል።

4. የታቀደው ስብስባ በተስተካከለ መልኩ የሚደረግ ከሆነ፥ አባላት ለስብሰባው ቅድመ-ዝግጅት ማድረግ ስለሚኖርባቸውና ለዚሁም ዝግጅት የሚረዱአቸውን መረጃዎች ከወዲሁ ማግኘት ጠቃሚ ስለሚሆንላቸው፥ እነሆ ካሁን ቀደም ለአባላት እንዳይደርስ ተከልክሎ የቆየውን የስንብት ደብዳቤዬንም እንደ አባሪ አያይዤዋለሁ።

መልካም እድል ለድርጅታችን!!!

ጌታቸው በጋሻው

***************************

**September 1, 2009**

**ለ ኢሕአፓ (ዴ) የአመራር ካውንስል፥ ለኢሕአፓ (ዴ) የአባላት መብትና ህግ አስከባሪ ኮሚሽን እና ለኢሕአፓ (ዴ) አባላት በሙሉ**

**ከጌታቸው በጋሻው**

**ጉዳዩ :- ከኢሕአፓ (ዴ) ካውንስል አባልነት ስለመሰናበት**

ከ5ኛው ጉባዔ በፊት በተደረገው የኢሕአፓ (ዴ) የአመራር ካውንስል 3ኛ ፕሌኔም ላይ ወንድሜ ሰለሞን ገ/ሥላሴ "ሲደርስበት ከነበረው በደል አኳያ ስታይ ወደ ኢሕአፓ መመለስ ከሚገባቸው ሰዎች ውስጥ ጌታቸው የመጨረሻው መሆን ነበረበት" ብሎ የተናገረውን የቀድሞው ካውንስል አባላት የነበራችሁ የምትዘነጉት አይመስለኝም። ድርጅቱ ውስጥ ሆኜ፥ እኔ በደል ደርሶብኛል ብዬ፥ አንድም ጊዜ በተመድብኩባቸው የስራና የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሰንፌ ወይም ለግሜ አላውቅም። አቶ ኢያሱ ዓለማዬሁ ኑሮው ሳደረገው የሀሰትና የክፋት ፖለቲካው ይጠቅመኛል ብሎ "በታኝ" ነው የሚለውን ታርጋ ለጠፈብኝ እንጂ የያኔው አመራሮች በነበራቸው ውስጣዊ የስልጣን ሽኩቻና የአመራር ጉድለት ((የዘሩ ክሸን፥ የአብዲሳ አያና (ሮባ)፥ የገብሩ መርሻ (ጋዙ)፥ የዳዊት ሰዩም እና የመህሪ ተስፋዬ (የማን ወይም ጌዲዮን) ተከታትሎ መሰናበት)) ሳቢያ የተፈጠሩት ውስጣዊ ችግሮች ድርጅቱንና ሰራዊቱን እንዳያፈራርሱና እንዳይበትኑ ለመከላከል ከተመደቡት ሌሎች የማክብራቸውና ዛሬም ለምስክርነት በህይወት ካሉ የልዑካን ቡድን አባላት (አምበርብር፥ ፀሀይ፥ ዳንኤል፥ ክፍሉ) ጋር በመሆን ከሚጠበቅብኝ በላይ ጥሬያለሁ። ከዚያም በማለፍ፥ የሪጅን 2 ሰራዊት በሁኔታዎች ተገዶ ወደ ሱዳን ግዛት ሲገባ፥ ሁሉም የአመራርና የልዑክ አባላት ወደ ገዳሪፍ ከተማ ሲያመሩ፥ እኔም እንደነርሱ ወደ ገዳሪፍ ለመሄድ ስችል፥ ነገር ግን ከመላው አባላት

Footnote # 6

ጋር አምራኩባ የስደተኞች ካምፕ ውስጥ በመቅረት÷ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ቢሮ የሚሰፈርልንን ዱቄት ዘይትና ጨው እየበላሁ ከአባላት ጋር እየኖርኩ በአባላቱና በአመራሩ መሀል አገናኝ ሆኜ ሳገለግል የቆየሁት እኔ ብቻ ነበርኩኝ፡፡ በወቅቱ የድርጅቱን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ይቆጣጠር የነበረው አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ በነበረው ስልጣን በየካምፑና በየመጠለያዎቹ (Shelters) ለሚኖሩት የድርጅቱ አባላት ምንም የገንዘብ ወጪ እንዳይደረግ ሲወስንና አባላት ተበትነው የየራሳቸውን ጉሮሮ የሚመግቡበትን መንገድ እንዲፈልጉ ሲደረግና ሲበተኑ÷ እኔም እንደ ሌሎቹ ሁሉ እየከፋኝ ድርጅቱን ለቀቅኩ፡፡ ድርጅቱንም ለቅቄ የራሴን ኑሮ መኖር ከጀመርኩ በኋላም÷ እኔ በጠላትነት ቆሜ በድርጅቱ ላይ የወረወርኩት አንድም ጠጠር ያለመኖሩን የሚያውቀው ኅሊናዬ ብቻ ሳይሆን መላው የድርጅቱ አባላት ጭምር ናቸው፡፡ እንዲያውም÷ ድርጅቱ ራሱን ከሌሎች ጠላቶቹ ለመከላከል ባልቻለባቸው ወቅቶች÷ በርከት ላሉ ጊዜያትና በርከት ባሉ አጋጣሚዎች ላይ የድርጅቱን ታሪክና የውድ አባለቱን መስዋዕትነት÷ ገድልና ለአገር ታማኝነት ከመከላከል አልቦዘንኩም ነበር፡፡ ስለዚህ÷ በቀድሞ ታሪካችን ጉዳይ ላይ ኅሊናዬ በጣም ንጹህ ነው፡፡ በታኞች በወቅቱ የነበሩት የያኔዎቹ መሪዎች እንጂ እኔ አልነበርኩም፡፡

አሁን ደግሞ ድርጅቱ ተጎድቷል÷ ማድረግ ያለበትን ለማድረግ አልቻለም÷ ከታሪካዊ ቦታው ላይ ወደ ጠርዝ እየተገፋና ከሕዝቡ እየራቀ  ነው÷ ትግሉ አቅጣጫውን እየሳተ ነው÷ ውድ ጓዶቻችን ከፍተኛውን መስዋዕትነት የከፈሉበት ድርጅት ትግልና ዓላማ መና እየቀረ ነው÷ ስለዚህ ወደዚህ ድርጅት ተመልሰህ በአመራር ማገልገል አለብህ ብላችሁ÷ አሁን ዛሬ በዚሁ የአመራር ካውንስል ውስጥ ያላችሁ÷ ከፍላጎቴ ውጭ ጫና አድርጋችሁብኝ÷ ለራሴ ለረጅም ጊዜ የገባሁትን ቃል አጥፌ÷ እየከበደኝ እየቀፈፈኝና እየጨነቀኝ÷ ቃላችሁንና ፍላጎታችሁን አክብሬ÷ ለሁለተኛ የድርጅት ትግል ዙር እራሴን አቀረብኩ በ4ኛው ጉባዔ ጊዜ፡፡ ሌሎች እኔን መሰል ጓደኞቼና ጠቃሚ የሆኑ የቀድሞ አባላት÷ ወደዚህ ድርጅት ሊመለሱና በአመራር ሊያገለግሉ ቀርቶ÷ እንደነበሩ እንኳን እንዲታወቅባቸው በማይፈልጉበት ወቅት ነው ይህንን ኃላፊነት የተቀበልኩት፡፡

በ4ኛው ጉባዔም ከተመረጥኩ በኋላ በሙሉ ልቤ ድርጅቱን ማገልገል ጀመርኩ፡፡ ድርጅቱ በከፍተኛ ውሰጣዊ ችግር ተተብትቦ እንዳለ ኃላፊነቱን በተቀበልኩ በበነጋው ተገነዘብኩ፡፡ እንዲሻሻል የበኩሌን ጣርኩ፡፡ ይህ በኔ ጥረት ብቻ የማይሻሻል ችግር መሆኑን ስረዳ የከአኮ ሁለተኛ ፕሌኔም በፍጥነት እንዲጠራ ገፋሁ÷ ተማጸንኩ፡፡ ፕሌኔሙ ተደረገ÷ ድርጅቱን ጠርንቀው የያዙ የሁለቱ ነባር መሪዎች (የአቶ መርሻ ዮሴፍና የአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ) ቅራኔዎችና ጥላቻዎች ለጊዜው መፍትሄ ያገኙ መስለውኝ ነበር፡፡ በደስታ ፍንድቄ እንደ ህፃን ልጅ እዚያው የፕሌኔሙ ስብሰባ ላይ የደስታ ልቅሶዬን አነባሁ፡፡ ብዙ ላይቆይ ሁለቱንም መሪዎች እዚያው ስብስባ ላይ “የማከብራችሁ ጨዋዎች ናችሁ” ብዬ አሞገስኳቸው፡፡  በጥሩ መንፈስ÷ በአዲስ ጉልበት÷ በብሩኅ ተሰፋ ተመልሼ መስራት ጀመርኩ፡፡ በተለያዩ ጥቂት ከተማዎች ተዘዋውሬ ጓዶችን አዬሁ÷ ለመታዘብ የቻልኳቸውን ነገሮች በሙሉ አዬሁ÷ ለጓዶች እንደሚዋሽ ተረዳሁ፡፡ ጓዶች በማይጨበጥ ተስፋ ብቻ ተታልለው÷ የግል ህይወታቸውን ረስተው÷ ለጥቂት የድርጅት መሪዎች ምቾትና ኑሮ ብቻ እንዲገብሩ መደረጋቸውን በዓይኔ አዬሁ÷ በኅሊናዬ ታዘብኩ÷ በጣም ተጨነቅኩ፡፡ ፕሌኔሙም ተደርጎ÷ የየራስን ቡድናዊ ግንኙነቶችን ከማጠናከርና ከማስፋት በስተቀር ምንም ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ስራ በአብዛኛው የድርጅቱ አመራር አባላት እንደማይሰራ ዳግም ተገነዘብኩ፡፡ ብዙ የጓዶች ገንዘብ (የኔም ጭምር) የባከነበት ፕሌኔም ዋጋ ቢስ እንደነበረ በግልጽ አየሁት፡፡ በዚህ ሁኔታ ለመቀጠል አልተቻለኝም÷ ጭንቀቴን የምትገልጥ አንዲት አጭር ደብዳቤ (በባለ 31 ገጹ የልዩነት ሰነዳችን ውስጥ እንደ አባሪ ቁጥር 1 የቀረበችውን) ለከአኮ ጻፍኩ÷ ኳስ አበደች ከዚያ በኋላ፡፡ የተረፈውን ታሪክ እናንተው ጨርሱት፡፡ ነገር ግን÷ ከወዲሁ እንዲታወቅልኝ የምፈልገው አንድ ቁም ነገር አለ፡፡ እኔ ይህችን ደብዳቤ የጻፍኩት ከማንም ጋር ተማክሬ÷ ማንንም ለይቼ ለመጉዳት ወይም ማንንም ለይቼ ለመጥቀም ሳይሆን  የጻፍኩት በራሴ ኅሊና የራሴን ጭንቀት ከመላው የከአኮ አባላት

Footnote # 6

ጋር ተጋርቼ፥ የጋራ መፍትሄ ለመሻትና ድርጅታችንን (ኢሕአፓን) ወደፊት ለማራመድ ብቻ ነበረ።

ለጥቆም ኢሕአፓ (ዴ) ተመሰረተ፥ አዲስ ራዕይ፥ አዲስ አሰራር፥ አዲስ ግንኙነት እውን ይሆናል ተባለ። ዴሞክራሲና ለውጥ የኢሕአፓ (ዴ) መሰረታዊ እምነቶችና መሪ ዓላማዎች ናቸው ተብሎ ቃል ተገባ። እኔም አመንኩ፥ ራሴንም ሰጠሁ። ምስጋና ይሰጣቸውና፥ በተለይም VEDRና የግንባር ኮሚቴ፥ ኢሕአፓ (ዴ)ን በዚህ መልኩ ለሕዝቡና ለድርጅቶች ሁሉ ለመሸጥ ጣሩ። ከንቱ አልነበረም ጥረታቸው። በአጭር ጊዜ ውስጥ የስንት ዓመቱን ጉድፍ አራግፈው፥ ኢሕአፓ (ዴ)ን እንደ አዲሰ ሙሽራ አቅርቦ በሕዝብና በድርጅቶች እንዲወደድና እንዲከበር ለማድረግ ችለዋል። ኢሕአፓ (ዴ)ን ለማሳደግና በትግሉ ውስጥ የሚለካ ሚና ለመጫወት እንዲችል ለማድረግ ልዩ እድል ፈጥረዋል። ይህ አሌ ከተባለ ወደፊት ልመለስበት።

እንግዲህ፥ እውነት ለውጥ ተደርጓል? እውነት ዴሞክራሲያዊ ተኩኗል? ምንም እንኳን አሮጌ ውሻን አዲስ ብልሀት ማስተማር አይቻልም የሚለው የፈረንጆች አባባል እውነት ቢሆንም፥ ብዙ ድሰኩሮቻችንና ጽሁፎቻችንን በመከተል፥ አዎ ለለውጥና ለዴሞክራሲ ተዘጋጅተናል ብዬ ለተወሰነ ጊዜ አምኜ ነበር። በውል ባማላውቃቸውና እንዲሁ በግምት ብቻ ምክንያት እየሰጠኋቸው ለማልፋቸው የግንባር ኮሚቴን አስታክከው ለሚነሱ ከአንዳንድ ደካማ ክርክሮች በስተቀር የኢሕአፓ (ዴ) አመራር ለለውጥ ያልተዘጋጀና ዴሞክራሲያዊ ለመሆን የማይችል ነው የሚያስብሉኝ ነገሮች አልነበሩም። ነገርግን፥ ጉድና ጅራት ከወደኋላ ነው እንደሚባለው ነገሮች የመቱኝ በVEDRና በአስተዳዳሪዎቹ ላይ ሲዘመት ነው። ጊዜው ደግሞ እጅግ የሚደንቅ ነው። VEDR ብዙ ብዙ መልካም ውጤቶችን እያስመዘገበና ጥራት ያላቸው የፖለቲካ ርዕሶች መጠቅ ባሉ ደረጃዎች ሲተነተኑ፥ በርካታ ምሁራንና አንቱ የሚባሉ የፖለቲካ መሪዎች ቀርበው ሲወያዩ፥ ታዳሚዎች አጀብ VEDR ብለው ሲያደንቁ ነበር አሰናካይና ተስፋ አስቆራጭ ጭቅጭቆችና ቅስቅሳዎች (ለምን ሌላ VEDR አይከፈትም እስከ ማለት ድረስ) ብቅ ያሉት። ይህ ምንም ሚስጢራዊነት የለውም፥ በዚህ መንገድ የተጓዘው ቡድን VEDRን ለመቆጣጠር ከመፈለጉ በስተቀር። ይህ እስከ ዛሬ ድረስ አላቆመም። በራሳቸው አነሳሽነት ጀምረው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እየበደሉ ለድርጅቱ የተዋጉትን ታማኝ የድርጅቱን አገልጋዮችን በዚያ መልክ ማብጠልጠልና ጥላሸት ቀብቶ በሌሎቹ የድርጅቱ አባላት ለማስጠላት መቀስቀስ ከኢ-ዴሞክራሲያዊነትም ባሻገር ነው። ይህ ነው እንግዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእንቅልፌ ያባነነኝ፥ ከሙሉ እምነቴም ላይ የገፈተረኝ።

ከዚህ በኋላ፥ ትልቁ ቲያትር አምስተኛው ጉባኤ ተብዬው ነው። ለዚህ ውድቅ ጉባኤ ምን ያህል በቀና አባላት በኩል እንደተለፋ አውቃለሁ፥ በተለይም በቺካጎ ጓዶች። ምን ያህል ተስፋም እንደነበረ እገምታለሁ። ከአብዛኛው የአመራር አባላት አንስቶ በገንዘብ፥ በጽሁፍና በጊዜ ብዙ ተከፍሎበታል፥ ተለፍቶበታል። ነገር ግን፥ በሚያሳዝን ደረጃ፥ ከአዘገጃጀቱ አንስቶ እስከ አፈጻጸሙ ድረስ የሚያሳፍርና የሚያስጠረጥር ነበር። ባልተጨበጠና አግባብነት በየሌለው አቀራረብ የአንድ አመራር አባልን (በየነ ጉራ) ሞራልና ስሜት በመስበር ገፍቶ ያስወጣ ፕሌኔም ያካሄደ፥ ምንም የረባ ድርጅታዊ ፖለቲካዊና የፖሊሲ ውሳኔ ያላሳለፈ (ካለ ትግል ስልት በስተቀር)፥ ምንም ተቀባይነትን ሊያገኝ በማይገባው የፌዝ ምርጫ (ምርጫ ተብሎም መጠራት የለበትም ብዬ አምናለሁ) የሀሳብ diversity ሊኖር እንዳይችል የሚያደርግና በአንድ ግለሰብ ዙሪያ የተማከለ የአመራር ካውንስል እንዲመሰረት ያደረገ አሳፋሪ ጉባዔ ነበር። ትልቅ ኪሳራ፥ ትልቅ ውድቀት።

ይህ ሁሉ ዝም ብሎ በአጋጣሚነት ጉባዔው ላይ የተከሰተ ነገር ሳይሆን አቶ መርሻ ዮሴፍ ያለምንም አስፈላጊ ጉዳይ ከጉባዔው በፊት ቀደምና ረዘም አድርጎ ወደዚህ ወደ አሜሪካ በመዝለቅና ወደ ተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች በመዘዋወር ያዘጋጀው ድርጊት ነው ብዬ

Footnote # 6

አምናለሁ። እውነት የአቶ መርሻ ተገባር ድርጅትን ማጠናከርና አባላትን ማሰባሰብ ቢሆን ኖሮ እዚህ በማያስፈልግበት አገር ጊዜና ገንዘብ ከማጥፋት በተራቆትንበትና እርሱ በሚኖርበት ክፍለ ዓለም የለውጥ አጋቹ ቡድን ባዶአችንን ባላስቀረን ነበር። ጉዳዩና ጥቅሙ ሌላ ሆኖ ነው እንጂ እዚህ (ለዚያውም ጓዶች ባልፈለጉት ቦታዎች ጭምር) ባለተዘዋወረና የማያስፈልጉ ጥርጣሬዎችንም ባለቀሰቀሰ። አቶ መርሻና ደጋፊዎቹ ይህንን የሚያደርጉበት የራሳቸው ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን፥ ይህ በማያጠራጥር መንገድ ድርጅቱን ክፉኛ የሚጎዳና የጎዳም ነው። ለምን?

በመጀመሪያ፥ ከአነሳሳችን ድርጅታችን የለውጥ ድርጅት ነው ብለን ነበር። ነገር ግን፥ ብዙዎቻችን፥ በተለይም አቶ መርሻ፥ የለውጥ አርአያ ልንሆን አንችልም። አቶ መርሻ ድርጅቱ፥ ኢሕአፓ፥ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ የአመራርነት ቦታዎች ላይ የቆዩና ከድርጅቱ ውድቀቶችም ጋር ከሚያያዙ ብዙ ነገሮች ጋር የተቆራኙ ስለሆነ  አቶ ኢያሱ ዓላማዬሁን እያወገዙ አቶ መርሻ ዮሴፍን ማንገስ፥ ለግለሰብ እንጂ ለድርጅትና ለትግል ግድ የለንም የምንል ካልሆን በስተቀር፥ የሞኝ ፖለቲካ ይሆናል። በጥቅሉ፥ የአቶ መርሻ በአመራርነት መቆዬት ለድርጅታችን፥ ኢሕአፓ (ዴ)፥ ጎጂ እንጂ አንዳችም ጥቅም የለውም። አቶ መርሻ ይኖረዋል ስለሚባሉት ልዩ እውቀቶችና ችሎታዎች ደግሞ የድርጅቱ አባል ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ በሚዘጋጁለት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊያበረክት ይችላል፥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ። ይህም ለአባላት በሚገባ እስከተገለጠ ድረስ ለመቀበል የሚያዳግታቸው ይኖራሉ ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። ለራሱም ደግሞ በገዛ ፈቃዱ ከአመራርነት ወረደ መባሉ ለታሪኩም ይበጅ ነበር። ለነገሩ፥ አቶ መርሻ በየጉባዔዎቹ እወርዳለሁ እያለ ሲናገርና ሲለመን ስንት ጊዜ ሆኗል? ከዚህም በላይ እኔና ሰለሞን ገብረ ስላሴስ እንዲወርድ ነግረነውስ አልነበረም? ከኔ ጋር ደግሞ፥ እኔ ከሁለተኛው ፕሌኔማችን ጀምሮ ለመቀጠል አለመፈለጌንና ኋላም ሰለሞን ባመጣው የሶስታችን መውረድ ላይ ስለመስማማቴ ስንከራከር በአቶ መርሻ የመውረድ አስፈላጊነት ላይ እኔና እርሱ ተስማመተንስ አልነበረም? ታዲያ ምነው ነገሮች በሙሉ በጉባዔ ላይ ተቀየሩ? ከቶውን አይገባኝም፥ አቶ መርሻ የአመራርነት ቦታውን ለመልቀቅ ፈጽሞ አይፈልግም ከማለት ሌላ። ለድርጅት እድገት የሚያስብ፥ ለትግሉ መጠናከር የሚጨነቅ፥ ለአገርና ሕዝብ የሚቆጭ መሪ፥ በሉ እኔ በሚመስለኝ እስካሁን ሞክሬ አልሆነልኝም፥ አልቻልኩም፥ እስቲ አዳዲስ መሪዎች፥ አዳዲስ ሀሳብ ያላችሁ፥ አዳዲስ አሰራር አመለካከትና ግንኙነት ለማፍለቅ የምትችሉ ተረከቡኝና ድርጅቱን አስቀጥሉ፥ ትግሉን ምሩ ብሎ በፀጋና በክብር አባላትን አመስግኖና መርቆ ቦታ ይለቃል እንጂ የሙጥኝ ብሎ አይቆይም። ይባስ ተብሎም፥ በርሱ እንደገና ኃላፊነት ላይ መመለስ ችግር እንደተፈጠረ እየታወቀ፥ የኢሕአፓ (ዴ) ገጽታና ፊት ሆኖ በሕዝብ እንዲታይ መደረጉ፥ የንቀት ንቀትና ለድርጅት ግደለሽነት ነው። ከዚህ ሁሉ የአቶ መርሻና ደጋፊዎቹ እርምጃ ያተረፍነው ነገር ቢኖር ኢሕአፓ (ዴ) የአቶ መርሻ ድርጅት መባሉን ብቻ ነው -- ኢሕአፓ የአቶ ኢያሱ፥ ኢሕአፓ (ዴ) የአቶ መርሻ። ጥረታችን፥ ዓላማችንና የእስካሁን ትግላችን በአቶ መርሻና በአቶ ኢያሱ የስልጣን ሽኩቻና ሽሚያ ብቻ ተጠቅልሎ መታዬቱ እጅግ ያሳዝናል። የሌሎቻችሁን አውቃለሁ ለማለት ባልደፍርም፥ እኔ የተሰለፍኩትና የታገልኩት ፈጽሞ ለዚህ አልነበረም። አቶ መርሻ፥ በኔ ግምት፥ ድርጅቱን ጎድቷል፥ ራሱንም ማስከበር አቅቶታል።

ሁለተኛ፥ አቶ መርሻና ደጋፊዎቹ ፈጽሞ ዴሞክራሲያዊ አይደሉም፥ ለአፋቸው ይሉታል እንጂ። ከነርሱ የተለየ ሀሳብ ያላቸውንና የተለየ አሰራር የሚሹትን በሙሉ ያጠቁራሉ፥ የስብዕና ድምስሳ ፖለቲካ ይጫወታሉ። በVEDRና በበየነ ጉራ ጉዳዮች ላይ ታዝቤአቸዋለሁ። ከዚህም አልፈው በቡድን ይንቀሳቀሳሉ፥ ሌላውን ከመስመር ውጭ ሄዶ ቀሰቀሰ በማለት ቀድመው ይከሳሉ፥ እነርሱ በሰበብ አስባቡ ለሁሉም አባላት ያልተወሰነና ያልተገደበ ግንኙነት ኖሮአቸውና ያለተቆጠበ ቅስቀሳ በግለሰብ አባለት እያካሄዱ። ሲያመቻቸው የድርጅታዊ አሰራር መርሆዎችን፥ ሲጠቅማቸው ደግሞ የተሰው አባላትን ስምና መስዋዕትነትን እያነሱ ሀሳብ ለማፈን ይሞክራሉ፥ በስሜት ለመጫወት ይጥራሉ። አሁን በቅርቡ በታየው የየንባ-ባምቢስ ጉዳይ ላይ እንኳን እየተደረገ ያለውን የመሸፋፈን

Footnote # 6

ጥረት እየደገፉ የሚጽፉትንና ሌሎችን የሚሰድቡትን ምንም አለማለት፥ በጉዳዩ እውነተኝነት ላይ አምነው የሚጽፉትን ደግሞ በድርጅት አፍራሽነት መኮነንና ውይይትን ለማገድ መጣር በግልጽ ይታያል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ፥ ኃይለስላሴ የሚባለው አባል በአቶ መርሻ ላይ ያቀረባቸው የዘረኝነት ክሶች እውነት ይሁኑ አይሁኑ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሲነጋገርና ውሳኔ ለመስጠት ሲፈልግ፥ አቶ መርሻ እራሱን ከውይይቱና ከፍርዱ እንደ ማግለል በአባሉ ላይ አፋጣኝ ውሳኔ እንዲበየንበት ሲገፋ ቆይቷል። ለዚያውም፥ ይህንን ጉዳይ ለመመልከት ካውንስሉም ሆነ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው እምነት ይጎድለዋል፥ ኮሚሽኑ ጉዳዩን እኔ እይዤዋለሁ ብሎ አውጀ፥ እናንተ እጃችሁን ከዚህ አውጡ እየተባለ እየተነገራቸው። አሰራሩም አካሄዱም ፈጽሞ ትክክል ያልሆነና ፍትኅን ያጓደለ ነበር። ለአገርና ለሕዝብ እታገላለሁ የሚል ድርጅት በቅድሚያ እራሱን ማጥራት ይኖርበታል፥ የአባላቱን መብት ማክበር ይጠበቅበታል። ከዚህ አንጻር ስመለከተው፥ የአሁኑ የኢሕአፓ (ዴ) ካውንስል ብዙ ይጎድለዋል፥ ጠንካራ ቡድናዊ ጫናና ይሉኝታ ቀይዶ ይዞታል፥ የድርጅቱ መጫጫትና መክሰም አይጨንቀውም።

ድርጅታችን ኢሕአፓ (ዴ) እንደተባለውና እንደተገመተው የለውጥና የዴሞክራሲ ድርጅት አይደለም፥ የለውጡ እንቅስቃሴ ተኮላሽቷል፥ በኔ አስተያዬት ዓላማውም በግለሰብና በቡድን ጥቅምና ምኞት ተለውጧል። እኔ በዚህ ለውጥንና ዴሞክራሲን በማይቀበል የቡድን ካውንስል ውስጥ ለመሳተፍ አልችልም፥ ኅሊናዬም አይፈቅድልኝም። ስለዚህ፥ ይህንን ደብዳቤ ካስገባሁበት እለት፥ከ Spetember 1, 2009፥ ጀምሮ ከካውንስል አባልነቴ በራሴ ውሳኔ መሰናበቴን፥ ነገር ግን በድርጅቱ አባልነቴ የምቀጥል መሆኔን አሳውቃለሁ።

ውድ የኢሕአፓ (ዴ) አባላት ሆይ:-

በ4ኛው፥ በልዩውና በ5ኛው ጉባዔዎች ለድርጅታችን ጠቃሚ ስራዎችን ሊሰራ ይችላል ብላችሁ ለኢሕአፓ ከአኮና ለኢሕአፓ (ዴ) የአመራር ካውንስል ደጋግማችሁ ስለመረጣችሁኝ ምስጋናዬን ከከፍተኛ አክብሮት ጋር እገልጣለሁ። እኔም እስከ ዛሬ ድረስ እሰራቸዋለሁ ብዬ በተሰማራሁባቸው የስራ ድርሻዎቼ አመርቂ አስተዋጽዖዎችን እንዳበረከትኩኝ ይሰማኛል፥ በሰራኋቸው ስራዎች እምነታችሁን እንዳላጓደልኩ ልቦናዬ ያውቀዋል፥ በወከልኳችሁ ቦታዎች ሁሉ እንዳላሳፈርኳችሁ መንፈሴ ይነግረኛል። ሆኖም ግን:-

- ዛሬ ሕዝባችን እንደቅጠል እየረገፈ ባለበትና ትግላችን ወያኔን ማስጨነቅ በሆነበት ሰዓት
- አገራችን እንደማንኛውም የፍጆት ሸቀጥ ስትቸበቸብ ከሕዝባችን ጎን መገኘት በሚጠበቀብን ወቅት
- የተቃዋሚ ኃይሎች ለመሰባሰብና ለመተባበር ተዘጋጅተው እየመጡ ባለበትና ድርጅታችን ኢሕአፓ (ዴ) ከፍተኛውን ሚና እንዲጫወት ሲጠበቅ
- ኢሕአፓ (ዴ)፥ በብዙ ድካምና ልፋት ባለፉት 18 ወራት ውስጥ የተገኙለትን የሕዝብና የድርጅቶች ፍቅርና ክብር በመጠቀም፥ ታሪካዊ ቦታውን ለመያዝና የትግሉ እምብርት ሆኖ ለመውጣት እድሉን ሲያገኝ

አብዛኛው የኢሕአፓ (ዴ) አመራር ካውንስል አባላት ግን ሀገራዊና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን ረስተውና ወደ ጎን ትተው፥ ለውጥንና ተሀድሶን ለሕዘቡና ለትግሉ ከማብሰር ይልቅ አንድን ግለሰብ ለማንገስና ድርጅቱን በዚህ አንድ ግለሰብ መዳፍ ስር ለማስቀመጥ ይጥራሉ፥ ውሰኔዎችን በአንድ ጎንዮሽ የቡድን ፍላጎት ላይ ይመሰርታሉ፥ ሌላም። ስለዚህ፥ በዚህ እንደገና በመረጣችሁኝ ካውንስል ውስጥ በመሆን በሙሉ እምነትና በመግባባት ላገለግል አለመቻሌን ተረድቻለሁ። ብዙ ጉዳቶች በድርጅቱ ላይ ሳይከተሉ፥ የከረረ የጥላቻ ፖለቲካ

Footnote # 6

ሳይነግስና ወደ አልባሌ እኩይ የፖለቲካ ተግባሮች ሳንወርድ ይህንን የሰጣችሁኝን ኃላፊነት እነሆ መልሼ ለናንተው በታማኝነት አስረክባለሁ። አመሰግናለሁ።

መጥኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!

ግልባጭ:- ለኢሕአፓ (ዴ) የአባላት መብትና ህግ አስከባሪ ኮሚሽን
ለኢሕአፓ (ዴ) አባላት በሙሉ

Footnote # 7 a

የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 23, 2010)
ለ፡ <u>ኢ.ሕአፓ ዴ አመራር ምክር ቤት አባላት በሞላ</u>

የተከበራችሁ የኢ.ሕአፓ ዴ አመራር ምክር ቤት አባላት በመላ የከበረ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ።

ጥር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 06, 2010) በተጻፈ መልዕክቴ ከኢ.ሕአፓ ዴ አባልነት መልቀቄን ለመላ አባላት ማሳወቄ ይታወሳል። እንደ እምነት የያዝኩት ድርጅቴን ኢ.ሕአፓን ለመልቀቅ የተገደድኩበትን ሁኔታዎች እንድታውቁ ወደድሁ።

ውድ የአመራር አባላት፡ በእኔ አመለካከት የጠበኩትን ያህል አመርቂና የሚጠበቅበትን ተወቷል ባልልም ኢ.ሕአፓ ዴ 5ኛ ጉባኤውን አካሂዷል። እቀበላለሁ። የአመራር አባላት አመራረጥ አስመልክቶ ከጉባኤ በፊትም ከጉባኤ ማግስትም በቀደምት መልዕክቴ ያስነበብኩትን ለታሪክ ባስረክበውም፡ በተሳሳተና በጥቂቶች የተቀነባበረ መንገድ ቢሆንም ጉባኤው እስከቀጣይ ጉባኤ በአመራርነት የመረጠውን አካል የምቀበልና የማከብር ነኝ። ከአምስተኛው የፓርቲያችን ጉባኤ ወዲህ እየጎላ የመጣው ውስጣዊ ችግራችንን ደንብና ሥርዓትን በተከተለ መልኩ መለያችን በሆነው ውይይት እንፈታ ዘንድ አምንበታለሁ። የኢ.ሕአፓ ዴ ውስጣዊ ችግር ኢ.ሕአፓ ከተከፈለ ጊዜ ጀምሮ ያለ ነው። ፓርቲው ተከፍሎ ኢ.ሕአፓ ዴ ካልን በኋላ የተከፈለበትን ምክንያት በወጉ በመዳሰስና ቀጣዩ ሂደታችንን ከቀድሞ አሠራር በተጨባጭ የተለየ ለመሆኑ አመርቂ እንቅስቃሴ አላደረግንበትም። መሠረታዊ የፓርቲውን ጉዳዮችና ችግሮች ልንመረምርና ልንታደስ በሁለንተናዊነት አለመዘጋጀታችን ብዙም ሳንጓዝ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ ተዘፈቅን።

ከዚህ በፊት የማነሳቸውና የጻፍኩባቸው ጉዳዮች ላይ ሳልገባ ወደ ዋናው መልዕክቴ እነሆ፡

በጁላይ ኮንፈረንስ በአዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ ሰ.አ.ን ወክዬ እሠራ ዘንድ ሁሉም የሰ.አ. አህጉራዊ ኮሚቴ አባላት ጥቆማውን በማጽደቅ ተመርጬ ከአዘጋጅ ኮሚቴው የካውንስል አባልም (አቶ ተሾመ) በደረሰኝ መልዕክት መሠረት ለመገናኘት ምላሽ በሰጠሁ ማግስት ለምን ከኢ.ሕአፓ ዴ ለቀቅሁ? ድርጅቴን ኢ.ሕአፓን የፈለገውን ችግር ተጋፍጬ ከጠንካራ አባላቱ ጋር ይስተካከላል ብዬ የነበረኝ ተስፋ እንዴት ተሟጠጠ? በራሴ ላይ የሚደረገው ተራ ዘመቻ አይፈታኝም። ከአትላንታ አገናኝነት ለማንሳት የሚደረገው ቅድመ ዝግጅት አያስደንቀኝም። ሰብእናን የሚነካ ተራ ስድብና ብልግና ግን በነማን እየተመራን እንደሆነ ጠቁሞኛል። ከአባላትም ሆነ ከአመራር አባላት በሥራም ጉዳይ ይሁን በአንዳንድ ጉዳዮች ስንነጋገር አለመግባባት፡ መጯጯህ ቢኖርም ማንም ማንን ዝቅ አያደርግም። በተለይ በአመራር ላይ ያላችሁ ለዚህ አርሀያ መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ቢያደርጉም ኃላፊነት አለባችሁ። ለምን ቢባል የኢ.ሕአፓዊነት ስነ ምግባር የማስጠበቅና የማስከበር ኃላፊነት አለባችሁና። እኔ እስከማውቀው እንኳን የኢ.ሕአፓ አባላት በኢ.ሕአፓ ውስጥ ያለፉ ሁላ በባህሪያቸው፡ ከኅብረተሰቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት፡ በተለያየ የሶሻል ኮሚቴዎች ውስጥ እራሳቸውን ሳያሳውቁ ተከብረውና አክብረው የሚንቀሳቀሱና የሚያንቀሳቅሱ ናቸው። ይህ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 7 a

በጉርምስና ዘመናቸው ፓርቲው የቀረጸባቸውን ሥነ ምግባርና ትህትና ዛሬም ሲያንጸባርቁ ይታያል።

ቅዳሜ ጥር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ቀን ላይ ከአቶ መስፍን ተፈራ ጋር በተደረገ ንግግር የማልጠብቀው የመደምደሚያ ስድብ እጅጉን ምን ላይ ነው ያለነው አሰኝቶኛል። በመጀመሪያ ደረጃ እንደ አመራር አባልነቱ ምንም ይባል፡ ያውም አልተባለም ከሱ አልጠበኩም። ስጠራው እንኳ መስፍኔ ብዬ የማከብረውና የምወደው ወንድሜ ነው። በፈለገው ጊዜና ሰዓት ያዘዘኝን በሚፈልገው ጊዜና ሰዓት የማደርስለት አክባሪው ነኝ። የተነጋገርነው የሬዲዮ ዝግጅት አስመልክቶ ነው። በዚህ ጉዳይ በየትኛውም ኮሚቴ የለሁበትም። ግና መስፍን የሬዲዮ አንባቢ ችግር ስላለበት በላከልኝ ቁጥር ያለምንም እርማት አስተካክዬ በቀጥታ ለአየር የሚውለውን የመጨረሻውን ክፍል MP3 Format እልክለታለሁ። ይህ የትብብር ሥራ በአብዛኛው ቅዳሜ ለሚቀርብ (የኅብረት ሬዲዮ) አንዳንዴ አርብ ምሽት ላይ ሁላ ሲላክልኝ ሥራ ነውና አንግቼበት በተባለው ሰዓት አደርሳለሁ። ከመስፍን ጋር ያለን ግንኙነት ይህ ነው። ከመስፍን "አሉላ ይህንን ልኬልሃለሁ" እኔም "መስፍኔ ጨርሼ ልኬልሃለሁ" ከሚል አጫጭር የመልዕክት ስልክ ያለፈ ስለ ድርጅታችን ሁኔታ እንኳ አውርተን አናውቅም።

ይህ በእንዲህ እያለ ወደ ሀገር ቤት የሚተላለፍ ሬዲዮ ሲጀመር የመጀመሪያውን የተከፈተበትን ዓላማ አስመልክቶ የቀረበውን አንብቤሀለሁ። ከዚያ የኅብረት ሬዲዮ የቅዳሜው ዝግጅት እንደሚቋረጥ ስሰማ በበኩሌ አዝኛለሁ። በተለይ በውጭው ኅብረተሰብ ዘንድ መኖራችንን ከማሳወቅ አልፎ የምናወጣውን ዴሞክራሲያ ዕትም፡ መግለጫዎች፡ ከኛም አልፎ የሌሎችን (ለምሳሌ የኅብረቱን) መግለጫ የምናሰማበት፡ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ጉዳቱ ይታየኛል። ሆኖም ከአቅም በላይ ከሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም። ለዚህ የኅብረት ሬዲዮ መዘጋት አስመልክቶ የስንብት ድብዳቤ እጽፍ ዘንድ መስፍን ሲጠይቀኝ "አይ እኔ አጻጻፉ እንዴት እንደሚሆን ስለማላውቅ ይህንን በተመለከተ የሬዲዮ ቦርድ ውስጥ ካሉት ወይም ሌሎችን አጽፍ ይህንን ብትተወኝ ደስ ይለኛል" ብዬ ለራሱ ነግሬ እሱም "ችግር የለም ሌሎች ይጽፉታል" ብሎኝ የመጨረሻ የስልክ ንግግራችን በዚህ ነበር የተቋጨው። ከዚህ በኋላና ወደ ሀገር ቤት ከተላለፈው የመጀመሪያ ዝግጅት በሁዋላ ምንም የተላከልኝ ባለመኖሩ አንብቤም አላውቅ። ከመስፍንም ጋር የነበረን የአርብ አርብ ግንኙነት በአልገባኝ ምክንያት ተቋርጧል። ግና በወቅቱ የአንባቢ ችግር እንዳለበት እሰማለሁ፡ እኔንም ማግኘት እንዳልቻለ፡ የኅብረት ሬዲዮ ስንብት ደብዳቤ ፃፍ ተብዬ እምቢተኛ እንደሆንኩ ስሰማ ሁኔታውን ለማወቅ እራሱን መጠየቅ ስለሚያስፈልግ ደወልኩለት። በተደጋጋሚ በተለያየ ቀንና ሰዓት ደወልኩ፡ አያነሳም። መልዕክት ብተው አይመልስም። በስተመጨረሻ ቅዳሜ ጥር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. አገኘሁት የጠየኩት ጥይቄ ለምን ያላደረኩትን እንደሚያወራ ነው። ቁጣ ቀናው። ረጋ በል ብዬ እኔም ቁጣዬን ቀጠልኩ። "ልትጠይቁኝ በምትፈልጉት ጠይቁኝ እንጂ በጎን የምታደርጉትን ማጥላላትና ስም ማጥፋት አቁሙ" አልኩ። በዚህ ሁኔታ የሰጠኝን የመጨረሻ ስጦታ አደግሞ ለማለት አሳፋሪነቱ ቢገባኝም መግለጽ አለብኝና ቃሉን በቀጥታ በማስፈሬ ይቅርታ እየጠየቅሁ "ልንፋህ" "ተነፋ" የሚል ነበር።

ውድ የኢሕአፓ ዴ አመራር አባላት፡ እንኳን ከኢሕአፓ ዴ አመራር ቀርቶ ከማንኛውም የኢሕአፓ አባል እንዲህ ዓይነት ቃል ይወጥል ብዬ ስለማላምን



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በወረወራቸው አስጸያፊ ቃላት ክፉኛ አዘንኩኝ፡ ደነገጥኩም። በግል ሕይወቴም ሆነ በአሳለፍኩት የሀገር ቤት የሥራና የኃላፊነት ዘመኔ የተከበርኩ ነኝ። በሙያዬም ቢሆን ብዙዎችን ያፈራሁና እስከሁንም የሚገለገሉበትን ሥራዬን ያበረከትኩ ነኝ። ኢሕአፓን ዳግም ከተቀላቀልኩ ወዲህ የአካዳሚክ ጊዜዬንና ሕይወቴን ለድርጅቱ ባበረከትኩ ሌላው ቢቀር ልሰደብ አይገባም ነበር። ድሮ ድሮ፡ ያኔ በልጅነቴ፡ በኩራት "የኢሕአፓ መሪዎች እነማን ይሆኑ?" ብዬ የምጓጓለት፡ "ምን ዓይነት ልዩ ፍጡሮች ይሆኑ" ብዬ ውስጤ ያደንቅ የነበረው አንዳድ አረማሞ መኖሩን በልጅነት አዕምሮዬ ባለመረዳቴ ነበር። ተክለ ሰውነት መገንባት የሚፈልጉ ግለሰቦች ፍላጎታቸው እንዳይዛባባቸው ከፍ ከፍ የሚያደርጉት ሥራቸው የቀደመውን ሳይሆን አፋቸው ያወራውን ነው። ኢሕአፓም የዚህ ዕድል ሰለባ ሲሆን ያሳዝናል። ያስቆጫል። ታማኝነታቸውን ለድርጅቱ ሳይሆን ለግለሰብ የገለጹና የማሉ አንዳንድ አባላትና አመራር አካላት ቢሳደቡ፡ ስም ቢያጠፉ፡ የሠሩትን ጥፋት ቢክዱ ማን ጠያቂ ኖሯቸው። ጊዜ ጥሎት ኢሕአፓ ቤቱ የነሱ ሆናልና። ተስፋዬ ደበሳይ እንደ አንድ ተራ አባል ኢሕአፓ ሕይወቴ ብሎ ደሙን ያፈሰሰለት ፓርቲ እንደበታቸውን መቆጣጠር የማይችሉ ተንሠራፍተውበት እያየን እንዴት ነው የምንጓዘው ወገን።

በኢሕአፓ ዴ ቆይታዬ ያቀረብኳቸው ሀሳቦች የሠነዘርኩዋቸው አስተያየቶች ለምን ምላሽ/ተቀባይነት አላገኙም ብዬ የማኮርፍ አይደለሁም። ሀሳቤን ለብዙሃኑ መሸጥ እስክችል ድርጅታዊ ግዴታዬንና ኃላፊነቴን እየተወጣሁ መጓዝ እንዳለብኝ ይገባኛል። አሁን ያለንበት ሁኔታ ግን ሁላችሁ ውስጣችሁ ያውቀዋል አደገኛ ነው። እውነት እውነት እላችኋለሁ በዚህ አካሄድ የትም እንደማንደርስ ለማስተዋል ሞክሩ። መሸነጋገሉንና የአፍ ጨዋታውን እንተወውና ለእርምት እንነሳ። እንደ አመራር አባልነታችሁ በጋራ፡ እንደ አባልነታችሁ በግል የሠራችሁትን ስህተት ለመቀበልና ለማስተካከል ድፍረቱን ካገኛችሁ ለችግራችን ተገቢውን ምላሽ ሰጣችሁ። የድርቅና ድል ጊዜያዊ እንደሆነ ከታሪክ እንማር። አሉላ ለቅቄአለሁ። እንደተናገርኩትም ከኢሕአፓ ዴ ሳይሆን ከሰው ቤት። ኢሕአፓን ግን ምንጊዜም አልተውም፡ በዚሁ ቤት እንገናኛለን። ግን ነገ የምናፍርበት ሥራ ለታሪክ አንተው።

በኢሕአፓ ዴ ሂደት ሚስጥረ "የንባ-ባንቢስ" ን አሉላ ስለሚያውቅና አንድ ቀን ያጋልጠኛል ተብሎ ካለው ስጋት እንዴት ተደርጎ ወደ ዲዳነት እቀየር ዘንድ የነገር አሻሮ ሲቆላ ይገርመኛል። ያስቀኛልም። የዚህን ሚስጥር ጉዳይ አያይዤ ልኬላችኋለሁ። ለእውነት የቆማችሁ ፍርድ ስጡ፡ አለዚያ እውነት ትፋረዳችኋለች።

በስተመጨረሻም ልገልጽ የምፈልገው፡ ጥፋተኛው እያለ ለንባ-ባንቢስ ጉዳይ ሲባል ተገፍቻለሁ። ከአደረገው ሰው በቀር ይህንን ማንም አያውቅም። አባላት በመላ በወሰድኩት እርምጃ አዝነውብኛል፡ ከእኔ አልጠበቁምና አይፈረድባቸውም። ከጥቂት አመራር አባላት በቀር አብዛኞቻችሁ ለጉዳዩ ባዳ ትሆናላችሁ ብዬ እገምታለሁ። በድርጅታችን ውስጥ የተደቀነብንን ችግር በውይይት ፈትተን፡ የተሳሳትን ሁላ ስህተታችንን ተቀብለን በቅንነት ለመጓዝ ካልተዘጋጀን "እኔ ከሞትኩ…" ሂደት ሊያመጣ የሚችለውን መገመት አያቅተኝም። በንጹህ ልባችሁ ለመስተካከል እራሳችሁን ሞግቱት እላለሁ። የንባ-ባንቢስ ጉዳይ በአድራጊው ይቅርታ መጠየቅ ብቻ የሚፈታ ነው። አይ ተብሎ አሁንም ክህደት ላይ ከተኬደ ለዚህ ያደረሰን ችግር መዘዙ ነገም ይከተላልና እውነት ለኢሕአፓ ዴ የቆምን መፈተኛችን ዛሬ ነው። በመሆኑም፡



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 7 a

- አቶ መንግስቱ (የንባ) ጥፋቱን አምኖ ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴንና አባላቱን ይቅርታ ይጠይቅ ዘንድ አመራር አካሉን እጠይቃለሁ፡
- አቶ መስፍን ተፈራ በደፈናው "አሉላን የማያስፈልግ ነገር በመናገሬና ስሜቱን በመጉዳቴ ተጸጽቻለሁ" በማለት ለኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ አባላት ይቅርታውን ያሰማልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ።

ውድ የአመራር አካላት፡

ለፓርቲያችን ደህንነትና አንድነትና ዕድገት እስከ ተጓዘን ድረስ ጥፋት ያጠፋ እንደ ጥፋቱ መጠን ቢቀጣም፡ ይቅርታ መጠየቅ ደግሞ ትልቅ አዋቂነት ነው። በተለይ ዛሬ ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ የደረሰበትን አጣብቂኝ ውስብስብ ያደረገው የንባ-ባንቢስ ጉዳይ አመራሩ በጥያቄዬ መሠረት እንዲያስተናግደው እጠይቃልሁ። የንባ (አቶ መንግሥቱ) ካደ አልካደ እንደ ሃይማኖቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይዤ፡ እንደ ፖለቲከኛነቴ የሀገሬን ባንዲራ በቀኝ እጄ የኢ.ሕ.አ.ፓን አርማ በግራዬ ይዤ በማከብራቸው አባላት ፊት የእውነት ምስክርኔቴን የማቀርብበት ጊዜው እሩቅ አይሆንም። ይህ የሆነ ዘንዳ ደግሞ እጅጉን ፓርቲውን እንጎዳዋለንና ሳታመነቱ ውሳኔ ስጡበት።

በአያያዝኩት የንባ-ባንቢስ ምስክርነቴ ላይ እንደገለጽኩት ወንድሜ መስፍን ተፈራ ለኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ ስትል የምታውቀውን ትናገረው፡ ታወጣው ዘንድ እጠይቃለሁ።

ወደ ድርጅቱ ተመልሼ የሚጠበቅብኝን ግዴታዬን እወጣ ዘንድ ከፈለጋችሁኝ የንባ-ባንቢስ ጉዳይ ዕልባት ያግኝ ባይ ነኝ። መልሱ አይሆንም የንባን መከላከል አለብን ከሆነ እናንተ እሱን ተከላከሉ እኔ ደግሞ የአቅሜን ኢ.ሕ.አ.ፓን እከላከላለሁ።

ቸር ይግጠመን

አሉላ
የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. (February 23, 2010)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

Footnote # 7B

**Nesibu, Abeba, Adam and all:**

**Mesfin's vulgarity and homosexual infatuation on Nesibu, manifested by his use of the offensive words "Linfah" and "Tenefa", should not surprise anyone who knows him closely. The DC comrades can attest to this more. I was actually dumbfounded when I learned that he was elected to EPRP-d's council. It must have been the work of Ato Mersha. In return for Mesfin's unconditional loyalty, Ato Mersha must have covered up Mesfin's undisciplined and immoral characters. Ato Mersha must have concealed information on the role Mesfin played during red terror in Addis Ababa, from EPRP members. Had members knew his character and past history, I don't think they would elect him to the council. They may not deny him conditional membership, but I don't think members would be careless to give him the highest responsibility in the organization. Let me share few facts I know about Mesfin Tefera. If Mesfin contests any of these facts, I will produce witnesses and evidence to anyone interested.**

**1) Do members of EPRP (d) know that by a majority vote Mesfin was reprimanded and then expelled from the old EPRP KEAKO? May be very few people know about this. Yes**

**a. Mesfin Teferra was brought to KEAKO (EPRP's leadership before the split) by Ato Mersha.**

**b. Mesfin Teferra was reprimanded by KEAKO for what they said was undisciplined and vagabond behavior, and association with enemy elements of EPLF.**

**c. When he failed to show improvement, he was expelled from KEAKO, until the split.**

**2) During Red Terror in Addis Ababa, Mesfin Teferra has exposed many EPRP members. As an informant, he cooperated with the fascistic derg to send several EPRP members to prison and "Maeklawi's" torture chamber.**

**3) In the early 1990s, while chairman of CODEF, ato Mersha, through his loyal soldier Mesfin Tefferra, worked relentlessly to replace EPRP with COEDEF. Weakening EPRP for almost 10 years.**

**These are few facts I know about the guy. Hence, don't be shocked by his vulgarity, it is his character.**

**Also, Abeba's characterization of the Mersha group as MAFIA is giving them undue credit. Albeit for bad reason, the Mafia is well structured and committed to their family. The Mersha group, on the other hand, is full of individuals who are intoxicated with their own ignorance and stupidity, they can't even see their own demise. The sad thing is, they are taking few dedicated individuals and our organization down with them.**

**With regards**
**Andarge Beyene**

Footnote # 8

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ለኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አካላትና አባላት በያሉበት፦

ጥር ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ. ም
January 22, 2010

በቅድሚያ ጓዳዊ ሠላምታችን ይድረሳችሁ፦

አንድ የፖለቲካ ድርጅትን እንደ ድርጅት እንዲቆም ከሚያደርጉትና ሊጠቀሱ ከሚገባቸው አበይት ጉዳዮች መካከል በመጀመሪያ አባላቱ ከሚጋሩት የፖለቲካ ራእይ የሚመነጭ የፖለቲካ ፕሮግራምና እንዲሁም በአባላቱ የጋራ አስተሳሰብና ትግሉና ድርጅቱ ባለበት አጠቃላይ ይዞታ ላይ ተመስርቶ፣ ትግሉ የሚጠይቀውን የአደረጃጀት ይዘትና ቅርጽ (አወቃቀር) ሊያስተናግድ የሚችል ህገ-ደንብ (ውስጠ ደንብ) መኖር ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው።

በአንድ የፖለቲካ እምነት ላይ የጋራ ግንዛቤ ያላቸውና ለወደፊቱ ምን መደረግ አለበት? ለሚለው ጥያቄ አንድ ወይንም ተቀራራቢ መልስ ያላቸው ግለሰቦች አንድ ላይ በመምጣት ያላቸውን ሃይል እንዴት ሊያስተባብሩ እንደሚችሉ፣ እንዴት መደራጀት እንዳለባቸው፣ ማን ምን ማድረግ እንዳለበት፣ ሥራዎች እንዴት መሠራት እንዳለባቸውና የእያንዳዱ ግለሰብ መብትና ግዴታ ምን እንደሆነና በአጠቃላይ በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት በሚያትት ህገ ደንብ ተሳስረውና ቃል ኪዳን ገብተው ነው ድርጅት የሚፈጥሩት። እነዚህን ግለሰብ አባላት ሊያስተሳስር የሚችለውና ድርጅታዊ መዋቅር ሊፈጥርላቸው የሚችለው ይሄው ደንብ ሲፈርስና ሲናድ፣ ከበሬታ ሲያጣ፣ ድርጅትም ማሰሪያው እንደተበጠሰ የእንጨት ሸክም ዝርግፍግፉ ይወጣል።

ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ፕሮግራማቸውም ይሁን ህገ ደንባቸው በየጊዜው ሊለወጥና ሊሻሻል ፣ ጊዜንና ሁኔታን ሊያስተናግድ በሚችል መልክ ተቀርጾ ሕይወት ያለው ሊሆን ይገባል። ባለው ህግ ላይ እየተመሰረቱና ያለውን ደንብ እያከበሩ ሊለውጥ የሚገባውን መለወጥ ደግሞ የአባላቱ መብትና ሃላፊነት ይሆናል። ያለውን ለመለወጥም እንዴት ለውጥ እንደሚመጣ የሚደነግገዉን ህግ መከተል ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ደግሞ ለውጥ ሥርዓት ያለውና ከቀውስ የጸዳ ይሆናል። አንድ የፖለቲካ ድርጅት መኖርና ትግሉን መቀጠል

850 Sligo Avenue Suite # 8
Siver Spring , MD 20910

P.O.Box 8141
Silver Spring, MD 20910

P.O.Box 88675
Los Angeles, CA 90009

Phone: 301-578-4466 Fax: 301-449-8363 Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

Footnote # 8

የሚችለው በውስጡ የተሰባሰቡት አባላቱ የድርጅቱን ሕገ-ደንብና አሠራር አክብረው ከቀጠሉ ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ግን ስንት ተቀናቃኝ ያለበት የፖለቲካ ድርጅት ይቅርና በበጎ አድራጎት ላይ የተመሠረተ ዕድርም ቢሆን እንኳ ዕድርተኛው ህጉን ካላከበረለት ህልውናውን ጠብቆ መቀጠል አይችልም።

ድርጅታችን ኢ.ሕ.አ.ፓ(ዴሞክራሲያዊ)ም አሠራሩ ዴሞክራሲንና ዲሲፕሊንን ያማከለ ነው። አባላትና አካላት የሚስማቸውን አስተያየት የመግለጽና ሥርዓት ጠብቀው ከሌሎች ጋር የመወያየት መብታቸው በህገ ደንባችን በግልጽ የተቀመጠ ነው። ተቃውሟቸውን በድርጅታዊ ሰንሰለታዊ አሠራር መሰረት ለበላይ አካል የማሳወቅ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የበላይ አካል ውሳኔን በተግባር ማዋል ግን ግዴታቸው ነው። (ህገ-ደንብ ክፍል አራት ቁጥር 1.3.2)

ከልዩ ጉባኤያችን ጀምሮ ውስጠ ድርጅታዊ ሁኔታችንን በማጠናከር ሰፋ ያለ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎች እንዲኖሩ፣ ተጠያቂነት ከፍ እንዲል፣ አሠራራችን አንጻራዊ ግልጽነት እንዲይዝና እነዚህ ለውጦችም አፍአዊና ጊዜአዊ ሳይሆኑ ቋሚና ተቋማዊ ለውጦች እንዲሆኑ ለማድረግ የማይናቅ ክንዋኔዎችን አድርጓል። ከነዚህ መካከል አንደኛ፣ አመራርን በተመለከተ የግለሰብ ተክለ ሰውነት እንዳይፈጠር የዕድሜ ልክ አመራር የሚባል እንዳይኖር ለማድረግ የወጣው ደንብ ነው። ለአመራር ኮሚቴ የሚመረጡ አባላቱ በኮሚቴው ውስጥ አንዱ ከአንዱ የማይበላለጥና እኩል ሥልጣን ያላቸው እንዲሆኑና በጋራ ዴሞክራሲያዊ የአመራር መተክል እንዲሠሩ የሚደነግገው ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተጨማሪ ደግሞ የእያንዳንዱ የአመራር ምክር ቤት አባል ተከታትሎ ሊመረጥ የሚችልበትን ጊዜ እንዲገደብ ሆኗል። ይህም በመሆኑ ህገ-ደንባችን በአመራር ኮሚቴው ውስጥ በየጊዜው አዳዲስ  አባላት እንዲገቡና መቀያየር የግድ እንዲኖር ለማድረግ እንዲያስችል ሆኖ ነው የተቀረጸው። በሁለተኛ ደረጃ፣ የአባላት መብት በእንድምታ እንዳይሸረሸርና ህገ-ደንቡም በማንኛውም አካልም ይሁን ግለሰብ ያላግባብ እንዳይጣስ፣ ተጠያቂነትም ተቋማዊና ተከታታይ እንዲሆን ለማብቃት የሚያስችል የህግና-የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጓል። የእነዚህን ተቋማዊና ህገ-ደንባዊ ለውጦች ይዘትና አገልግሎት በተመክሮ ለማዳበርና ለማጠናከር ብዙ ሥራ ወደፊት የሚጠበቅ ቢሆንም  መሠረቱ ግን ተጥሏል። በምሳሌነቱም ለሌሎችም ተቃዋሚ ድርጅቶች ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ነውና ልንኮራበት የሚገባ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በብዙ ተመክሮ ገና ያልዳበረ አዲስ ያቋቋምነው ተቋም መሆኑን ተገንዝበን፣ ለማደግና ለመጠናከር ዕድል ልንሰጠውና ልንደግፈው ይገባል። በዚህ መልክ ነው ድርጅት የሚገነባው፣ የሚዳብረው፣ ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ተግባራዊ እድገት የሚኖረው ብለን እናምናለን።

የኢ.ሕ.አ.ፓ(ዴሞክራሲያዊ) የአመራር ምክር ቤት ዋናው ሃላፊነቱ ጠቅላላው ጉባኤ የወሰናቸውን ውሳኔዎች ማስፈጸምና በነዚህ ውሳኔዎች ላይ ተመስርቶ ትግሉን መምራት ነው። የድርጅቱ አሠራር ሥርዓትንና ደንቡን የተከተለ እንዲሆንና ሥራዎችም በትክክልና

Footnote # 8

ወግ ባለው መልክ መሠራታቸውን ከማስረገጥ ወጥቶ ምክር ቤቱ አባላት በጉባኤ የወሰኑትን ውሳኔ የመሻርና የመቀየር ምንም ሥልጣን የለውም።

የድርጅታችን አምስተኛ ጉባኤ የመረጠው አመራር ካውንስልም እንደዚሁ የድርጅቱን ደንብና ሕግጋት ተከትሎ መሥራትና ጉባኤው የወሰናቸውን ውሳኔዎች መከተል ይጠበቅበታል። ጉባኤው በተጠናቀቀ ጥቂት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ከተመረጡት የአመራር ኮሚቴ አባላት መካከል ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው የኮሚቴው አባል ሆነው ከተመረጡት ሌሎች አባላቱ መካከል አንዱን ከምክር ቤቱ መውጣት አለበት፤ እንዲያውም የአመራር ምክር ቤቱን እንዳለ አልወደድኩትምና መፍረስ አለበት በሚል የቀሰቀሰውን ውዝግብ፣ በምክር ቤቱ በኩል በመቻቻልና ሥርዓትና ወግ ባለዉ መንገድ ለመፍታት ያልተደረጉ ጥረቶች አልነበሩም። ዶ/ር ጌታቸው በርካታ ተከታታይ የማደፍረስና ሥርዓትንና ደንቦችን የማፍረስ ተግባር ቢፈጽምም፣ በመቻቻል መፍትሄ ማምጣት ይቻላል በሚል ተስፋ የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ ሳይሳኩ ቀርተው እንደምታውቁት ዶ/ር ጌታቸው ከSeptember 1, 2009 ጀምሮ አካሉን በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ በቅቷል።

አምስተኛውን ጉባኤ በተመለከተ ዶ/ር ጌታቸው በጻፈውና በተለያየ ጊዜ እንደገለጸው "ከአዘገጃጀቱ አንስቶ እስከ አፈጻጸሙ ድረስ የሚያሳፍርና የሚያስጠረጥር ነበር" ይለዋል። በአጠቃላይም "ውድቅ"፣ ጉባኤ ነበር ብሎም ይደመድማል። የምክር ቤቱን አባላት ለመምረጥ የተደረገዉን የምርጫ ሂደት ደግሞ "ምንም ተቀባይነት የማይገባው የፌዝ ምርጫ" sham and bogus election ብሎ ይሰይመዋል። የተመረጠውን አመራር ካዉንስል "በአንድ ግለሰብ ዙሪያ የተማከለ" ብሎ ይከሰዋል። ይህንና ይህን በመሳሰሉት ክሶችና ውንጀላዎች የተሞላውን የመልቀቂያ ደብዳቤ ነበር ዶ/ር ጌታቸው ለአባላት እንዲላክለት ካውንስሉን የጠየቀው። አባላት የዶ/ር ጌታቸውን ከካውንስል አባልነቱ መልቀቅ ማወቅ ያለባቸው ስለነበረ ምክር ቤቱ ይህንኑ ከማሳውቁ በፊት፣ የዶ/ር ጌታቸው አቀራረብ የጉባኤውንም ይሁን የምክር ቤቱን ህጋዊነት የሚጠይቅና ክስና ውንጀላም ያለበት በመሆኑ ህገ-ደንባችን በሚያዘው መሠረት የአባላት መብትንና የህግ አስጠባቂ ኮሚሽንን የሚመለከተው ሆኖ ስለአገኘው ኮሚሽኑ መርምሮ ከህጋችን አንጻር መፍትሄ ወይንም አስተያየት እንዲስጠና አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ እንዲወስድ ደብዳቤው ለዚሁ ህጋዊ አካል ተልኳል።

ዶ/ር ጌታቸው ከዝግጅቱ ጀምሮ "የሚያስጠረጥር" ነበር የሚለው አምስተኛው ጉባኤ ሁሉንም የድርጅት አባላት በውክልና ብቻ ሳይሆን ለመገኘት የሚችሉ ሁሉ በነፍስ ወከፍ በአካል መሳተፍ እንዲችሉ ያደረገ በመሆኑ ሕጋዊነቱን "ሊጠረጠር" የሚያስችለው አንድም ሁኔታ ነበር ብለን አናምንም። የተመረጠው የስብሰባ ቦታም ራሱ ዶ/ር ጌታቸዉ በሚኖርበት ከተማ በመሆኑ እራሱና በቅርቡ ያሉ የድርጅት አባላት ከሌሎች በአየርና በመኪና ረጅም ጉዞ አድርገው ከተሳተፉት የበለጠ ጉባኤውን ለመሳተፍ እንዲችሉ አደረጋቸው እንጂ ድብቅና "የሚያስጠረጥር" ሁኔታን ሊፈጥር የሚችል አልነበረም። የሚያስጠረጥር ነገር አለ ብሎ ካመነም ላለፈው ምክር ቤት አቅርቦ እንዲታይለት ማድረግ

Footnote # 8

ይቻለው ነበር፣ በጉባኤውም ላይ ነበረኝ የሚለውን ቅሬታ ለጉባኤው አቅርቦ እንዲታይለት ማድረግ ይችል ነበር። ይህን ግን አላደረገም። ዶ/ር ጌታቸዉ "አሳፋሪ" ነበር በማለት የሚዘልፈው የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ አሁን ያለውን የአመራር ምክር ቤት ብቻ የሚመለከት አይደለም፤ በጉባኤ ላይ የተሳተፉ አባላትን ሁሉ የሚያናንቅና የሚያጥላላው ነበር። ጉባኤውንና በጉባኤው የተሳተፉትን የድርጅቱ አባላትና ድርጅቱን ነው የሚያራክሰው። አገር አቋርጠውና ሥራና ቤተሰብ ጥለው ለትግልና ለድርጅት ግንባታ ሲሉ የተሰባሰቡት አባላትና እነሱ የሰየሙት ጉባኤ ሊሰጠው የሚገባውን ከበሬታ ከዶ/ር ጌታቸዉ ማግኘት ነበረበት/ነበረባቸው እንጂ በድፍረት "ውድቅ" በማለት ሊጥላሉ ባልተገባቸው ነበር።

ዶ/ር ጌታቸው በርግጥም በጉባኤውና በድርጅቱ አባላት እምነትና ክብር ቢኖረው ኖሮ መስተካከል አለበት የሚለውን ጉዳይ በዚያው በጉባኤው ላይ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችል ነበር። የሂደቱ አካል ነበር፣ ጉባኤው ሲዘጋጅ ነበር፣ በጉባኤው ተሳትፏል፣ በምርጫው ሂደትና በውሳኔዎቹ ላይ ነበር፤ በእጩዎች ጥቆማ ላይ ተሳትፏል፣ ድምጽ ስጥቷል፤ እራሱም ተመርጧል። ያልተስማማውና ያልጣመው ነገር ቢኖር የመጨረሻው ውጤት ነው። የግል ፍላጎቱ ሳይሟላ፣ ቀድሞ በድብቅ ያደረገው ቅስቀሳ ሳይሳካ ሲቀርና መደምደሚያና መጨረሻው እሱ እንደፈለገው ሳይሆን ሲቀረ ጉባኤው ካበቃና ከተበተነ በኋላ፣ የጉባኤው ውሳኔዎች እንዲገለበጡ ህጋዊነት በሌለው መልክ ቅስቀሳ ማድረጉና ዘመቻ መጀመሩ የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ መንፈስ የተከተለ አይደለም።

ዶ/ር ጌታቸውና በራሱ ዙሪያ ያሰባሰባቸው ግለሰቦች የጉባኤውን ውሳኔና ሂደት በማጥላላትና በማጣጣል አባላት በበጎና በደስተኛነት ታሪካዊ እያሉ የጠሩትንና በግልጽነትና ያለምንም ገደብ ሃሳባቸውን በማቅረብ ለየእምነቶቻቸው የተሟገቱበትን ጉባኤ ውድቅ የሆነ፣ የተደናቀፈ...ወዘተ የሚል ቅጽል በመስጠት አባላት በአዲስ መንፈስ ትግሉን ለማስቀጠል የነበራቸዉን ተስፋ ለማጨለም ሞክሯል። ወደ ጭቅጭቅና ንትርክ እንዲለወጥ ለማድረግ ፏችሯል። በአዲስ የተመረጠውን የአመራር ምክር ቤትም "አልወደድኳችሁም"ና ምክር ቤቱ መፍረስ አለበት በሚል አወጀ። ምክር ቤቱ ይህን አልተቀበለውም። አንድ የምክር ቤት አባል በአምባገነንነት ምክርቤቱ ይፍረስ ሲል እንዴትስ ብሎ ሊቀበለው ይችላል?

ዶ/ጌታቸው በርግጥ ጉባኤው እሱ እንዳለዉ ከሆነና ምርጫውም "ተቀባይነት የሌለዉ ከሆነ፣ ለምን ራሱ በዚህ ምርጫ በመመረጥም ይሁን በመምረጥ ተሳተፈ? በእጩነት ተጠቁመዉ እንቀበለውም ያሉትን የቀድሞው የምክር ቤት አባላት እጩነቱን መቀበል አለባቸው በሚል ተከራክሮ እንዳልነበረ ሁሉ እነዚሁ ግለስቦች በአንድ ግለስብ ዙሪያ የተማከሉ ናቸዉ በሚል ሊከሳቸዉ ለምን ተነሳ? ለምን የድርጅቱ ከፍተኛ አካል የሆነው የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ተሰብስቦና ውሳኔ ሊስጥ በሚችልበት ሁኔታ ላይ እያለ በግልጽነትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ትክክል አይደለም የሚለውን በማንሳት ሃሳቡን አቅርቦ አባላት ውሳኔ እንዲሰጡበት አላደረገም? ለምንስ ከተመረጡት የምክር ቤት አባላት ጋር አብሮ ለመሥራት የማያስችለኝ ነገር አለ ብሎ ካመነ፣ ለጉባኤው ይህንኑ አቅርቦ እራሱን ከምክር-ቤት እጩነት እወጣለሁ አላለም? ጉባኤውስ እዚያው ላይ የቀረበውን አዳምጦ ውሳኔ የመስጠት

Footnote # 8

ዕድሉን ለምን ተነፈገና ሳምንታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌላ ጉባኤ ይጠራ፣ ምክር ቤቱም ይፍረስ ወደሚል ውዝግብ ድርጅቱን ለመክተት ፈለገና ትግሉንና ድርጅቱን የማዳከሙን ተግባር ሥራዬ ብሎ ተያያዘው?

የምክር ቤቱን አመራረጥ በተመለከተ ጉባኤው እንደ ከፍተኛው የድርጅቱ አካል ከፕሮግራም መቀየር፣ እስከ ህገ-ደንብ ማሻሻል፣ የትግሉን አቅጣጫ እንዳመነበት ከማድረግ እስከ ትግሉን የሚመሩትን አመራር አባላትን ቁጥርና የአመራረጥ መንገድ የመወሰንና ማንኛውንም ድርጅቱን የተመለከተ ሁሉ የማድረግ ያልተገደበ ሥልጣን አለው። መሪዎቹን የመምረጥ፣ የቆዩትን ሁሉም ወይም በከፊል እንዳይቀጥሉ አድርጎ ሌሎች አዲሶችን የመተካት፣ የነበሩት እንዳሉ ይቀጥሉ የማለትም ይሁን ቁጥሩን ከፍ ዝቅ የማድረግ ሥልጣን በጉባኤው እጅ እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም። ሕጋዊ ሆኖ የተሰየመውን ጉባኤ ህጋዊነት አስመልክቶ ጥያቄ ካልተነሳ በቀር፣ በጉባኤው የተገኙ የድርጅቱ አባላት ሁሉ ውሳኔዎችን በመወሰን ረገድ የነበራቸውና ሊኖራቸው የሚገባቸው ሥልጣን የአንድ ድምጽ ያክል ብቻ ነው። ዶ/ር ጌታቸው ከዚህ የተለየ ሥልጣንና ድምጽ ይገባኛል ካላለ በስተቀር?! ስለዚህም እንደማንኛዉም የጉባኤው ተሳታፊ የሚሰማዉን እምነቱን ለጉባኤው የማቅረብ መብት ነበረው። ጉባኤውም ሃሳቡን ሰምቶ ሊቀበለውም ላይቀበለውም የሚያስችለው ሥልጣን ነበረው። ጉባኤው ግን ዶ/ር ጌታቸው ያላነሳውንና ያላቀረበውን ገምቶ ዶ/ር ጌታቸውን ሊያረካ የሚችል ውሳኔ ላይ ለመድረስ አይቻለውም። ስለዚህም የዶ/ር ጌታቸው ችግር ዴሞክራሲያዊ አሠራር የሆነውን የብዙሃንን ውሳኔ ያለመቀበል ብቻ ሳይሆን ለጉባኤ ያላቀረበውንና ጉባኤው የመወያየት ዕድል ያላገኘበትን ጉዳይም እሱ እንደፈለገው አልሆነም በሚል መቃወሙና አልፎም ውሳኔው ተሽሮና ሂደቱ ተቀልብሶ "ጨዋታ ፈረሰ ነገር ደፈረሰ" እንዲሆን ለማድረግ መሞከሩ በፍጹም ተቀባይነት የሌለው የአፍራሽነት ተግባር ነው። ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ድርጅቱንና ትግሉን እንዲመራ ሃላፊነት የተሰጠው ምክር ቤት ደግሞ ጉባኤው የሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት ይሠራል እንጂ አንድ የምክር ቤት አባል ሃላፊነት በጎደለው መልክ የጉባኤውን ውሳኔ ካልደመጠጥኩ የምክር ቤቱን ውሳኔ አልቀበልም ስላለ ብቻ፣ ሃላፊነትና አደራን ወርውሮ መጣሉን ምክር ቤቱ አልተቀበለውም፣ አይቀበለውም።

ምክር ቤቱ በህገ-ደንባችን መሠረት ዴሞክራሲያዊ አሠራርንና የጋራ አመራር መተክልን ተከትሎ የሚሠራ አካል ነው። በምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ የተመረጡ ሁሉም አባላቱ እኩል ሥልጣን ያላቸዉ ናቸው፣ ሆነውም መሥራት አለባቸው ብለን እናምናለን። አንድም የምክር ቤት አባል የራሱን አስተሳሰብና ፍላጎት በአብዛኛው አባላት ላይ የመጫን መብትም ሥልጣንም የለውም። የግለስብን አዛዥ ናዛዥነት፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ መሬት ይገመሳል፣ ሰማይ ይታረሳል በሚል በማስፈራራትና በመዛት ድርጅቱን ከዴሞክራሲያዊነት ወደ ግለሰብ አምባገነንነት እንዲዘቅጥ አንፈቅድም። ዶ/ር ጌታቸዉ የድርጅቱን መሠረታዊ የዴሞክራሲያዊ አሠራር አይቀበልም። የጉባኤውን ሥልጣንና ውሳኔ እንደሚጋፋዉ ሁሉ በምክር ቤቱ ውስጥም ሃሳቡን ለሌሎች አካፍሎና የሌሎችንም ሰምቶ ምክር ቤቱ በጋራ የሚወስነውን ውሳኔ ከመቀበል ይልቅ በግልጽ "አልቀበልም!"፣ "የብዙሃን ድምጽ አይገዛኝም"

Footnote # 8

“የብዙሃን/አናሳ የሚል አሠራር አልቀበልም” በሚል በትዕቢትና በድፍረት የምክር ቤቱ ውሳኔ ተግባራዊ እንዳይሆን የማሰናክል ሁኔታዎችን ሲፈጥር ቆይቷል። ይህ አምባገነናዊ አዝማሚያው ደግሞ አሁን ባለው ምክር ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ባለፈዉ ምክር ቤትም የአንድ ዓመት ተኩል የሥራ ዘመን ወቅት በተደጋጋሚ የተከሰቱበት ሁኔታዎች በርካታ ነበሩ። ማስፈራራትና ወዮላችሁ ማለት የዶ/ር ጌታቸዉ የተለመዱ ባህርያት ናቸዉ። አሥራ አምስቱን የምክር ቤት አባላት (አርባ ከመቶ የሚሆኑት አዲስ ተመራጮች) ያለምንም እፍረትና በንቀት በአንድ ግለሰብ ዙሪያ የሚያጎበድዱ አድርጎ ያስቀምጣቸዋል። ይህ ድፍረቱና ትዕቢቱ ለራሱ ከሚሰጠዉ ያልተመጣጠነ ግምት የሚመነጭ መሆኑን በተለያዩ የምክር ቤቱ አባላት ላይ በሚሰነዝራቸዉ ዘለፋና ትንኮሳዎች አሳይቷል። በምክር ቤቱ በኩል ደግሞ በተለያየ ጊዜ በግልም ሆነ በጋራ በመሆን ዶ/ር ጌታቸው የሚያሳየውን አምባገነናዊ ፀባይ ቀይሮ የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ አሠራር እንዲከተልና ያለውን ሃሳብና አስተያየት እያቀረበ ገንቢ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ተሞክሯል። አልሆነም፣ አልተሳካም።

ጉባኤው የመረጣቸውን የምክር ቤት አባላት በግፊትና በተጽእኖ ምክር ቤቱን ትተው እንዲወጡ አጥብቆ ገፍቷል። አባላቱ በምክር ቤቱ መቀጠላቸዉ አይጠቅምም ብሎ የማመን ግለሰባዊ መብቱ ቢሆንም፣ አባላት በጉባኤ የመረጧቸውን የምክር ቤት አባላት እሱ ስላልፈለጋቸው ብቻ መውጣት አለባቸው በሚል የሚያደርገዉ አግባብ የሌለው ግፊት ዴሞክራሲያዊ ካለመሆኑም በላይ የድርጅቱን የተለመደ አሠራር መርኅ የተከተለ አይደለም። እነዚህ ግለሰቦች እንዳይመረጡ በግልጽ በጉባኤው መድረክ ላይ መከራከር እድሉ እየነበረው ጉባኤው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በየቦታው የድርጅት አባላት ለሆኑና ላልሆኑ በግለሰብ እየተገናኘ ይህንን በማናፈስና በመቀስቀስ ድርጅቱን ለማናጋት መሯሯጥ ግን በፍጹም ተቀባይነት የለውም። የድርጅታችንን ዴሞክራሲያዊ መሠረት ያናጋል።

ዶ/ር ጌታቸዉ የ“የንባ-ባንቢስ” ንግግር በሚል ያቀረበውን ክስ ምክር ቤቱ እንደ ሽፋፈነ አድርጎ ይከሳል። ወረቀት አገኘሁ ብሎ ለምክር ቤቱ ያቀረበው ራሱ ዶ/ር ጌታቸዉ ሲሆን፣ ምክር ቤቱ ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን አስቀያሚ ዘረኝነትን ተመልክቶ ተከሳሹ አባል በርግጥ ይህን አድርጓል ወይ? የሚለው እንዲጣራ ወስነ። በዚህም መሠረት የመጀመሪያዉ ጥያቄ ዶ/ር ጌታቸው ይህን መረጃ ብሎ ያቀረበውን ከየት እንዳመጣ ሲጠየቅ አሻፈረኝ፣ በምንም ሁኔታ ምንጬን አልገልጽም ነበር የዶ/ር ጌታቸዉ መልስ። ጉዳዩን የሚያጣራው የአባላት መብትና ህግ አስጠባቂ ኮሚሽኑም ሲጠይቀው ይህንኑ የአሻፈረኝ መልስ ነው የሰጠው። በርግጥ በህቡእ ከሚታገልና ከፍተኛ መተማመንና ትሥሥር ከሚጠበቅበት አንድ ታጋይ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ከሆነ ግለሰብ ምንጩ ከየት እንደሆነ አልገልጽም፣ ግን ተከሳሹ አድርጓል ተብሎ ታምኖ ይከሰስልኝ ማለት ይጠበቅ ነበር? ማንም ሰው ወንጀሉ በማስረጃ እስከሚረጋገጥበት ድረስ ነፃ ነው፤ “Everyone is presumed innocent until proven guilty” የሚለውን የፍትህ ዝቅተኛው መብት እንዴት ለፍትህና ለህግ የበላይነት ሲታገል አያሌ መስዋእትነት ከከፈለና እየከፈለ ካለ አንድ ድርጅት ለራሱ አባል በጭፍን እንዲነፍግ ይገፋል? ዶ/ር ጌታቸው ተሸፋፈነ የሚለውስ እስኪ ማን ነው ጉዳዩ ግልጥነት

Footnote # 8

እንዳይኖረው ያደረገው? ጉዳዩን ያመጣዉ እሱ ራሱ፣ ምንጩን አልናገርም ያለ እሱ፣ ምኑ ተገልጦ ነውና የሚሸፈነው? ዶ/ር ጌታቸው ይህን ወረቀት ያገኘው በርግጥ ከሌላ ምንጭ ነው? ወይንስ በተወሰነ ደረጃ ቅሬታ አላቸው የሚላቸውን ግለሰቦች ልብ በመሳብ ድርጅት የማፍረስ ሤራ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከዛ ጊዜ በኋላ የሆኑትና ያደረጋቸውን ተግባሮች መመልከቱ በቂ ነው።

ዶ/ር ጌታቸዉ፣ አመራር ካውንስሉ ጊዜ ወስዶ ያለዉን ችግር ለመነጋገርና ለመፍታት ያደረገውን ጥረት አልቀበልም በማለቱና ከዛ አልፎም ይቀርባቸዋል ምናልባትም ያከብራቸዋል በሚባሉ ግለሰቦችና እንዲሁም የቀድሞ የምክር ቤት አባላት ያሉበት የመምከርና የሽምግልና ሙከራ አሻፈረኝ በሚል ምክር ቤቱን በገዛ ፈቃዱ ለቆ ወጣ። ዶ/ር ጌታቸው ከምክር ቤት አባልነቱ እራሱ ካገለለ በኋላ የድርጅቱን ህገ-ደንብ ክፍል 5፣ አንቀጽ 4፣ ቁጥር 4.5 እና 4.6 በመጻረር የአመራር ምክር ቤት አባል በነበረበት ወቅት ምክር ቤቱ በሰጠው ሃላፊነት የሚያዉቀዉን ድርጅታዊ ሚስጥር የጉዳዩ ባለቤት የሆነዉ ምክር ቤት ምንም ፈቃድ ሳይሰጠው Sep 18, 2009 በመድረክ አሰፈረ። ምክር ቤቱ ይህን የህግ ጥሰት አስመልክቶ ከተወያየ በኋላ ድጋሜ እንዳያደረግ ጥንቃቄ እንዲወስድ የሚያስገነዝብ ደብዳቤ ለዶ/ር ጌታቸው ጻፈለት። የዶ/ር ጌታቸው መልስ በፈለገው ጊዜና ሁኔታ በእጁ ያሉትን ዶሴዎች እንደሚጠቀምባቸው፣ ማንምም እንደማያቆመው መዛት ነበር።

በማስከተልም ምንም እንኳን ምክር ቤቱ ዶ/ር ጌታቸው ራሱ በሁሉም አህጉሮች በሚደረጉ የአባላት ቴሌኮንፈረንሶች በመሳተፍ በእርሱ በኩል አሉ የሚላቸዉን ጉዳዮች ለአባላት ማስረዳት እንዲችል ቢመቻችለትም ምክንያት በማቅረብ እርሱንና ምክር ቤቱን ለማዳመጥና ግንዛቤ ለመውሰድ የተሰበሰቡትን አባላትና ስብሰባውን ረግጦ ወጣ። ከወጣም በኋላ ከጥላሁን በፈቃዱ ጋር በመመሳጠር የድርጅቱን አባላት የኢይሜል አድራሻ ያለፈቃዳቸው በመሰብሰብና ከድርጅት ውጭ ያሉ ግለሰቦችን በመጨመር በድርጅቱ ስም ሌላ መድረክ ከፈተ። መድረኩንም በመጠቀም ድርጅቱን ለመከፋፈልና የተወሰኑ አባላትን በማስወገድ የተወሰኑትን ደግሞ ከሌላ ድርጅት አባላት ጋር ቀላቅሎ ከሌላ ድርጅት ጋር በመሆን መቀጠል ዓላማው እንደሆነ በይፋ አወጀ። ሌሎች የድርጅቱ አባላት የድርጅቱን መመሪያ እንዳይቀበሉና ህገ-ደንቡን እየጣሱ እሱን እንዲከተሉ ማበረታታትና መቀስቀስ የሌት ተቀን ሥራዉ አደረገው። ቀደም ሲል ለምክር ቤቱ በላከው መልእክቱ እንደዛተውም በእጁ የነበሩ የድርጅቱን ዶሴዎች በማሰራጨት ለዚሁ የብተና ፕሮፖጋንዳ ተግባሩ ተጠቀመባቸው። ኢትዮጵያዊ ባህልና ድርጅታዊ ሥነምግባር በጎደለው መልክ አባላትን የማዋረድና የመስደብ ተግባር ላይ ተሰማራ። ጉባኤውን “ውድቅ” ነው በሚል እንደማይቀበለው ገለጸ፣ የተመረጠውን ምክር ቤት “አምባገነን” ነው ብሎ ሰየመው፤ አባላት በእምነት ያቋቋሙትን የአባላት መብትና ህግ አስጠባቂውን ኮሚሽን የምክር ቤቱ መገልገያና መደበቂያ አድርጎ ሲያራክሰው፣ የእርሱን አመለካከት የማይጋሩትን የድርጅቱን አባላትን ደግሞ “የሚያፎደፉዱ፣ ወገበ ቢስ፣ እበላ ባዮች” እያለ ይዘልፋቸዋል፣ ለማዋረድ ይሞክራል።

Footnote # 8

ባለፉት ጥቂት ወራት የድርጅትን ደንቦች በመጣስ በከፍተኛ ደረጃ ድርጅቱን በመጉዳትና በማዳከም ሥራ ከተሰማሩት መካከል ሌላው ግለሰብ ደግሞ በየነ ገብራይ ነው። በየነ ገብራይ እንደ ጌታቸዉ በጋሻው እሱም በአምስተኛው ጉባዔ የተሳተፈና በተደረገው ሂደት ሁሉ ያለምንም ገደብ ሃሳቡን የሰጠ ነበር። በተለይም የትግል ስልትን በተመለከተ አማራጭ የትግል ስልት ነው ብሎ የሚለውን በማቅረብ ያለምንም እቀባና ገደብ መብቱን ተጠቅሞ የተሳተፈ ሲሆንና ስብሰባው አልቆ ወደመኖርያ ከተማው እንደደረሰ ጉባኤውን በተመለከተ ሲጽፍ " ... 5ኛው ጉባኤያችን ካሁን በፊት ጉባኤዎቻችን ልዩ ነበር ማለት እችላለሁ። ሃሳቦች በነጻ የተንሸራሸሩበት፣ ተሳታፊዎች ሁሉም በጣም ደስተኛና ጓዳዊ ፍቅራቸው ከፍተኛ የነበረበት ጉባኤ ነበር። ውጤቱም ያማረ ነበር" እንዳላለ ሁሉ ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ " አምስተኛ ጉባዔ ተብየው፣ የተደናቀፈው ጉባዔ፤ የተጨናገፈ ጉባዔ" ወደሚለው ስያሜ ነው የተዘዋወረው። በጉባዔ የተመረጠውን ምክር ቤትም አምባገነን ቡድን ማለቱን ተያያዘው።

በየነ ገብራይ "የንባ-ባንቢስ" የሚለውን መርዝ በማጋነንና "ከየንባ ጀርባ ቡድን አለ፣ የንባና ባምቢስ ብቻቸውን አይደሉም ይህን ያደረጉት" በሚል ውንጀላ በድርጅቱ ውስጥ መጠራጠርንና አለመረጋጋትን ለማስፋት ጥረት ሲያደርግ፣ የአባላት መብትና ህግ አስጠባቂ ኮሚሽኑና ምክር ቤቱ ነገሩ እስኪጣራ ለኮሚሽኑ ዕድል እንዲሰጥና አባላትም በዚህ ጉዳይ በመድረኩ ላይ እንዳይጽፉ የተሰጠውን መመሪያም የህገ-ደንባችንን ክፍል 4 አንቀጽ 1 ቁጥር 1.2 እና 1.3 እንዲሁም ክፍል 4 አንቀጽ 4 ቁጥር 4.3.1 እና ክፍል 5 አንቀጽ 4 ቁጥር 4.2፣ 4.3 እና 4.8 በማንአለብኝነት በመተላለፍ ችግሩን ለማራገብ ሞክሯል።

በየነ ገብራይ በማንአለብኝነቱ በመቀጠል የመድረኩን ህግ በመተላለፍ ከመድረኩ ሲታገድ ከጥላሁን በፈቃዱ፣ ከጌታቸው በጋሻውና መሰሎቹ ጋር በመሆን በድርጅቱ ስም ከህግ ውጭ ያቋቋሙትን መድረክ በመደገፍና ሌሎችንም ይህንኑ ሕገወጥ መድረክ እንዲቀላቀሉ በማበረታታት በጸረ ድርጅት እንቅስቃሴ ላይ ተሳትፏል።

በየነ ገብራይ በዚሁ የማፍረስ ሥራው በመግፋት ህግ በመተላለፍ በተቋቋመውና ከድርጅቱ ውጭ ያሉ ግለሰቦች ባሉበት መድረክ ላይ የድርጅቱን ህገ ደንብ ክፍል 5 አንቀጽ 4 ቁጥር 4.5 እና 4.6 በመተላለፍ ተሰጥቶት በነበረው የድርጅት ሃላፊነት ያውቃቸው የነበሩ የድርጅት መዋቅሮችንና የድርጅት ሚስጥሮችን አውጥቷል። በመሆኑም ተጥሎበት የነበረውን ድርጅታዊ አመኔታ አጉድሏል።

ባለፈው ምክር ቤት የመጨረሻ በፕሌነም አላግባብ ተገምግሚያለሁ ብሎ ሁለት ጓዶችን ከሶ ለኮሚሽኑ ካቀረበና ጉዳዩ በኮሚሽኑ እጅ እያለ ሕጋዊ ሂደቱን ጠብቆ እንዳይሄድ ክሱን ያላአግባብ በመድረክ አሠራጭቷል። የአሠራር ደንባችንንም ጥሷል።

Footnote # 8

በየነ ገብራይ በአንድ በኩል ጉባኤው በተጠናቀቀ ጥቂት ወራት ውስጥ መድረክ ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄው መልስ የሚሆን የአባላት ቴሌኮንፈረንስ ቢጠራም ይህኑኑ ምክር ቤቱ የጠራውን የአባላት ቴሌኮንፈረንስ በመቃዎም ከመድረኩ ራሱን አግልሏል። ከዚያም በማስከተል ምንም እንኳን ምክር ቤቱ የአባላት ጠቅላላ ኮንፈረንስ ቢጠራምና በአግባብ መወያየትና እውነታዎችን ፈትሾ የማግኘት ሁኔታ ቢመቻችም በህገ-ወጥ መድረኩ በተለያየ ጊዜ ምክር ቤቱንና የመረጡትን አባላቱን ማጥላላቱንና በስድብ ማብጠልጠሉን ቀጥሎበታል። ከዚያም አልፎ እሱ የሚለው ካልሆነለት "በፓብሊክ" ወጥቶ ስድቡን እንደሚቀጥል ዝቷል። አቶ በየነ ገብራይ ሥርዓት ባጣና አላግባብ በተለጠጠ የመብት ስም ራሱን ከድርጅቱ ህልውና በላይ አድርጎ በመቁጠር አብዛኞቹ አባላት የተስማሙበትን ሕግና ደንብ ያጥላላል፤ ድርጅትን ያውካል። ለእርሱ ዴሞክራሲ ማለት እርሱ የጠላውን ሰው ክብረ ህሊና መግፈፍና ማንቋሸሽ፤ እንዳሻው ማዋረድ፤ በጉባዔ በአባላት ተመርጠው በሃላፊነት ላይ የተሠማሩትንም ጓዶቻቸውን የትግልና የሥርዓት መመሪያ አለመቀበል ነው።

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ግለሰቦች በተጨማሪ ዮሐንስ ሞገስ  የድርጅታችን ውስጠ ደንብ ለእያንዳንዱ አባል የሚፈቅደውን መብትና ግዴታ ያለከበረና ሌሎችም አባላት የፓርቲውን ሕግ በመጣስ ተባባሪዉ  እንዲሆኑ በሰፊው ቅስቀሳ ያደረገ ግለስብ ነው። ይህም ተግባሩ በድርጅቱ ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ ነግሶ ድርጅቱ ሊዳከም ወይም ሊበተን እንዲችል ያደርገው ጥረት መሆኑን እስካሁን ድረስ ባቀረባቸው ጽሁፎች ማረጋገጥ ይቻላል።

የንባ-ባንቢስ በመባል የሚታወቀው ክስ በውስጣችን መጥፎ ስንጥርን የፈጠረ አሳዛኝ ክስተት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ቢሆንም ጉዳዩ ተጣርቶ መፍትሔ እስከሚያገኝ ድረስ ትዕግስት አድርጋችሁ ጠብቁ በሚል የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ምክር ቤትና የሕግና የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሺን ለአባላት የሰጡትን መመሪያዎች መጣስ ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ ውስጥ ከየንባ- ባንቢስ ጀርባ ቡድን አለ በማለት ከፍተኛ የሆነ መጠራጠር ለመፍጠር ሞክሯል።

የሕግና የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሺን በየንባ-ባንቢስ ጉዳይ የወስነውን ውሳኔ አግባብ ባለው መንገድ ተቃውሞውን የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ሆኖ ሳለ ጉባኤ የመረጣቸውን የኮሚሽን አባላት "ለኛዎቹ ኮሚሺነሮች" በሚል በማናናቅና ኮሚሽኑንም  በቡድነኝነት በመፈረጅ ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻና ቅስቀሳ ያደረገና ሌሎችም እንዲከተሉት በሰፊው ጥሪ በማቅረብ ምክር ቤቱ ግዴታውን እንዳይወጣ ለማሰናከል ሙከራ አድርጓል።

ድርጅቱን በመከፋፈል ትልም በህገወጥነት የተቋቋመውን ፎረም በመደገፍ፣ በዚህ ሀገወጥ ፎርም ድርጅት አፍራሽ የሆኑ ቅስቀሳዎችና  የጥላቻ መንፈስ የተላበሰው ዘመቻ አካሂዷል/በማካሄድም ላይ ነው።

Footnote # 8

አባላትን ለማወያየት ምክር ቤቱ የጠራውን የቴሌፎን ስብሰባ አባላት እንዳይሳተፉ በይፋ ከፍተኛ ቅስቀሣ በማድረግ አባላት በድርጅታቸው ውስጥ ያለውን ጉዳይ እንዳይወያዩ እንቅፋት ለመሆን ሞክሯል።

የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ህጋዊ የአባላት የውይይት መድረክ (Forum) መተዳደሪ ደንብን በመጣስ የተደረገበትን የተሳትፎ እቀባ እንዲነሳለት ይቻል ዘንድ ለጥፋቶቹና ለሰሕተቶቹ ግለ-ሂስ እንዲያደርግ ምክር ቤቱ ላቀረበለት ጥያቄ ምንም ዓይነት ቀና መልስ አልሰጠም፤ ትብብር አላሳየም።

አባላት በበቂና በግልጽ ተወያይተው በጉባኤ የተወሰነን የትግል ስልት "የይስሙላ ትግል" ብሎ በመሰየም በትግሉ ለመቀጠል እንደማይፈልግ በህገወጡ ፎረማቸው ላይ ግልጽ እያደረገ በሌላ በኩል ግን በተለያየ መልክ በድርጅቱ ውስጥ አለመረጋጋት ለመፍጠር በሚደረገው አፍራሽ እንቅስቃሴ ከቀንደኛ ተዋናኞች አንዱ በመሆን እየተሳተፈ ነው።

በዶ/ር ጌታቸው በጋሻው፣ በበየነ ገብራይና በዮሐንስ ሞገስ ቀስቃሽነትና አቀነባባሪነት ይህ ሁሉ የተገለጸው ጥፋት እየተፈጸመ፤ ምክር ቤቱ ችግሮችን ለመፍታት በትዕግሥት የሚቻለውን ጥረት አድርጓል። ምክር ቤቱ በተወሰኑ ጓዶች የተሰነዘረውን የአባላት ኮንፈረንስ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ሃሳብ በመቀበል አጠቃላይ የአባላት ኮንፈረንስ በፈረንጆቹ የበጋ ወራት ውስጥ እንዲደረግ ወስኖ ለአባላቱ አሳውቋል። ሦስቱ ግለሰቦች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም አለ በሚሉት ችግር ላይ ሕግና ደንብን ተከትለው ከአባላት ጋር ለመወያየት ግለ-ሂስ አካሂደው እንዲመለሱ ሲጠየቁ ዶ/ር ጌታቸውና በየነ ገብራይ አሁንም ምክር ቤቱን በማንቋሸሽና በመዛት የተሰጣቸውን ዕድል መዋቅርን ጠብቀው ሳይሆን በዛው በከፈቱት ህገ-ወጥ መድረክ ውድቅ ሊያደርጉ ሲሞክሩ ዮሐንስ ሞገስ ለጥሪው መልስ መስጠቱን ትቶ በተመሳሳይ መንገድ የራሱን ተጻራሪ ሃሳብ መግፋቱን ቀጥሏል።

<u>ውድ የድርጅቱ አባላት፣</u>

ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው፣ በየነ ገብራይና ዮሐንስ ሞገስ ባለፉት ጥቂት ወራቶች ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉትን የድርጅቱን ህግጋት ጥሰዋል። የድርጅትን መሠረታዊ የሆነ የዴሞክራሲያዊ አሠራር፣ "ሁሉም አባላትና አካላት ለፓርቲው ጉባኤ ውሳኔዎች፣ ለፓርቲው መሠረታዊ ህግና ለደንቦቹ ተገዢ ይሆናሉ።" የሚለውን የድርጅታችን ደንብ (ህገ-ደንብ "ክፍል 4፣ ቁጥር1.2) በመጻረርና የጉባኤውን ውሳኔ ባለመቀበልና ተገዥ ባለመሆን፣ የአባላት ግዴታን በተመለከተ በሚደነግገው የህገ-ደንብ በክፍል 5፣ አንቀጽ4 በቁጥር 4.2 ፣ በ4.3፣ በ4.4፣ በ4.5፣ በ4.6 እና በ4.8 የተዘረዘሩትን በመተላለፍና ባለማክበር፣ እንዲሁም በርካታ የድርጅታችንን የሥነ-ምግባር ደንቦችን በመጣስና ከህግ በላይ በመሆን የድርጅቱን ትግል እንዲዳከም አስተዋጽዖ አድርገዋል፤ የድርጅቱን አባላት የትግል ስሜት ለመግደልና ተስፋ እንዲቆርጡ ለማድረግ ጥረዋል፣ ሌሎችን በማስተባበር ድርጅቱን ለመከፋፈል

Footnote # 8

ሞክረዋል፣ ተስጥቷቸው በነበረው ሃላፊነት ያውቁ የነበረውን የድርጅቱን ሚስጥር አመኔታ በማጉደል አውጥተዋል፣ በድርጅቱ ላይ አሲረዋል። ስለሆነም፣ በድርጅታችን ሕገ ደንብ ክፍል 5፣ አንቀጽ 7፣ ቁጥር 7.2-ሠ ፣ መሠረት ከዛሬ ከጥር ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ. ም (January 22, 2010) ጀምሮ ከኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባልነታቸው መታገዳቸውን እንድታውቁ ይሁን።

የኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) ምክር ቤት

<u>ግልባጭ</u>
ለኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) የሕገና የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚሽን

Footnote # 9

## አዲዮስ ኢሕአፓ (ዴ)

ሁሉንም ሀሳቦቼን እጋራለሁ ለማለት ሳይሆን፣ ሚቼ አቶ ዘርዑ ክሸን፣ ከተማ ውስጥ ከተመታን በኋላ ኢሕአፓ የሚባል ነገር እኮ የለም ብሎ ነበር አንድ ጊዜ። ይህም በወቅቱ አነጋግሮናል። ሆኖም ግን፣ በከተማ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መመታታችንንና በየእርከኑ የነበሩትን በርካታ የአመራር አባላትና የሰው ኃይላችንን እንደገበርን እያወቅን፣ የሕዝባችንን ችግር በመመልከት፣ በአገሪቱም ላይ ያንዣበቡትን አደጋዎች በማሰብና፣ ለትግሉም የተከፈለውን መስዋዕትነት በመገንዘብ እስቲ እንደምንም እያልን እንሞክረው ብለን በሠራዊቱ ውስጥ ችግር እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ (ማለትም ብተና ተብሎ እስከሚጠራው ጊዜ ድረስ ማለት ነው) በድርጅቱ ስም ስንቀሳቀስ ነበር። ከዚያ ከዝነኛው አራተኛ ፕሌኔምና የሠራዊቱ ብተና በኋላ ግን ይህ ድርጅት ውስጣዊ ልዩነቶችንና ችግሮችን በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታትና ለመታረም አለመቻሉን በተደጋጋሚ (በከተማና በገጠር) ስናየው አብዛኛው የድርጀቱ መሪዎችና አባላት ድርጅቱን ለቅቀን ወጥተናል። ከድርጅቱም ብንወጣም፣ ብዙዎቻችን ግን ትግሉን እናስቀጥላለን ብለው ድርጅቱንና ሠራዊቱን ይዘው በቀሩት የአንድ ጊዜ የትግል ጓዶቻችን ብለን በቆጠርናቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ ምንም ጠጠር ሳንወረውርባቸው፣ እንዲያውም ሲያሙን፣ በውጭ ስንረዳቸው ቆይተናል።

እንሁ በትግል እንቀጥላለን ብለው ድርጅቱ ውስጥ የቀሩት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ድርጅቱንና የሰማዕታቱን ታሪክ ከሌሎች ድርጅቱን ለመጉዳት ከሚሞክሩት ግለሰቦች ለመከላከል ተስኗቸው ሲጠቁና ሲያስጠቁ ስንመለከት ደግሞ፣ በተለይም ወንድሜ አቶ ሠለሞን ገብረስላሴና እኔ፣ በማዘንና በቁጭት በተለያዩ የጽሁፍና የንግግር መድረኮች ላይ በመገኘት፣ ቢያንስ ቢያንስ፣ ያንን መስዋዕትነትን በህይወቱ ጭምር ለትግሉና ለሕዝቡ የከፈለውን የጀግና ትውልድ ታሪክ ስንከላከል ከርመናል። ድርጅቱንና የአባላቱን የትግል ገድል ጥላሸት ለመቀባት ታጥቀው ተነስተው የነበሩትን ሰዎች ከሞላ ጎደል አሽማቀናል፣ በወቅቱም ለድርጅቱ ትንሽ የመተንፈሻ ቀዳዳ ለመፍጠር ረድተናል።

ወያኔ ሥልጣን ሊይዝ ሲቃረብና ሥልጣን ከያዘም በኋላ ለዚህ በኢሕአፓነት ለሚንቀሳቀሰው ድርጅት ስናድርግለት የነበረውን ድጋፍ በመጨመር ትብብራችን ድርጅታዊ ቅርጽና መግለጫ እንዲኖረውም አድርገናል። በርከት ያሉ ሕዝባዊ ድርጅቶች በየቦታው እንዲፈጠሩና የትግሉ ተባባሪዎች እንዲሆኑ ለማድረግ በቅተናል። በነበርንባቸው ተቋሞች ውስጥ፣ በተለይም በዩኒቨርስቲዎች፣ ኢሕአፓ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ላይ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ለፍተናል። ለምሳሌ፣ በወቅቱ በኢሕአፓ መሪነቱ ይታወቅ የነበረው አቶ መርሻ ዮሴፍ Michigan State University ያስተናግደው በነበረውና ብዙ እውቅ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ ምሁራን፣ እንዲሁም የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት በተሳተፉበት ታላቅ ዓለም አቀፋዊ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን ለወያኔ ካስረከቡት ረዳት የስቴት ዲፓርትመንት ፀሀፊና የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊ ሄርማን ኮሄን፣ ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ በቦታው ላይ ከነበረው የአሜሪካ አምባሳደር ሮበርት ሆዴክና አገናኛቸውና ጉዳይ አስፈጻሚያቸው ሆኖ ካገለገለው ፖል ሄንዚ ጋር በአጠቃላዩ ስብሰባ (ማለትም በ Plenary Session ላይ) በክብር እንዲጋበዝና መድረኩን ከነዚህ

Footnote # 9

ሰዎች ጋር እንዲጋራ ለማድረግ መቻላችን እንደ አብነት ሊጠቀስ ይችላል። ይህንን እድል በዚያን ጊዜ ያገኘ ሌላ አንድም ድርጅት አልነበረም። በዚህ አጋጣሚ ለሁለት ጓደኞቼና ባልደረቦቼ ለዶክተር አብርሃም እንግዳና ለዶክተር ብርሃኑ ዓለማዬሁ ልዩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ሌላም እንደ አንድ ትልቅ ምሳሌ የሚጠቀስ ጉዳይ አለ። ይህም የፓርቲው 25ኛው ዓመት ክብረ-በዓል (የብር ኢዮበሊዩ) ነው። ይህ በዓል የተከበረው በልዩ ድምቀት ነበር። በዓሉን ልዩ ያደረገው ደግሞ በጥራቱ፣ በጥልቀቱና በዓይነቱ ይህ ፓርቲ በታሪኩ ውስጥ እስከዛሬ ድረስ አድርጎት የማያውቀው የሁለት ቀን ስብሰባ (ወይም ሲምፖዚዬም) ነው። ወንበሮች በሙሉ ተይዘው፣ የስብሰባው አዳራሽ ቆመው በሚያዳምጡና በሚሳትፉ ሰዎች ተሞልቶ፣ የመቆሚያ ቦታ ያላገኙ ሰዎች ከስብሰባው ክፍል ውጭ ባለው መተላለፊያ መንገድ ላይ ተደርድረው በድምጽ ማጉያ ሲያዳምጡ የነበረበት ስብሰባ ነው። ይህ ስብሰባ የተመሰገነውና አባላቱ የተደሰቱበት ሊሆን የቻለው ድርጅቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቹን፣ ተቺዎቹንና ገለልተኞችን በአክብሮት ጋብዞና አስተናግዶ በቀረቡበት ክሶችና ሂሶች ላይ የራሱን የመከላከል መልስ ለመስጠት የቻለበት በመሆኑ ነው። ይህ ልዩ ስብሰባና የክብረ-በዓሉ ስነ-ስርአት በቪዲዮ ተቀርጾ በሰፊው ተበትኗል፣ ድርጅቱም ኮርቶበታል። በዚህም ላይ፣ ለስብሰባው ሙሉ በሙሉ መስካት እንደገና ሁለቱን ጓደኞቼን ዶክተር አብርሃም እንግዳንና ዶክተር ብርሃኑ ዓለማዬሁን እንደገና ከልብ አመሰግናለሁ።

እንግዲህ፣ ብዙዎቻችን የቀድሞ አባላት በድርጅቱ መዋቅር ውስጥ ሳንገባና ሳንሸበብ፣ ከገንዘብ ሌላ፣ ድርጅቱን ስንረዳው የነበርነው እዚህ ላይ በጠቀስኳቸውና በመሳሰሉት ዘዴዎች ነበር። ይህንን ሁሉ ስናደርግ ዛሬ በጠላትነት ፈርጀውኝ ሊያጠፉኝ የሚያልሙትና የሚለፉት፣ በተለይም በጣም እወዳቸውና አከብራቸው የነበሩት የካናዳ ወንድሞቼ (ዊንድሰርና ቶሮንቶ የነበሩት እነ አቶ ለይኩን ተሾመ፣አቶ መላኩ አወቀ፣አቶ መስፍን መድኅኔ፣ አቶ አክሊሉ ወንዳፈራሁ) ጠንቅቀው ያውቁታል፣ የምናቀርባቸው ዝግጅቶች ተጠቃሚና ተሳታፊ በመሆን። ይህን ድርጅት ይህን ያህል ስንረዳ፣ ድርጅቱ ጉድለት የለውም፣ ወይም ድርጅቱን ተመልሰን ለመቀላቀል እንፈልጋለን በማለት እንዳልሆነም ያውቁታል። ወደ ድርጅቱ እንድንመለስ ብዙ ብዙ ጊዜ ተጠይቀን ፈቃደኞችም እንዳልሆንን ያውቁታል። ከውጭ በመሆን ድርጅቱን ስንረዳ በኛ በኩል በዋናነት ከግንዛቤ ውስጥ ያስቀመጥናቸው ሁለት ቁምነገሮች (ወይም considerations) ሰማዕቶቻችንና ሕዝባችን ብቻ ነበሩ። ትተነው እንደሌሎች እንዳንቀመጥ የሰማዕቶቻችን ታሪክ፣ ራዕይና ገድል በማንም አልባሌዎች ሲብጠለጠልና ሲራከስ ድርጅቱ ሊከላከል አልቻለም። ይህንን ጥቃት መከላከልና ይህ ድርጅት ምናልባት ከደረሰበት ችግሮችና ሽንፈቶች በመማር እራሱን አርሞ እንደገና ለማደግና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አማራጭ አድርጎ ራሱን ሊያቀርብ ይችል ይሆናል በሚል ቀጭን ተስፋም ነበረን።

ወደ ድርጅቱ እንድንመለስ በቀናና በደግ አሳቢ አባላት ሲደረግብን የነበረው ጫና ቀላል አልነበረም። አቶ መርሻ ራሱ። ይህ ጫና እየበዛና እያሳዘነን ሲመጣ፣ ወደ 1998 ገደማ ይመስለኛል፣ አንድ ቀን አቶ ፋሲካ በለጠ፣ በጣም በሚያሳዝነኝና አንጀቴን በበላው አነጋገር ሲጠይቀኝ፣ "እሺ፣ በሕዝቡ ዓይን እኔ አባል ሆንኩ አልሆንኩ ብዙ ልዩነት የለውም፣ አባል አይደለም ብለው የሚያምኑ የሚኖሩ አይመስለኝም፣

Footnote # 9

በገንዘብ መርዳቱንም እቀጥላለሁ፣ አደባባይ ላይ ወጥቼ ድርጅቱን መከላከል በሁሉም መልኩ እንደ ድሮዬ አደርጋለሁ፣ ነገር ግን መዋቅር ውስጥ አልገባም፣ የሀሳብና የመናገር ነጻነቴ እስከተጠበቀልኝ ድረስና ይጠቅማል ብለህ እሰከአሰብክ ድረስ እንደ አባል ቁጠረኝ” ብዬ ስነግረው መስማማቱ ብቻ ሳይሆን የተደሰተው ደስታ እስታሁን ይታወሰኛል። ከመደሰቱም የተነሳ እንዲያውም ና እራት ልጋብዝሁ ብሎኝ ተያይዘን ወደ አንዱ አበሻ ምግብ ቤት ሄድን ዲሲ ውስጥ። እራትም በላን፤ አንዳንድ መለኪያ ወይንም ጠጣን። አንተ የሚታገል ድርጅት መሪ ነህና ገንዘቡን ለትግል አድርገው ብዬ ተቀላልደን ሂሳቡን ከፊዬ ጠበቅ አድርገን ተቃቀፍንና ተሰነባበትን። የኔ አባልነት ታሪክ እንግዲህ ይህ ነው።

በእንደዚህ እያለን ነው እንግዲህ ከዶክተር ብርሃኑ ዓለማዬሁ ጋር ሆነን በ2006 ወደ አራተኛው ጉባዔ ብቅ ያልነው። የሁለታችንም አመጣጥ ጉባዔውን ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ ሳይሆን እንዲሁ ለድጋፍ ያህል በመክፈቻውና በሚከተሉት አንድ ወይም ሁለት ቀናት ውስጥ ደግሞ አቢይ በሆኑ ሁለት ጉዳዮች ላይ ሀሳባችንን ሰጥተን ለመሄድ ነበር። ጉባኤው የተጀመረው ወደ ዓርብ ምሽት አካባቢ ይመስለኛል። ዶክተር ብርሃኑ ሰኞ ዕለት ሲመለስ እኔ ደግሞ ማክሰኞ ነበር የተመለስኩት። ጉባኤው ግን ያለቀው ዓርብ ነበር በሳምንቱ። ሰኞ ማታ ግን የዘላለም ጸጸቴ ሆኖ የቀረው አንድ ነገር ተፈጸመ። እነኝህ በጣም እወዳቸውና አከብራቸው የነበሩት የካናዳ ወንድሞቼ ያልኳቸው ወደ ክፍላቸው አስገብተውኝ ላለማድረግ ወስኜ ለራሴና ለቤተሰቤ የገባሁትን ቃል አስፈረሱኝ። በጣም በጣም ቅር እያለኝ፣ ሰውነቴ እየከፋው፣ አይገፉት ግፊትና ጫና አድርገውብኝ አመራር ውስጥ እንድገባ አስገደዱኝ። እወዳቸው ነበር፣ አከብራቸው ነበር፣ ላሳዝናቸው አልፈልኩም፣ ተሸነፍኩ። አሞኝ አደረ፣ ሆስፒታል የሚያስወስድ ባይሆንም። ስሜት እየተናነቀኝ፣ የማልፈልገውን ነገር ሰዎችን ላለማስከፋት ብዬ መፈጸሜ በራሴ ላይ እንድናደድ እያደረገኝ፣ ከዚህ የሚከተለውን አጭር መልዕክት ለጉባኤው ጽፌ ለወንድሜ አቶ ሠለሞን ገብረስላሴ ሰጥቼ ወደምኖርበት  አገር ተመለስኩ። በዚህ ላይ ዶክተር ብርሃኑን እጅግ አደንቀዋለሁ፣አመራር ውስጥ እንዲገባ ቢሞከር ቢገፋ ቢለመን ፍንክች አላለም፣ ወደ መኖሪያ አገሩ ከተመለስ በኋላም።

አቶ ሠለሞን ገብረስላሴ ለጉባኤው ያነበበው የመልክቴ ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል።

*4/11/06*

*ውድ ጓዶች፣*

*ወደዚህ የኢሕአፓ 4ኛ ጉባኤ የመጣሁት የአገራችንን የወደፊት ዕድል ሊወስኑ ይችላሉ ብዬ ባሰብኳቸው ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎች፣ (1) የትግል ስልት፣ (2) ኅብረት/ውህደት ላይ ለመወያዬትና ሀሳቤን ለመግለጥ ነው። አመራር ውስጥ ለመግባት ሀሳቡንም ፍላጎቱንም የለኝም። የሥራዬ፣ የኑሮዬና የቤተሰቤ ሁኔታዎች አንድ የኢሕአፓ አመራር መስራት የሚገባውን ያህል ለመስራት ያስችሉኛል ብዬ ካለመገመቴም በላይ፣ አሁን ለትግሉ እያበረከትኩኝ ነኝ ብዬ ከማምነው የእንቅስቃሴ ተግባር ውስጥ ያወጣኛል ብዬ እሰጋለሁ። ይህንንም በተደጋጋሚ ለብዙ ጓዶቼ ገልጫልሁ። እዚህ ጉባኤ ላይም ጥቆማውን አልቀበልም ብል እንዳያዝኑብኝ ለምኛቸዋለሁ። ሆኖም፤*

Footnote # 9

1. *እዚህ ከመጣሁ በኋላ በተለያዩ በርካታ አባላት ጫናና ተማጽኖ ስለቀረበልኝ፣*
2. *የኔ አመራር ውስጥ መግባት የጓዶችን እምነትና ድጋፍ የሚያጠነክር ከሆነ፣*
3. *መናገርና ሀሳብን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን በተግባር ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የግል ተሳትፎን በገቢር ማሳዬት ለእምነት፣ ለተቀባይነትና አስተዋጾ ለማበርከት ጠቃሚ በመሆኑ ጥቆማውን (nominationኑን) ለመቀበል ተገድጃለሁ።*

*ሆኖም ግን፣*

1. *በቂ ጓዶች የሚገኙ ከሆነ፣*
2. *በሌላ በኩል፣ በተለይም ከፓርቲው ውጭ ካሉ ዴሞክራሲያዊ ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር መስራት የበለጠ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ከተገመተ*

*ከምርጫው ብታወጡኝ ደስተኛ እሆናለሁ። በአጠቃላይ፣ ከዚህ ጉባኤ ውሳኔና ከጓዶቹ ፍላጎት ውጭ ልሆን አልችልም።*

*ጌታቸው በጋሻው (ፊርማ)*

እንግዲህ፣ በዚህ ሁኔታና መልኩ ነው እኔ ወደ ድርጅት አመራርነት (ከአኮ) በከፍተኛ ድምጽ የተመረጥኩት። ለምንድነው ይህን ሁሉ መናገር ያስፈለገው?

የኔን ከድርጅት መባረር አስመልክቶ ድርጅቱን አንቆት ያለው የቡድን አመራር January 22, 2010 አንድ ደብዳቤ ለኔ በግሌ፣ ሌላ ባለ 11 ገጽ ወረቀት ደግሞ ለመላው አባላት ልኮ ነበር። ደብዳቤው እንደደረሰኝ ይህ ቡድነኛ አመራር የገነባውን የሀሰት ካብ የሚንድ የመልስ ደብዳቤ እጽፋለሁ ብዬ ነበር። ደብዳቤውንና ወረቀቱን ደግሜ ሳነብ፣ ለዚህ ዓይነቱ የማፈሪያ ጽሁፍ መልስ መስጠቱ ጊዜንና ጉልበት ከማጥፋት ሌላ በማይገባው ደረጃ ክብር እንደመስጠት ስለሚሆን ንቄ ብተወው ይሻላል ብዬ ነበር። ነገር ግን፣ ሰሞኑን ከአንዳንድ የድርጅቱ አባላት የተረዳኋቸው ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ከነከኑኝ። አንደኛው፣ ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ አንድ የመጨረሻ ዕድል ይሰጠው የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አሉ የምትላቸውን ችግሮች በጉባኤው ላይ ማቅረብ ነበረብህ የሚለው ነው። እነኝህ ሁለት ነጥቦች በሰፊው መብራራት ይኖርባቸዋል።

### ወደ ድርጅቱ እንድመለስ የመጨረሻ ዕድል

"ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ አንድ የመጨረሻ ዕድል ይሰጠው" የሚለውን ለመግለጽ ወይም ለማስረዳት የሚቻለው ወደ ኋላ ተመልሶ እኔ እንዴትና ለምን ፊቴን ወደ ድርጅቱ እንዳዞርኩ በመዘርዘር ነው። እንግዲህ፣ ከዚህ በላይ በዘረዘርኩት እንዴት ወደ ድርጅቱ እንደተመለስኩ ለሁሉም አባላት ግልጽ ይሆናል የሚል የተስፋ ግምት አለኝ። ባጭሩ፣ ድርጅቱ ታሪካችንን ከጥቃት ለመከላከል ባለመብቃቱ፣ አደባባይ ላይ ቆሞ ራሱን ለመግለጥና ለመከራከር ባለመቻሉና በዚህም ደግሞ የምናፍረው እኛ የቀድሞ አባላት ጭምር በመሆናችን ምናልባት ከደረሱበት ተደጋጋሚ ውስጣዊ ችግሮችና ሽንፈቶች በመማር ራሱን አርሞ አንድ የትግል ኃይል ይሆናል በሚል ተስፋና ለዚህም እርዳታ እንዲያገኝ ከማሰብ ብቻ ነው። ይህንን በተደጋጋሚ ለአባላት ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። በሕዝቡ እይታ ይህ ድርጅት ብዙ ሽክምና ጉድፍ አለበት።

Footnote # 9

አውቃለሁ አንዳንዶቻችሁ ይህንን መስማት አትፈልጉም፣ ግን ሀቁ ይህ ነው። እኔ በዚህ ድርጅት አማካይነት የማገኘው አንዳችም ጥቅም የለም፣ በስም፣ በግንኙነት፣ በገንዘብ፣ በጊዜና በጉልበት ከመጎዳት በስተቀር። ስለዚህ፣ በኔ አስተያዬት "ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ አንድ የመጨረሻ ዕድል ይሰጠው" የሚለው ትልቅ የስድብ ያህል ነው። ለዚያውም፣ አሁን ድርጅቱን አንቆ ያለውን ቡድነኛ አመራር ምንነትና ፍላጎት አረጋግጬ ካወቅኩኝ በኋላ።

ኢሕአፓ (ዴ) ብለን ልናሳድገው የለፋንለት ድርጅት ያበቃለት፣ May 16, 2010 ከምሽቱ 9:30 አቶ መርሻ ዮሴፍ ለአመራርነት በእጩነት ቀርቦ ሲቀበለውና ተመረጠ ተብሎ ሲታወጅ ነው። ነገር ግን፣ ምርጫ የሚባል ነገር እንዳልነበረ መስማማት ይኖርብናል፣ እውነት ምርጫ ምን ማለት እንደሆነ የምናውቅ ከሆነ። በዝቅተኛው ተራ ትርጓሜው ምርጫ ማለት ተወዳዳሪ እጩዎች ቀርበው የተወሰኑት በቂ ድምጽ አግኝተው ምድብ ቦታቸውን ሲይዙና ሌሎች ዝቅተኛ ድምጽ ያገኙት ደግሞ (ለምሳሌ፣ እንደ አቶ መርሻ ዮሴፍ ማለት ነው) ሲወድቁ ነው። ይህ ሳይኖር ማንም ተነስቶ አንዱን ሰው ስለ ጠቆመ ይህ ሰው ምንም ያህል ድምጽ ያግኝ አመራር ውስጥ ቢገባ ምርጫ ተደረገ ማለት አይደለም፤ በምርጫ መሰረታዊ ትርጓሜ ላይ ማፌዝ ነው የሚሆነው። በተጠለፈው ጉባኤ ላይ የሆነው ይህ ነው። 15 ሰዎች ተጠቆሙ፣ 15ቱም አመራር አባላት ሆኑ ተባለ፣ የመጨረሻዋን ትንሽ ድምጽ ያገኘው አቶ መርሻ ዮሴፍ ጭምር።

ዛሬ ኢሕአፓ (ዴ) የሚባል ድርጅት አለ ማለት እራስን ማታለል ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም መዋሸት ነው።

- ኢሕአፓ (ዴ) ቺካጎ ውስጥ የለም፣ ካሁን ቀደም ዮሀንስ ሞገስ እንዳለው በብዙ ከተሞች ያሉት አባላት ድርጅታዊ ግዴታዎቻቸውን በሁሉም መልኩ እርግፍ አድርገው ትተውታል፣
- ከተመረጡት 3 የአህጉራዊ ኮሚቴ አባላት ውስጥ 2ቱ ለቀው ወጥተዋል (በአባላት የተመረጠ ህጋዊ አህጉራዊ ኮሚቴ የለም ማለት ነው)፣
- ከተመረጡት 5 የመብት ኮሚሽን ውስጥ 2ቱ ወጥተዋል (በአባላት የተመረጠ ኮረም የሚሞላ የመብት ኮሚቴ የለም ማለት ነው)፣
- ከየከተማው ከድርጅት አባልነት በይፋ እየጻፉ ያሳወቁና እንዲሁ በዝምታ እራሳቸውን ያገለሉ አባላት በርካታ ሆነዋል።
- ወደ ማዕከሉ የሚመጣ የአባላት መዋጮ ካቆመ ወራት ተቆጥረዋል፣ ለሬዲዮ ማስኬጃ የተለመደውን ቶምቦላ ለመሸጥ እንኳን ፈቃደኛ ጠፍቷል።

ታዲያ ምኑ ላይ ነው ለኔ "ወደ ድርጅቱ እንዲመለስ አንድ የመጨረሻ ዕድል" የሚሰጠኝ? የአባላት ሞራል ወድቆ፣ መንፈሳቸው ተሰብሮ፣ ተስፋቸው ጨልሞ? ወይ! እራስን አለማወቅ! የሚባለው እንደዚህ ዓይነቱ ነው።

ወገኖቼ፣ ይህ ቅጥ አምባሩ የጠፋበትና ድርጅቱን ወዴት እየወሰደው እንዳለ ማወቅ የተሳነው ደካማ ቂመኛ ጨካኝ የቡድን አመራር በየነ ጉራን፣ ዮሀንስ ሞገስንና ጌታቸው በጋሻውን አባረርን ብሎ ቢፎክር ቢያሽካካ ከምንም አትቁጠሩት። እኛ ብቻ ሳንሆን ሁላችሁም በተግባር (objectively) ተበትናችኋል። አዎ፣ እንደተለመደው እየዋሿችሁ፣ አንድ ገጽ እንኳን ልትሞላ የማትችል የ 6 ወር ዘገባ በ11 ገጽ

Footnote # 9

እያባዙላችሁ፣ በጭፍኑ የዚህ ቡድነኛ እስረኞች የሆናችሁትን እንደ ጥገት እያለቡአችሁ እስከሚቻላቸው ድረስ ሊጋልቡአችሁ ይሞክራሉ። እያወቁ መታለል መብት ነው፣ ያንን ምንም ለማድረግ አይቻልም። ነገር ግን፣ ሀቁ ይሄው በኔና በሌሎችም ተነግሯችኋል። አንዴ መታለል ያለ ነው፣ አይከፋም፣ አታላዩ ይፈርበት እንጂ። ሁለቴ፣ ሶስቴ መታለል ግን.... (እናንተው ጭርሱት ... ሰደበን እንዳትሉኝ ደግሞ)። ይህንን ነጥብ ለማጠቃለል፣ አልፈልገውም እንጂ፣ ብፈልገውም ኖሮ "የመጨረሻው ዕድል" ተሰጥቶኝ የምመለስበት ድርጅት የለም!!! ጎሊናዬን ሽጬ፣ የአንድ ግለሰብ አገልጋይ አልሆንም ብዬ ከኢሕአፓ (ዴ) የአመራር ካውንስል በገዛ ፈቃዴና በራሴ ውሳኔ እንደወጣሁ ግን ምን ጊዜም አትርሱ።

**ለምን ጉባኤው ላይ አልተናገርክም?**

ሁለተኛውን ነጥብ፣ ማለትም "አሉ የምትላቸውን ችግሮች፣ በተለይም ስለ አቶ መርሻ ዮሴፍ በአመራርነት መመረጥን በጉባኤው ላይ ማቅረብ ነበረብህ" ወደሚለው ነጥብ ልዙር። ቡድኑም በዚህች ነጥብ ላይ ግብ ለማስቆጠር ሲለፉ ተመልክቻለሁ። ይህንን ነገር፣ ማለትም ለምን በጉባኤው ላይ እንዳላነሳሁት በካውንስሉ ስብሰባ ላይ ደጋግሜ ገልጫለሁ። አስፈላጊ ከሆነም ቃለ-ጉባኤዎቹን በዋቢነት ለማቅረብ እችላለሁ። የቡድኑ ጨዋታ የሞኝ ልቅሶ ሆኖ ነው እንጂ ለምን በጉባኤው ላይ እንዳላነሳሁት ግልጽ ነው። ለአባላትም በተለያዩ ጊዜያት በጽሁፍ ጭምር ለመግለጥ የሞከርኩ ይመስለኛል። አሁንም ግልጥ ካልሆነ እስቲ አንድ ጊዜ ልሞክር።

ጉባኤው የተዘጋጀውና የተካሄደው በካናዳ የካውንስሉ አባላት ነው (ዶክተር ታዬ ዘገዬ፣ አቶ መስፍን መድኅኔና አቶ ጌታቸው አየለ)። ጉባኤው የሚካሄደው አሜሪካ፣ ለዚያውም እኔ በምኖርበት ከተማ። አንድም የአመራር አባል ከአሜሪካ አልተጨመረበትም በጉባኤው አዘጋጅ ኮሚቴው ውስጥ። ያኔ እኔ ሁሉን ነገር ስሠራ ነገሮችን እመለከት የነበረው በእምነት፣ በቅንነትና በየዋኀነት ነበር። አዘጋጅ ኮሚቴው ለምን ከአሜሪካ ያሉትን ያመራር አባላት አልጨመረም ብዬ ራሴንም እንኳን አልጠየቅኩም። አሁን ጉዳዩን ቀረብ ብዬ ስመለከተው፣ እኔ የካውንስል አባል ከመሆኔም ሌላ ጉባኤው በሚካሄድበት ቦታ ላይ ስለሆንኩ የጉባኤው አዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ መኖር ነበረብኝ። ብዙው የጉባኤው አስተዳደራዊ ጉዳዮችና ውሳኔዎች ሲደረጉ ጉባኤው በሚካሄድበት ቦታ ያሉት የድርጅቱ አካላትና አባላት ማወቅና መረጃዎች መስጠት ይኖርባቸዋል። የጉባኤው ቦታ የተያዘው በኔና በአበራ ሲሳይ ስም፣ ለዋስትናና ለመገልገያ የተሰጠው የኔ ክሬዲት ካርድ፣ የሚፈለጉትን ግልጋሎቶች የምናቀርበው እኛ የቺካጎ አባላት፣ ሁሉን ነገር ከላይ ሆነው የሚቆጣጠሩትና የሚያዙት ግን ካናዳዎችና አቶ መርሻ ዮሴፍ ነበሩ። ድንቅ ነው። የጉባኤው ቀን እንኳን ሲወሰን ሳምንቱ በሙሉ ለኔ አይመችም ነበር። ያ ሳምንት የጠቅላላ ፈተና ሳምንት ነበር ለኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች። እኔ ደግሞ የዲፓርትመንቱ ኃላፍ ነኝ። ፈተና መስጠት ብቻ ሳይሆን ብዙ አስተዳድራዊ ውሳኔዎችን እምሰጥበት ሳምንት ነው። ከዚያ በፊት ያለው ሳምንት ለዶክተር ሰዒድ አይመችም ተባለ። ከጉባኤው በኋላ ያለው ሳምንት ለዶክተር ታዬ አይመችም ተባለ። ግድ የለም እኔው ልቸገር ብዬ ከአቅሜ በላይ የሆነ አጣብቂኝ ውስጥ እራሴን ከተትኩኝ ድርጅት ይጠቀማል ብዬ። ብዙዎቻችሁ ልብ ላትሉ ትችላላችሁ፣ ስብሰባ ላይ እያለሁ ለስልክ ብዙ ጊዜ እወጣ ነበር፣ ኢ-ሜይል ላይ ብዙ እሰራ ነበር። አንዳንዴ ሮጥ ብዬ ቢሮ ደረስ እያልኩ የሚፈረሙ ነገሮችን ፈርሜ፣ ውሳኔ የሚጠብቁ

Footnote # 9

ጉዳዮችን ከውኘ ነበር ወደ ጉባኤው እመለስ የነበረው። ይህ ሁሉ ለድርጅት። ቡድኑ ግን እዚያው ቁጭ ብሎ ሴራውን ያሴር ነበር። ትልቁ ሴራ አጀንዳ አቀራረጽ ላይ ነው።

ምርጫው ሆን ተብሎ የመጨረሻ አጀንዳ ሆነ። ምንም ጠቃሚነት በየሌላቸው ጉዳዮች ላይ ስብሰባው ተንዛዛ፣ አንድ ተናጋሪ መድረኩን ከያዘ ሲደክመው ብቻ ነበር የሚያቆመው። ጠቃሚ የሆኑት፣ ለምሳሌ እንደ ፓርቲው ህገ-ደንብ፣ የኮሚሽኑ ህገ-ደንብ ያሉት አጀንዳዎች፣ ወድ ኋላ ተገፉ። እነርሱም አልተጨረሱም። ቅዳሜ እለት ጊዜው ገፋ፣ መሸ፣ ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ሆነ፣ አዳራሹ ደግሞ የሚዘጋው ከምሽቱ በ10፡00 ሰዓት ነው። አሁንም ስለ ምርጫው የሚያወራ ወይም የሚያነሳ አንድም ሰው አልነበረም። ነሲቡም በፓርቲው ህገ-ደንብ ላይ ቀድም አድርጎ ወደ አንድ ስልሳ ገጾች ጽፎ ኖሮ፣ አንዴ መድረኩን ከያዘ በኋላ ላልተወሰነ ጊዜ ህገ-ደንቡ ላይ ያቀረባቸውን ሀሳቦች ይወቅጥ ነበር፣ ሊቀ-መንበሩም (አቶ ተሾመ) ከካናዳ ነው። አሁን እኔን በጣም ጨነቀኝ። ይናገራሉ ብዬ የገመትኳቸው በሙሉ አፋቸው ተለጎመ። እሁድ ጠዋት ብዙዎች ወደ መጡበት እንደሚመለሱና ምርጫ ሊደረግ እንደማይችል አውቅ ነበር። የሚናገር ሲጠፋ ስነ-ስርዓትና አካሄድ ብዬ ስብሰባውን አስቁሜ ያለውን የሰዓት ገደብና የምርጫውን ሁኔታ ለሊቀ-መንበሩ ለአቶ ተሾመ አስገነዘብኩ። ቡድኑ በዚያን ሰዓት ሁሉ አድፍጦ ይመለከት ነበር። አሁን ነገሩ ሲገባኝ ለካስ ምርጫው ባይደረግ ግድ አልነበራቸውም። ምክንያቱም በቀድሞ ካውንስል ውስጥ ነጻ ሀሳባ ያላቸውና በኅሊናቸው ድምጽ ይሰጡ ከነበሩት አምስት አባላት ውስጥ አራቱ (ዶክተር ሰዒድ፣ ሠለሞን፣ በየነና፣ ዶክተር ዓለማዬሁ) አሁን አመራር ውስጥ ለመቀጠል እንደማይፈልጉ በማያወላውል መንገድ ስለውሰኑ፣ ጉባኤው ለተቀሩት የካውንስል አባላት ሙሉ ውክልና (mandate) ሰጥቶ ቢበተን ቡድኑ ደስታኛ ይሆን ነበር። ስለዚህ፣ በጊዜ መቃጠል ምንም አልተጨነቀም ነበር ቡድኑ። ያም ካልሆነ፣ እነኝህ አራቱ (ኋላ ግን ዶክተር ዓለማዬሁ ላይ አመለካከታቸውን ቀይረው ያገኟቸው መሰለኝ) ወደ አመራሩ እስካልተመለሱና እኔን እንደምንም አባብለውኝ እንድቀበል ካደረጉኝ (በኔ መቀጠል እነርሱ የቀመሯት አንድ ምክንያት አላቸው -- በተለይ የውጭውን ሁኔታ አስመልክቶ) ለዚህ ለውሸት ምርጫ በደንብ ተዘጋጅተው መጥተዋል። ያደረጉትም ይህንኑ ነው። እኔን የገረመኝ ግን፣ ሌሎች ዛሬ ለዚህ ድርጅት እንጨነቃለን ብለው ትዝብት ውስጥ እስከሚወድቁ ድረስ ደፋ ቀና የሚሉት ቢያንስ ቢያንስ ለምን የጊዜው ለምርጫ መጣበብ እንዳልጨነቃቸው ነው። እንዲያው ድጋፍ አገኝ እንደሆን በማለት ትልቅ ሰው ነው ብዬ እምገምተውን አንድ ሰው ምነው ዝም የምትለው ጊዜው እንዲህ ሲባክን በማለት ስጠይቀው “ምን ላድርግ፣ ልጩህ እንዴ?” አለኝ። አልገባኝም፣ ዝም ብዬው አሳለፍኩኝ ብስጭቴን ውጬ። ነሲቡን ግን ውድ ጎን ወስጄው፣ ምን ነካህ መድረኩን እንዲህ ይዘህ ጊዜውን የምታቃጥለው? የአመራር አለመመረጥ ምን ማለት እንደሆነ ይሰማሃል? ብዬ ቅሬታዬን ገለጽኩለት፣ እርሱም በጣም ተሰማው። እንግዲህ፣ ከአቶ መርሻ እንደገና ወደ አመራሩ መመለስ ጀርባ የነበረው የአጀንዳ ሻጥርና የጊዜ ቁጥጥር ይህን ይመስላል።

አመራር ውስጥ ችግር እንደነበረ ለምን ቀደም ብለህ አልተናገርክም ለሚለው ጥያቄ መልሴ ቀላል ነው። አመራር ውስጥ ችግር የነበረው አቶ መርሻ ዮሴፍ ብቻ ነው። ሌሎቹ አጃቢዎቹና ተከታዮቹ ናቸው። እርሱ ከየሌለ ችግር አይሆኑም ነበር። ከርሱ ጫፉን ካላገኙ በክርክርም ብዙ አይገፉም ነበር። አንድ በጣም የሚያስቅ ምሳሌ ልንገራችሁ። አንዱ ሁሌ ቀደም ቀደም የሚል የአቶ መርሻ ዮሴፍ ጋሻ ጃግሬ፣ ካውንስሉ

Footnote # 9

ውስጥ በግንባር ጥያቄ ላይ ስንነጋገር፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ የግንባር ምስረታ ሂደታችንን ስለሚጠላና ስለሚፈራ፣ ይህ የካውንስል አባል "እኔ በአጠቃላዩ የግንባር ምስረታ ሂደታችን ላይ ችግር አለኝ። ስለዚህ፣ ለሚቀጥለው የካውንስል ስብሰባ በጽሁፍ አቀርባለሁ" አለና አወጀ። አቶ መርሻ ዮሴፍም ተደሰተ። እኔም ቀበል አድርጌ፣ ይህ በጣም ጥሩ እርምጃ ነው፣ ከቻልክ አንድ ሁለት ቀን ከስብሰባው በፊት ላክልን አንብበን እንድንመጣ አልኩኝና ተስማምተን አጀንዳው ተዘጋ። የስብሰባው ቀን ደረሰ፣ ወረቀቱም አልመጣም። የታል ወረቀቱ ብለን ስንጠይቅ (ይረሳሉ ብሎ ሲጸልይ ክርሞ እንደሆን አላውቅም) "ኦ፣ ስድስት ገጽ ከጻፍኩ በኋላ ልጄ መጥቶ መብራቱን አጠፋና ዶኩሜንቱ ጠፋ" ብሎ እርፍ። እኔ አፈርኩለት፣ የመብራት ኃይሉ ሲመለስ ኮምፒውተሩ recovered documents ብሎ እንደሚያወጣለት አናውቅም ብሎ ያስብ ይሆን? መቼም ዶክተር ሰዒድን በግልጽነቱ ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ብዬ እገምታለሁ፣ "ይህችማ ውሻው የቤት ሥራዬን በላብኝ ያለው የሰነፍ ተማሪ ነገር ናት" ብሎ ማለት። ለዚህ ለዋሸን የካውንስል አባል እንደገና ተሻማቀቅኩኝ።

የአቶ መርሻ ተከታዮች ብዙም ችግር አይደሉም፣ በክርክርም ብዙ አይገፉም፣አማራጭ ሀሳቦችን በማቅረብም እምብዛም ናቸው ብያለሁ። እንዲያውም፣ ብዙዎቹ ለብቻቸው ሲሆኑ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው። ችግሩ አቶ መርሻ ዮሴፍ ባለበት በጋራና በቡድን ሲሆኑ ብቻ ነው። ያኔ ነው ቂመኝነታቸው፣ ጨካኝነታቸው የሚመጣባቸው። በክርክርም ግግም ሊሉ ይችላሉ ያኔ። ለአንድ ነገር ተከራክረው ለሌላ ነገርም ድምጽ ይሰጣሉ አቶ ምርሻ ዮሴፍን ተከትለው። ለዚህም አንድ ሌላ ምሳሌ ልስጣችሁ። ከዚህ ከተጠለፈው 5ኛ ጉባኤ በኋላ ኮሚቴዎችን ማሟላት ነበረብን። እኔ ቀደም ብዬ ለካውንስሉ ስበሰባ ከአንድ 10 ቀናት በፊት እያንዳንዱ ኮሚቴ ውስጥ ስንት ሰዎችና እነርሱም እንማን ቢሆኑ እንድሚሻል በዝርዝር በጽሁፍ ሀሳቤን ለጠፍኩላቸው። እንደፈለጋቸው እንዲቀይሩ፣ እንዲያሻሽሉና እያንዳንዳቸው እፈለጉበት ኮሚቴ ውስጥ እራሳቸውን ቀደም አድርገው እንዲመድቡ ተማጽንኩ፣ ስብሰባውን ለማቀላጠፍ ስለሚረዳ። በዚህም መሰረት፣ ለስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሶስት ሰዎች በቂ ይሆናሉ በማለት ዶክተር ታዬ ዘገዬን (ለአስተዳደራዊ ቅልጥፍናውና ለጥሩ ሰነድ ያዥነቱ)፣ አቶ መስፍን ተፈራን (ዲሲ በመሆኑና ለብዙ ግንኙነቶች ሊረዳ የሚችል በመሆኑ)፣ አቶ ተሾመን (ለቴክኖሎጂ እውቀቱና ለአህጉራዊ ኮሚቴ ተመክሮው) በማሰብ ጠቆምኳቸው። ታዬኝ አቶ መርሻ ዮሴፍ ምን ያህል እንደተንጨረጨረ። ይታያችሁ፣ አንድም ሰው እስከ ስብሰባው ቀን ድረስ ባቀረብኩት ሊስት ላይ ሀሳብ አላቀረብም ካለ አቶ መስፍን መድኀኔ በስተቀር። እርሱም ቢሆን እርሱን የጠቆምኩበትን ኮሚቴ ተቃወመ እንጂ የራሱን አማራጭ ምድብ እንኳን አላቀረበም። እኔ የጥቆማ ሊስት ያቀረብኩት ስብሰባውን እንዲያፋጥንልን፣ ስብሰባው ላይ ተግናኝቶ እባክህ በሞቴ እዚህ ግባ እዚይ ሂድ የሚለውን የጊዜ ማጥፊያ ምልጃና ልመና ለማስወገድ ነበር። እንደፈራሁት ይህ አንድ አጀንዳ ከ 7 ሰዓት በላይ የፈጀ ቴሌኮንፈራንስ ሆነ።

ይህስ ይሁን፣ የሚገርመው የአቶ መርሻ ዮሴፍ አልሞት ባይ ተጋዳይነትና የአጃቢዎቹ ሁኔታ ነው። መጀመሪያ አቶ መርሻ ዮሴፍ እርሱ ብዙ ጊዜ በሥራ አስኪያጅነት እንደሠራና ብዙ ልምድ እንዳለው አወጀ ተክታዮቹን ከመስመር ለማስገባት። ቀጠለና ሥራው ብዙ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ አባላቱ 3 ሳይሆኑ 5 መሆን አለባቸው አለ። ሶስት ይሁኑ ከተባለ ዕድል አይኖረኝም ብሎ ሰጋ፣ አምስት ይሁኑ ከተባለ ብዙ ልምድ አለኝና እኔን ጠቁሙኝ ብሎ ለተከታዮቹ ቀደም አድርጎ መልክቱን ማስተላለፉ ነው።

Footnote # 9

ክርክር ተነሳ። እኔ፣ እንኳን ዛሬ ተከፍለን፣ ቀድሞ በአንድነት እንዳለንም 3 ሰዎች ብቻ ነበሩ (ዶክተር ታዬ ዘገዬ፣ ዮናስ (ስዊዘርላንድ)ና፣ አቶ ተገኝ ሞገስ ብቻ ብዬ ተከራከርኩ። ግግም ሊሉ ይችላሉ ያልኩትን ልብ በሉና ክርክራቸው ለዛና ቁምነገር እያጣ ሲሄድ ክርክሩን ለመቁረጥ እንችል ዘንድ አንድ ሀሳብ አቀረብኩ። ስለ ሥራው ብዙዎቻችን ካለን ግምት ይልቅ በቀድሞው ካውንስል የሥራ አስኪያጁን ሥራ ከሞላ ጎደል ይሠሩት የነበሩት ዶክተር ታዬ ዘገዬና ዶክተር ዓለማዬሁ አበበ ብቻ ነበሩና እነርሱ ምን ያህል ሰው እንድሚያስፈልግ ይንገሩን አልኩ። ሁለቱም ተራ በተራ 3 ሰው ብቻ ይበቃል ብለው መሰከሩ። ውይ! አቶ መርሻ ዮሴፍና ተከታዮቹ ጉድ ፈላባቸው። ሌላ ክርክር መፍጠር ነበረባቸው አቶ መርሻን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ ለማስገባት።

አንዱ የተጨነቀው የአቶ መርሻ ሰው "እሺ እኔም 3 ሰው ይበቃል ብዬ አምናለሁ፣ ነገር ግን አንዱ ሰው አቶ መርሻ ዮሴፍ ነው መሆን ያለበት" አለ። ይህ የካውንስል አባል በጣም አሳዘነኝ። ከቡድኑ ጋር በሰላም ለማደር ሲል የማያምንበትን ነገር ተናገረ። አቶ መርሻ ዮሴፍ የፈለገው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ መግባትን ብቻ ሳይሆን፣ ኮሚቴውን በበላይነት ለመቆጣጠርም ነበር። ለዚህ ደግሞ ዶክተር ታዬ ዘገዬን ማስወጣት ነበረበት። ለዚህም ታዬ ከዚህ ኮሚቴ ወጥቶ የድርጅት ኮሚቴ ውስጥ ቢገባ ይሻላል ብሎ ሀሳብ አቀረበ። በነገራችን ላይ ይህ ኮሚቴ እውነተኛ የድርጅት ሥራ ይሠራል ብዬ አላምንም፣ምንም የሚታይ ነገር ስለየለለ።

ዶክተር ታዬ ዘገዬ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጸሀፊ ነበርና አቶ መርሻ ዮሴፍ የእርሱን ቦታ ክፉኛ ተመኝቷት ነበር። እኔ ግን፣ እዚያው ስብሰባው ላይ በጣም አጥብቄ ተከራከርኩ ዶክተር ታዬ በዚያ ኮሚቴ ውስጥ እንዲቀር፣ ሥራው እንዳይበደል ብዬ። ኮሚቴው ብዙ የአስተዳደራዊ ጽሁፍ ሥራዎች (ደብዳቤዎችንና ዘገባዎችን ማርቀቅ) አሉበት። አቶ መርሻ ደግሞ መጻፍ አይችልም። ለዚህ ነው ዶክተር ታዬ እዚያ ቦታ ላይ የሚያስፈልገው። እዚህ ላይ የሚገርመው ነገር፣ ዶክተር ታዬስ ምን ትላለህ ተብሎ ሲጠየቅ፣ እራሱን እንደ ምን እንደሚያይ አላውቅም፣ጉሙዝ ምን ያውቃል ዓይነት መልስ ሰጠ። "ታዬ ምንም አይመርጥም እተመደበበት መስራት እንጂ" ብሎ በጣም አሳዘነኝ፤ ምነው ምንም ምርጫ የለውም? ሰው ዕቃ አይደል ሌላው እንደፈለገው የሚጠቀምበት።

በመጨረሻ ወደ ድምጽ መስጠት እንሂድ ተባለና ተከታዮቹ ትዕዛዙን በቀጥታ እዚያው ስብሰባ ላይ ተቀብለው ኖሮ 5 ሰዎች ይሁኑ የሚለው የአቶ መርሻ ፍላጎት ከ 2/3ኛ ድምጽ በላይ አግኝቶ እንዲያልፍ አደረጉ። ይሄ ነው ምንም የሀሳብ ነጻነት የሌለው የአቶ መርሻ ዮሴፍ ጉዳይ አስፈጻሚ ካውንስል። እነኝህ ናቸው ጎሊናቸው በሚነግራቸው መሠረት ድምጽ ለመስጠት የማይችሉ የኢሕአፓ (ዴ) መሪዎች። እንደገና፣ እንህ ናቸው "ይንቀናል፣ ይሰድበናል፣ አምባገነን ነው እርሱ" የሚሉኝ። ምነው ባላወቅኳቸው ኖሮ እስከነጭራሹ። አይ! ብዙ ብዙ ምሳሌዎችን ለጠቅስላችሁ እችላል ነበር፣ ነገርን ማስፋት ብቻ ነው የሚሆነው ብዬ ትቼዋለሁ።

ባጠቃላይ፣ አቶ መርሻ እስካለ ድረስ ነገረ-ሥራቸው ሁሉ የሞኝ ሥራ ይመስላል የተከታዮቹ። ይህ ግን፣ እስከዛሬ ድረስ አቶ መርሻን ጠቅሞታል። "ሞኝ ያሸንፋል፣ እንዴት ብሎ፣ እምቢ ብሎ" እንዳሉት። እርሱ ያስያዛቸውን ግግም ብለው እስኪሰለች ይደጋግሙታል። በመጨረሻ ወደ ድምጽ መስጠት ይኬዳል።

Footnote # 9

ድምጹ በቡድኑ መስመር ይቆጠራል። ውጤቱ ምንም ይሁን ምንም፣ አቶ መርሻ ያለው ይሆናል። አቶ መርሻ ደግሞ አርቆ የሚያስብና አዳዲስ መላዎችን ለመፍጠር የሚችል ቢሆን ኖሮ እስከዚህም ባልከፋ ነበር። ነገር ግን፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ በሻገተ አስተሳሰብና አካሄድ የዛሬውን ዓለም ለመቆጣጠር ይሞክራል። ያው አሁን የምታዩት ነው፣ ድርጅቱን ይዞ ገደል ገባ፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ ለግላዊ ጥቅሙ ሲል።

እኔ እዚህ ላይ ለማሳረፍ የፈለግኩት፣ በካውንስሉ ውስጥ ችግሩ አቶ መርሻ ዮሴፍ ብቻ እንደሆነና እርሱ ከካውንስሉ ቢወገድ ተከታዮቹ ብዙም ችግር ሊፈጥሩ የማይችሉ መሆናቸውን ብቻ ነው። ደጋግሞ በማስረዳትና ጠበቅ አድርጎ በመከራከር ድርጅቱን ለማሳደግ የሚችሉ ነገሮችን ለመሥራትና ጉዳዮችን ለማስፈጸም የተከታዮቹን ትብብር ለማግኘት ይቻል ነበር። ሳይሆን ቀረ፣ ድርጅት ለአቶ መርሻ ዮሴፍ ፍላጎትና ምቾት ተሰዋ።

ታዲያስ ይህንን ሁሉ ብሶትህንና ችግሮች ለምን ጉባዔ ላይ ትንፍሽ ሳትል ቀረህ ብላችሁ የጠየቃችሁኝ አላችሁ። ጥሩ ጥያቄ። መልሱ ደግሞ አቶ መርሻ ዮሴፍ ሸነገለኝ፣ አቶ መርሻ ዋሸኝ፣ አቶ መርሻ ካደኝ፣ አቶ መርሻ አታለለኝ ነው ባጭሩ። ቀደም አድርጌ የምርጫው አጀንዳ እንዴት ወደ መጨረሻ ላይ እንዲሆን እንደተደረገና ጉባኤ ሊጠናቀቅ አንድ ሰዓት ሲቀረው ጮሄ በስነ-ስርአትና በአካሄድ ጥያቄ ስብሰባውን አስቁሜ ሊቀ-መንበሩ ወደ ምርጫ አጀንዳ እንደወሰደን ገልጫለሁ።

ከምርጫው ቀደም አድርገህ ለምን አጀንዳ አስይዘህ ስለ ውስጣዊ ችግሩ ተናግረህ አቶ መርሻ ዮሴፍ እንዳይመረጥ አልተናገርክም የምትሉ ከሆነ ሁለት ነገሮችን እንድትገነዘቡ እጋብዛችኋለሁ። አንደኛው፣ ሰው ይመረጥ አይመረጥ የሚባለው ነገር የሚነሳው በምርጫ አጀንዳ ላይ ነው እንጂ ራሱን የቻለ አጀንዳ ሆኖ አይደለም። ሁለተኛውና ዋነኛው፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ ከጉባኤው አስቀድሞ፣ ካናዳ ውስጥ እያለ፣ ከተከታዮቹ ጋር ተማክሮና አሲሮ፣ ውረድ ብሎ ጥያቄውን ያቀረበለትን አቶ ሠለሞን ገብረስላሴን ትቶ፣ ለኔ ስልክ ደውሎ፣ "እኔ በዕድሜ፣ በጤናና ለረጅም ጊዜ ስልጣን ላይ በመቆዬቴ ለምርጫ አልቀርብም" ብሎኝ ቃል ከሰጠኝ በኋላ፣ "የሶስታችን በአንድ ጊዜ መልቀቅ ለድርጅታችን ገጽታ ይሁን ለቀጣይነቱ ስለማይበጅ አንተ መቀጠል አለብህ" ብሎ ተማጸነኝ። እኔ እስከ ቅዳሜ፣ May 16፣ ከምሽቱ 9:30 ድረስ የማውቀው ይህንኑ ብቻ ነው። አቶ መርሻ ዮሴፍ፣ በዚህ የመውረዱ ጥያቄ ላይ፣ መዋሸቱን፣ መካዱን፣ ማሴሩንና መሸንገሉን ፈጽሞ አላውቅም ነበር። እግዜር ይስጠውና፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ፣ በካውንስሉ ስብሰባ ላይም ይህንን የገባልኝን ቃል አልካደውም። "እኔ ለአንድ ሰው ቃል ገባሁ ብዬ፣ የሌሎችን ጓዶችን ጥያቄና ፍላጎት አልረግጥም" ነው ያለው በስብሰባችን ላይ።

እንግዲህ፣ ከላይ ለማሳዬት እንደሞከርኩት፣ እኔ ለካውንስሉ ችግር አቶ መርሻ ብቻ ነው ብዬ ነው የማምነው። ይህ ሰው ደግሞ አልመረጥም ብሎ ቃል ከሰጠኝ፣ ችግሩ ተወገደ ብዬ ነው የማምነው። ተከታዮቹ ችግሮች ናቸው ብዬ አላምንም ፈጽሞ። ገና ለመጠንከርና ለማደግ የምንሞክር ድርጅት ነን። ችግሮችን በዘዴና በብልሃት ለማስወገድ ከቻልን ችግር አለ ብሎ ማወጅና ሽብር መፍጠር አያስፈልግም። የችግሮች ሁሉ ምንጭ የሆነው አቶ መርሻ ዮሴፍ በክብር እወርዳለሁ ካለኝ እኔ ለምንድነው የለም ከመውረዱ በፊት ይህን ሰው ያዙልኝ፣ እርገሙልኝ፣ አስወጡልኝ.... ማለት የሚኖርብኝ?በተጻራሪው፣

Footnote # 9

እወርዳለሁ ብሎ ቃል ሲሰጠኝ አከብርሃለሁ፣ እወድሃለሁ ነው ያልኩት። ይህንን ስታደርግም ነው በሌሎች ዘንድም የምትወደደው፣ የምትከበረው፤ እንደ አርአያ የምትጠቀሰው፣ ለሌሎች ድርጅቶችም ትምህርት የምትሆነው ብዬ ነው ያመሰገንኩት። ለካስ አጅሬ በልቡ የያዘው ሌላ፣ ጭፍን ተከታዮቹን ያዘጋጃቸው በሌላ። አታለለኝ፣ ካደኝ፣ ዋሸኝ፣ ሸነገለኝ የምለው ይህንን ነው።

ሌሎች እንደኔ ያልተሞኙ ነበሩ። ስልክ ይደውሉና ይህ ሰው በየከተማዎቹ እየተዘዋወረ የምርጫ ዘመቻ (campaign) እያደረገ ነው "ሙሉ ጤናማ ነኝ፣ ጉልበቴ ጠንካራ ነው፣ ሽምግልና አይሰማኝም…እያለ" ብለው ሲነግሩኝ እኔ በተቃራኒው ነበር እምከራከራቸው። እርሱ ዳግመኛ ለምርጫ እንደማይቀርብ ቃሉን ሰጥቶኛል፣ አሁን በየከተሞቹ የሚዞረው ድርጅትን ለማጠናከርና ጓዶችን ለማጠንከር ነው፣ ይህንን ቃሉን የማያከብር ከሆነ ከካውንስሉ ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ ሠለሞንና እኔ እንቃወመዋለን ብዬ ስነግራቸው አዙረው እኔን ይመክሩኝ ነበር። የለም አንተ አታድርገው፣ እስካሁን ከርሱ ጋር ያደረግከው ስምምነት ይበቃል፣ በሌሎች ዘንድ ተከታዮቹ እየቀሰቀሱ ያሉት "ጌታቸው የሚፎካከረው ከመርሻ ጋር ነው" እያሉ ነውና አንተ ተነስተህ በስብሰባው ላይ ብትቃወመው ነገሩ በተለየ መልክ ነው የሚታዬው ይሉኝ ነበር።

ይህንን ከላይ ያቀረብኩትን ምክንያት በግንዛቤ ውስጥ እንያዘውና፣ እስቲ የርሱ ስም ጥቆማ ሆን ተብሎ እስከ መጨረሻ በቡድኑ ተይዞ እንዲቆይ ተደርጎ ሊጠቃለል ባለበት ሰዓት ላይ እኔ ጥቆማውን ተነስቼ ብቃወም ምን ነበር የሚሆነው? ስምምነት ይግኝ ነበር? ያ ስብሰባ በሰላም ይጠቃለል ነበር? ፈጽሞ፣ ቀውጢ ነበር የሚሆነው። ነገሮች መንልንል ይጀምሩ ነበር፣ እሰጥ አገባው ይጦፍ ነበር፣ ያውም በሠላም ለመደማመጥ ቢቻል ኖሮ። በማያጠራጥር መልኩ ስብሰባው እጅግ በጣም አስጸያፊና አሳፋሪ ይሆን ነበር። ያንን ሆኔታ በዚያን ጊዜ የምጋብዝበት ምንም ምክንያት አልነበረም። አቶ መርሻ ዮሴፍ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ብሎ ድርጅቱን ለመሰዋት ወስኖና አሲሮ መጥቷል።

በብዙ አባላት ዘንድ ያልታወቀ ነገር አለ፣ አሁን ገና ለመገንዘብ የቻልኩት። የቡድን አመራሩ ብዙዎቻችሁን ለማሳመን የቻለው "ጌታቸው ከአመራሩ የወጣው አቶ መርሻ ዮሴፍ ካልወረደ ብሎ ነው" የሚለውን የሀሰት ክሱን ነው። እርግጥ ነው፣ የአቶ መርሻ አመራር ውስጥ መመለስ ድርጅቱን እንደሚጎዳ አምን ነበር። ይህንን ለርሱም፣ ለተከታዮቹም በግልጽ ነግሬአለሁ። ሆኖም ግን፣ አቶ መርሻ ተመረጠ ብዬ ሁሉን ነገር እርግፍ የማደርግበት ምክንያት የለም።

- አቶ መርሻ ከተመረጠ በኋላ ከርሱ ጋር ፓልቶክ ላይ ቀርቤአለሁ፣
- VOA ለድርጅታችን ክፍት እንዲሆን አድርጌአለሁ፣
- ከድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ቀጥያለሁ፣ የተደረጉትን የካውንስሉንና የግንባር ኮሚቴውን ስብሰባዎች በሙሉ ተካፍያለሁ።
- ካናዳ ድረስ ሄጄ የገጠመንን ችግር ለማቃለል ሞክሬአለሁ።
- ምንም እንኳን የርሱ መመረጥ ብዙ ዕድሎች እንዲያመልጡን ቢያደርግም፣ ካሁን ቀደም በተገኙት መልካም ውጤቶች ላይ በማተኮር ለመሥራት መቻል እንዳለብን ለአቶ መርሻና ለቡድኑ ነግሬአለሁ።

Footnote # 9

- ስንለያይም ደግሞ፣ ሁሌ እንደማደርገው አቅፌው ስሜው፣ገንዘብም ለኪሱ ሰጥቸው ነበር የተመለስኩት።

ይህን ያህል ነበር አቶ መርሻ በጉባኤው ተመረጠ ከተባለ በኋላ የሞከርኩትና ያደረግኩት። ከአመራሩ መውጣት ከቶውንም አልታሰበኝም፣ የድርጅቱ ለመቀጠል መቻል ከሁሉም ቀዳሚነት ነበረውና።

ችግሩ የመጣው አቶ መርሻ ዮሴፍ ኢሕአፓ (ዴ)ን እንደ ግል ንብረቱ ለመያዝና ለማዘዝ እንዲያስችለው እርሱና ቡድኑ እንቅስቃሴዎችን ሲጀምሩ ነው።

- የድርጅታችን ገጽታ አቶ መርሻ ዮሴፍ እንዲሆን ጣሩ፣
- ከአባላት የተነሱትን ችግሮች ለመደበቅ በሚያምቻቸው ዘዴ አባላትን በተናጠልና በሚያፍን ሁኔታ ለማነጋገርና ለማስፈራራት ሞከሩ፣
- ካለ አቶ መርሻ ዮሴፍ በስተቀር ማንም የካውንስሉ አባልና የአካባቢው ፓርቲ አካል የማያውቀውን ግለሰብ የኢሕአፓ (ዴ) አመራር ካውንስል አባል አደረጉ፣ ይህ ሰው የፓርቲ አባል ለመሆኑ እንኳን ምንም መረጃ የለም
- በካውንስሉ ውስጥ የሚደረጉት ድልደላዎች ሁሉንም የድርጅቱን እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር በሚያምቱት ሰዎች እንዲሞላ ለማድረግ ሞከሩ፣
- የካውንስሉ ድምጽ አሰጣጥ በቡድን ፍላጎትና ጥቅም ሆነ። ዴሞክራሲ፣ ማጆሪቲ፣ ማይኖሪቲ የሚባሉ ነገሮች ትርጉም አጡ።
- ለአቶ መርሻ ዮሴፍ የማይመቹ ሰዎች ወደ አመራር ካውንስሉ እንዳይገቡ ተቀሰቀሰባቸው (በየነ ጉራ፣ ለምሳሌ)
- አቶ መርሻ ዮሴፍን የሚቃወሙ ሰዎች በአባላት መድረክ እንዳይሳተፉ ታገዱ (ኃይለ ሥላሴ፣ ለምሳሌ)።

ከዚህ በኋላ ወደ ቁልቁለት እሽቅድምድም ሆነ።

**ለማጠቃለል ያህል**

ይህ በአቶ መርሻ ዮሴፍ የሚመራውና ኢሕአፓ (ዴ) ብሎ ራሱን የሚጠራው ወገን እውነተኛ ድርጅት አይደለም። ካሁን ቀደም በላኩላችሁ አንድ መልእክት ላይ ያሰፈርኩትን እንደገና ልጥቀስላችሁ።

> *እስከ ዛሬ ድረስ በኢሕአፓ ውስጥ ከቡድን ውጭ መስራት አይቻልም። የሚሞክር ካለም የእሳት እራት ይሆናል። የድርጅቱ ታሪክ የተሞላው በተፈራራቂነት የበላይነትን በጨበጡ የቡድን መሪዎችና በተቀናቃኞቹ የስልጣን ፉክቻ ነው። የታዩትን መከፋፈሎችና ውስጣዊ ችግሮች መለስ ብሎ መመልከቱ በቂ ይሆናል። አንድም ጊዜ ከአባላት ችግርና መከፋፈል ተነስቶ አያውቅም። የበለሳውን ጉዳይ ለማንሳት የሚፈልጉ ሊኖሩ ይቻላሉ። የበለሳውና አጠቃላይ ብተና የተባለው የሚዳ ሁኔታም ከመሪዎቹ መጣላት በኋላ (አራተኛው ፕሌኔም በመባል ከሚታወቀው) የተከሰተ ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታ ነው። ስለዚህ፥ የኢሕአፓ አባላት*

Footnote # 9

> *ሁልጊዜ የመሪዎች የስልጣን ፍላጎት ሰለባዎች ናቸው። የዛሬ ሁለት ዓመት የለውጥ አጋቹን ቡድን ጥለን ስንወጣ የቡድን ጨዋታውን እዚያው ቀብረን የመጣን መስሎን ነበር። በጣም ተሳስተናል በጣም ተታለናል። እዚያው ውስጥ ተፈጥሮ ጊዜንና ሁኔታን አድብቶ ሲጠብቅ የነበረ ቡድን እኛን ተጠቅሞብን በራሱ ቀደሞ ሊያደርገው ያልቻለውን የድርጅቱን መከፈል አጠናቆ ይኸው ዛሬ ነግሶብናል። ወደ ኋላ ዞር ብዬ ስመልከተው፥ መቼም እስከ ሰራን ድረስ በፖለቲካ ህይወታችን ውስጥ አንዳንድ ስህተት መፈጸማችን አይቀርም፥ ፓርቲውን የዛሬ ሁለት ዓመት ለመከፈል ያበቃው ይኸው የሁለት ቀደምት መሪዎቸ (የአቶ መርሻ ዮሴፍና የአቶ ኢያሱ ዓለማዬሁ) የስልጣን ፉክቻ መሆኑን ዛሬ በሙሉ ልቤ ተቀብዬዋለሁ። በዚህም ውስጥ ያላዋቂ ተባባሪ ሆኜ በመነዳቴም አዝናለሁ፥ እፀፀታለሁ። ፓርቲው መከፈል አልነበረበትም። ይህንን የመከፈል ሁኔታ እንደተገነዘብኩኝ፥ይህንን የአቶ መርሻ ዮሴፍ ቡድንን አምኜ አብሬ ከመዶለት፥ ከሁለቱም አልተባበርም ብዬ ሜዳውን ለሁለቱ የስልጣን ተፎካካሪዎቸ ለቅቄ መወጣት ነበረብኝ። ድርጅቱ ያኔ መከፈሉ ሊቀር የማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱ የተረጋገጠ ቢሆንም የአጥፊ ተባባሪ መሆን ግን አያስፈልግም። ይህ ክስተት እንደገና ሊቀለበስ ይገባዋል ብዬ አምናለሁ፥ እኔም በምችለው አቅሜ ለመርዳት አሞክራለሁ።*

ይህ ጥቅስ እውነት ነው፣ በጣም አምንበታለሁ። ዛሬ ብዙ ሰዎች አቶ መርሻ ዮሴፍ ድርጅቱን ለመክፈልና የራሱን ቡድንና ድርሻ ቆርሶ ለመውሰድ ጌታቸውን ተጠቀመበት ነው የሚሉት በውጭ። ትክክል ናቸው፣ ተጠቅሞብኛል። ከክፍፍሉ በፊት ድርጅቱ ውስጥ አየኋቸው ብዬ ያቀርብኳቸውን ችግሮች በመጠቀም የአቶ መርሻ ዮሴፍ ደካማ ቡድን ተጠመጠመብኝ። የተነሳው ውስጣዊ ችግር መፍትሄ እንዳያገኝ በእሳት ላይ ቤንዚን በመነስነስ እኔንና በሀቅ ለዴሞክራሲያዊ ውስጣዊ ስርዓት የተነሱትን ቅን አባላት በመገፋፋትና የበለጠ በማጣላት ለረጅም ጊዜ ሲያስቡትና ሲዶልቱ የነበረውን ህልማቸውን ፈጸሙ። ከአባላት ይቀርቡ የነበሩ ጊዜያዊ መፍትሄዎች በሙሉ ውድቅ እንዲሆኑና ተቻችሎ ዘላቂ መፍትሄዎች እንዲፈለጉና ድርጅታዊ አንድነቱ እንዳይጠበቅ ሌት ተቀን ሰሩ። እነኝህ የድርጅቱን መከፈል የገፉትና ዛሬም ከርሱ ጋር በመቆም የኔንና የሌሎች ሀቀኛ ታጋዮችን ስም ለማጥፋት መሳሪያ እየሆኑ ያሉት ግለሰቦች ለሀቀኛ ውስጣዊ ስርዓት የቆሙ ሳይሆኑ በክፋትና በጥላቻ የተሞሉ፣ ምንም የእውነተኝነትና የታጋይነት ስሜትና ኅሊና የሌላቸው የአቶ መርሻ ዮሴፍን ጥቅም ለመጠበቅ የተሰባሰቡ ጥርቅሞች ናቸው።

ዛሬ ድርጅት አለ ብለው ከነዚህ ጋር የቀሩት የዋህ አባላት እኔን እንደ ምሳሌና እንደ መቀጣጫ መውሰድ አለባቸው። ሁላችንም እንተዋወቃለን፣ ማንኛችን ለዚህ ድርጅት ምን ያህል እንደከፈልን፣ ማንኛችን ምን እንደሰራን በዝርዝር እናውቃለን። አቶ መርሻ ዮሴፍ ለአፉ፣ ለጥቅሙ፣ እንደ ታናሽ ወንድሜ ነው የማየው እያለ ከርሞ፣ ዛሬ እኔ ላይ ይህን ያህል ሴራና በደል የፈጸም ሰው ኅሊና ቢስ ቢሆን ብቻ ነው። አልመቸው ብሎት ነው እንጂ፣ *November 8, 2009* ለ 10 ሰዓት ሙሉ የሰሜን አሜርካ አባላቱን ጠርቶ በቴሌኮንፈራንስ ሲያስወቅጠኝና ሲያስረግመኝ የዋለ ሰው ምን ሊያደርገኝ እንደሚፈልግ መገመት አያዳግትም። በጣም ያሳዝናል፣ አቶ መርሻ ዮሴፍ ለማንኛችሁም ያለው ፍቅርና ጥላቻ የሚለካው ምን ያህል ለስልጣኑ ባላችሁ ታማኝነት፣ ምን ያህል ለጥቅሙና ለምኞቱ እንደምትጨነቁና ምን ያህል ገንዘብ በምትሰጡት ነው። ለድርጅት ግድ የለውም፣ አሁን የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት አለመፈለግ ብቻ

Footnote # 9

ሳይሆን፣ የጥቃት እርምጃዎችን ለመውሰድ በመሞከሩ ዛሬ ድርጅቱን ጥለው እየወጡ ያሉትን አባላት ብቻ መመልከቱ ይበቃል። ይህ ሰው እዚህ ድርጅት ውስጥ ያለው ለራሱ ነው። ይህ ሰው ይህ ድርጅት እርሱ ለሚያስበው ለራሱ ጥቅም የማይሆን ከሆን አስር ቦታ ቢበጣጠስ ቢበተን ግድ የለውም። አሁን እየሆነ ያለው ይህ ብቻ ነው። ህልሙና ምኞቱ የድርጅቱን ስም ብቻ ይዞ አንድ ቀን በሆነ አንድ ተዓምር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ አንድ የፖለቲካ መሪ ሆኖ መግባት ብቻ ነው።

ይህ ግለ-ሰብ በበላይነት የሚመራው ቡድን ወይም ድርጅት ፍትም ሊደርስ አይችልም። በሕዝብ ዘንድ አመኔታ አያገኝም። በሌሎች ድርጅቶች ዘንድ (እስከ ጉባኤው ድረስ የተገኘችው የፖለቲካ ካፒታል ተመንዝራ እስክታልቅ ድረስ ነው እንጂ) ምንም ክብርና እምነት የለውም፣ ሁሉም አይወዱትም። ኢሕአፓ (ዴ) የአቶ መርሻ ዮሴፍና ጥቂት አጃቢዎቹ ብቻ የሚተቃቀፉበትና የሚያላዝኑበት አሳፋሪ ስብስብ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።

የአቶ መርሻ ዮሴፍ እኩይ ተግባሮችና የኢሕአፓ በእንደዚህ ዓይነቶቹ ደካማና ራዕይ ቢሶች እጅ መውደቅ በታሪክ የሚያስወቅስ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገትና መብት ውድ ህይወታቸውን በመስዋዕትነት ያስረከቡትን ሰማዕቶቻችንን ማርከስና ማዋረድ ነው። ታዲያ፣ ዛሬ ወይም ትናንትና የኢሕአፓ አባላት የነበራችሁ በሙሉ፣ እስከመቼ ድረስ ነው ይህንን የታሪክ ዝቅጠት፣ ይህንን የታሪክ እፍረት የምትሸከሙትና የዚህን ገናና ድርጅት ታሪክ፣ መስዋዕትነትና ገድል ስታሰድቡና ስታዋርዱት የምትኖሩት? ታሪክና ጊዜ ይፈርዳችኋል!!

ጌታቸው በጋሻው

2/19/2010